«ትውልድ የገጠመውን የሥነ-ልቦና ወረራ የሀገሩን ታሪክ በማወቅ ሲወጣው ይችላል »
ገጽ 10

ዓድዋን ያከበረ የስነ ጥበብ አውደ ርዕይ
ገጽ 14

«ታሪክን ጠለቅ አድርጎ ለተገነዘበ ሰው ዓድዋ ብዙ ምስጢሮችን ያዘለ ነው»
ገጽ 16

አዲስ ዘመን
ኢፕድ
83ኛ ዓመት ቁጥር 173 የካቲት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ቅዳሜ
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# የዓድዋ አደራ ለአዲሱ ትውልድ



አዲሱ ገረመው

**ዜና ትንታኔ**

ላለፉት በርካታ ዓመታት የዓድዋ ድል ለተማሪና ሠራተኞች የዕረፍት ጊዜ፤ ለአንዳንዶች የትርፍ ሰዓት ሥራ ተጨማሪ ገቢ ከመሆን የዘለለ ብዙም ትርጉም እንዳልተሰጠው ይደመጣል። አሁን ግን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የመነቃቃት መንፈስ እያበበ እንደሚገኝም እየተነገረ ይገኛል። ለታሪካዊ ሰዎችና ቦታዎች ተገቢውን ክብር ከመስጠት ባሻገር ድሉን ከጀግኖች አባቶች ከተሰጠው አደራ ጋር ማክበር እንደሚገባ ምሁራን ይገልጻሉ። ለመሆኑ የዓድዋ ድል ለአዲሱ ትውልድ ምን አደራ ሰጠ?

የዓድዋ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




# የጥቁሮችን የጨለማ ዘመን የገፈፈው ድል

ሄለን ወንድምነው

**ዜና ሀተታ**

በዘመኑ ዓለም ለጨለማ አስተሳሰብ እጅ ሰጥታለች። የቆዳ ቀለም ሰውን ለሁለት ይከፍል ነበር። ጥቁርና ነጭ የተባለ የጌታና ሎሌ መደብ ተፈጥሯል። ይህም ሰዎችን የበላይና የበታች ያደርጋል ተብሎ የተጫነ የጭቆና ቀንበር፤ የሉዓላዊነት ተግዳሮት ነው። ይህ የቅኝ ግዛት እሳቤ እልፍ ዘመን አስቆጥሯል። እምነቱን በደምና በአጥታቸው ያሻሩት ጥቋቁሮቹ የዓድዋ አናብስት እስኪነሱ ድረስ።

ቅኝ ግዛት ነጮች የጥቁር ሕዝቦች የበላይ ነን ብለው ኃያልነታቸውን ያጸኑበት ነበር። ጥቁሮችም ይህንኑ አምነው ለዘመናት ተገዝተዋል። በ1888 ዓ.ም ጣሊያን ፋሽስት ዘመናዊ የጦር መሳሪያን ታጥቆ ኢትዮጵያን ለመውረር ዘመተ። ኢትዮጵውያን ሀገር ለመውረር የመጣውን ጠላት በኅብረት ሆነው በዓድዋ ተራራ ድል አደረጉት።

የዛሬ 128 ዓመት በቅኝ ገዥ የጣሊያን ፋሽስት ወታደሮች ላይ ኢትዮጵውያን ድልን ተቀዳጁ። ኢትዮጵያውያን በዓድዋ ተራራ የተቀዳጁት አንጸባራቂ ድል ነጮች በጥቁሮች መሸነፍ እንደሚችሉ ማረጋገጫ ሰጠ። ክስተቱ በባርነት ቀንበር የነበሩትን የጥቁር ሕዝቦችና የቅኝ አገዛዙን ተዋናዮች አስተሳሰብ ቀየረ።

የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያ አንድነት የነበረው አበርክቶ የአደባባይ ምስጢር ነው። የድሉን ትሩፋት በአሁኑ ዘመን ለመጠቀም ምን መደረግ አለበት። የዝግጅት ክፍላችንም የታሪክ ምሁራንን ምላሽ ጠይቋል።

የጥቁሮችን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






## “ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የኢትዮጵያ ዋናው መልኳ መሆኑን ከዓድዋ ዘመቻ በተሻለ ለማሳየት የቻለ ክስተት አናገኝም”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የኢትዮጵያ ዋናው መልኳ መሆኑን ከዓድዋ ዘመቻ በተሻለ ለማሳየት የቻለ ክስተት በዘመናዊ ታሪካችን አናገኝም ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ128ኛው የዓድዋ ድል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በመልዕክታቸው እናቶቻችንና አባቶቻችን ታላቁን የዓድዋ ድል ከሰጡን 128 ዓመታት ብናስቆጥርም የዓድዋ ድል የሰጠንን ዕሴቶች ግን በሚገባ የተጠቀምንባቸው አይመስለኝም፤

“ኅብረ ብሔራዊ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል








# “ኢትዮጵያዊያን በዓድዋ ድል ጠላትን ድል ከማድረግ ባሻገር ለጥቁር ሕዝቦች አልገዛም ባይነትን ያሳዩበት ነው”

- አቶ ተመስገን ጥሩነህ
የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያዊያን በዓድዋ ድል በአንድነት እና በትብብር ጠላትን ድል ከማድረግ ባሻገር ለጥቁር ሕዝቦች አልገዛም ባይነትን ያሳዩበት ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ።

"ዓድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ-መንግሥት ግንባታ" በሚል መሪ ሃሳብ ከጥር ዘጠኝ ቀን 2016 ጀምሮ ሲካሄድ የቆየው የሰላም ንቅናቄ ከፍተኛ የመንግሥት አመራሮች በተገኙበት ትናንት ተጠናቋል።

በማጠቃለያ መርሀ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ እንደገለጹት፤ኢትዮጵያ በዓድዋ ድል በጀግኖች ልጆቿ የጋራ ክንድና ተጋድሎ ጠላትን ድል ከማድረግ ባለፈ ለጥቁር ሕዝቦች አልገዛም ባይነትን ያሳየችበት ነው።

ዓድዋ ሦስት ቁልፍ ነገሮች ተደምረው ያስገኙት ድል ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እነሱም ኅብረት ፣ ፍቅርና ትብብር ናቸው ብለዋል።

አቶ ተመስገን ዓድዋ በህብረ ብሔራዊ አንድነት በተዋቀረው የኢትዮጵያውያን ኃይል የተገኘ አፍሪካዊ ድል መሆኑን ገልጸው፤ በዓድዋ ሙዚየም መታሰቢያ የቆሙላቸውን የጦር መሪዎች ስንመለከት ድሉ ህብረብሔራዊነታችን ያመጣው መሆኑን እንረዳለን ሲሉ ገልጸዋል።

የዓድዋ ዘማቾች ኅብረት የብሔር ብቻ አልነበረም፤ መሪዎች፣ መላው ኅብረተሰብ፣ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች፣ የኪነጥበብ ሰዎች፣ ስንቅ የሚያዘጋጁ እናቶች፣ ሴቶችና ወንዶች እንዲሁም ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ወዳጆች የዘመቱበት ነው ያሉት አቶ ተመስገን፤ የኢትዮጵያን ጠላቶች ለማንበርከክ ፣ ድህነትን ድል ለማድረግ ፣ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን ለማጥፋት በህብር ሆነን መዝመት ይገባናል ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

ዛሬም የምግብ ፣የኢኮኖሚ ፣ የኢነርጂ ፣የሳይበር ሉአላዊነታችንን ለማስከበር መነሳት ያለብን ሁላችንም ነን ሲሉም አስገዝበዋል።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም በበኩላቸው ፤ኢትዮጵያ ከማንም ሀገር ጋር ጦርነት ማድረግ ፈልጋ አታውቅም። ገፍቶ ለመጣ ጠላት ግን በአትንኩኝ ባይነት አሸናፊነትን በመቀዳጀትና ታሪካዊ ጀብድ በመፈጸም የምትታወቅ ናት ሲሉ ተናግረዋል።

ዓድዋ የአንድነታችን ሰንሰለት ፣ የነፃነታችን ሰንደቅ ፣ የጀግንነታችን ልህቀት መሆኑን ገልጸው፤ ድሉ የአንድ

ዘመን ክስተት ብቻ ሳይሆን የአሁኑ ትውልድ የሚማርበት የጀግኖች አሻራ ነው ብለዋል።

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ምሁራን ትውልዱን በመቅረጽ ለስኬታማ ሀገረ-መንግሥት ግንባታ አዎንታዊ ሚና መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት ናት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሆኖም በሀገሪቱ እየተከሰቱ ያሉ የደኅንነትና የእርስ በእርስ ግጭቶች ያላትን ገናና ታሪክ እያሳነሰ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ እያጋጠማት ያለውን ችግር ለማስተካከልም ምሁራን የአንበሳውን ድርሻ ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የተጀመረውን የሀገረ-መንግሥት ግንባታ ስኬታማ ለማድረግ የዛሬው ትውልድ ከትናንት የዓድዋ ጀግኖች ትብብርና አንድነት ትምህርት ሊወስድ ይገባል ብለዋል፡

የአሁኑ ትውልድ ድህነትና ኋላ ቀርነትን ታሪክ በማድረግ ለሀገር እድገት የራሱን አሻራ በማሳረፍ የዓድዋን ታሪክ መድገም ይኖርበታል ሲሉም አክለዋል።

"ዓድዋን ለዘላቂ ሰላምና ለጠንካራ ሀገረ-መንግሥት ግንባታ" በሚል ሲካሄድ የቆየውን ንቅናቄ ሰላም ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር በጋራ ያዘጋጁት መሆኑም በመርሀ ግብሩ ተገልጿል።

# ዓድዋ የሰው ልጆችን ሁሉ እኩልነት ያረጋገጠ ድል ነው

**መስከረም ሰይፉ**



ምክትል ፕሬዚዳንት ዘውዱ ገብረንጉስ



አርበኛ በርነሽ መላኩ



አርበኛ ሰብለ ንጋቱ

አዲስ አበባ፡- ዓድዋ የሰው ልጆችን ሁሉ እኩልነት ያረጋገጠ ድል መሆኑን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አመራርና አባላት አስታወቁ።

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳባቸውን የሰጡት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ምክትል ፕሬዚዳንት ዘውዱ ገብረንጉስ እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም የብርሀን ምንጭ በመሆን በጥቁሮች ላይ የነበረውን ጭቆና በመስበር የሰው ልጆችን እኩልነት ያረጋገጠ ድል ነው።

ዓድዋ በአጼ ምኒልክ መሪነት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተነስቶ የዘመተበት በመሆኑ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የጋራ የድል ውጤት ነው ያሉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ድሉ አባቶቻችን ደማቸውን አፍስሰው ያስተላለፉልን መሆኑን በመረዳት የአሁኑ ትውልድ በልማት ፣ በትምህርት ፣ በቴክኖሎጂ የጋራ ድሉን በመስራት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል ብለዋል።

ከውጭም ሆነ ከውስጥ ያሉ አካላት በኢትዮጵያ ከታሪክ ውጪ የሆኑ አላስፈላጊ ትርክቶች ለወጣቱ እየሰጡ ለሀገሩ ያለውን ነገር የማዛባት ሥራ እየሰሩ እንደሚገኙ አንስተው፤ ወጣቱም ይህንን አላስፈላጊ የሆነ ትርክት ሀገርን ከመጉዳት በስተቀር ምንም ትርፍ እንደሌለው በመረዳት ልዩነቶችን ማክበርና ችግሮችን በሃሳብ ልእልና መፍታት እንደሚኖርበት ጠቁመዋል።

ሌላኛው ኢፕድ ያነጋገራቸው ተተኪ አርበኛ በርነሽ መላኩ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል በጥቁሮችና በነጮች መሀከል የነበረውን ልዩነት ከመስበር በተጨማሪ የጾታ እኩልነት የታየበት ነው ብለዋል።

የዓድዋ ጦርነት በድል እንዲጠናቀቅ ከመሪዋ እቴጌ ጣይቱ ጀምሮ ሌሎች ሴት አርበኞች የወደቀን በማንሳት፣ ስንቅ በማቀበልና ሌሎች ሥራዎችን በማገዝ ትልቅ ሚና አኑረዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በሀገሪቱ አሁን ያለው ትልቅ ችግር አለመደማመጥና መከፋፈል ናቸው ያሉት ተተኪ አርበኛዋ፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜም በኢትዮጵያ ብዙ አለመግባባቶች ፣ ብዙ ልዩነቶች መኖራቸውን አውስተዋል።

ሕዝቡ የሀገሩ ሉዓላዊነት ሲነካ ሁሉም ችግሩን በመተው በአንድነት በመሰለፍ ጠላትን ማሸነፉን ገልጸው፤ ያሁኑ ትውልድም በብሄር፣ በሃይማኖት በጎሳ ሳይለያይ ችግሮቻቸውን በውይይት በመፍታት ሀገሩን ወደፊት ማስኬድ ይገባዋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር አባል ተተኪ አርበኛ ሰብለ ንጋቱ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል የመተባበር ውጤት መሆኑን ገልጸዋል።

አርበኛ ሰብለ፤ ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የድል ምሳሌ ነው ያሉ ሲሆን፤ ያሁኑ ትውልድም ለዓድዋ የሚገባውን ክብር በመስጠት ለልጆቹ ማስተማርና ማስተዋወቅ ይገባዋል ብለዋል።

# የዓድዋ ድልና የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ

**ሞገስ ጸጋዬ**



ዶክተር አለምሰገድ ደበሌ



አቶ ያለው ከበደ

**ዜና ትንታኔ**

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ለጥቁር ሕዝቦች አዲስ ምዕራፍ የተበሰረበት ዕለት ነው። ኢትዮጵያዊያን ከቅኝ ገዥዋ ጣሊያን ጋር ተዋግተው ነጻነታቸውን ያወጁበትና ለጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነ ድል የተመዘገበበት ዕለት ነው። ይህ ድል በርካታ ኃያላን ሀገራት በአዲስ አበባ ኤምባሲ በመክፈት መደበኛ ግንኙነት እንዲጀምሩ ምክንያት ሆኗል። ለዓለም አዲስ የዲፕሎማሲ ምዕራፍ የተከፈተበትና የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ መጉላት የጀመረበት መሆኑንም የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ።

128ኛው የዓድዋ ድልን በተመለከተ በአርሲ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህር የሆኑት አለምሰገድ ደበሌ(ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ሙሉ በሙሉ ያልተቀበሉ ሀገራት ለኢትዮጵያ እውቅና ለመስጠት የተገደዱበት ነው። ይህም ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል ነው።

ከዓድዋ ማግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ ነጻ ሀገር መሆኗን ሙሉ ለሙሉ የተቀበሉበትና የተለያዩ ሀገራት ኤምባሲያቸውን የከፈቱበት ወቅት ነው ያሉት ዶክተር ዓለምሰገድ፤ የተሸነፈችውን ጣልያን ጨምሮ፣ እንግሊዝ፣ ሩሲያ፣ ጀርመንና ሌሎች በቅኝ ግዛት የሚሳተፉ ኃያላን ሀገራት በኢትዮጵያ ኤምባሲ ከፍተዋል ብለዋል።

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ በዓለም ላይ እውቅና እንድታገኝ አስችሏታል ያሉት ዶክተሩ፤ በዓለም ደረጃ ለመታወቅም መብቃቷን ጠቁመዋል። ከዚህ ባሻገር ሉዓላዊነቷ መከበሩ ትልቅ ስኬት መሆኑን ተናግረዋል።

ዶክተር ዓለምሰገድ እንዳሉት፤ ይህ ሁሉ ከአዲስ አበባ ስምምነት በኋላ የመጣ ነው። ስለ ኢትዮጵያ ጥያቄ የተነሳበትና ለባርነት ትግል መሰረት የጣለ ነው። ኢትዮጵያም ቀስ በቀስ በተለያዩ ሀገራት ኤምባሲ በመክፈት የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንድታራምድ እድል ፈጥሯል። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ድል ያጎናጸፈ መሆኑን መናገር ይቻላል።

እንደ ዶክተር ዓለምሰገድ ገለጻ፤ በኢኮኖሚው መስክም የተለያዩ የንግድ ስምምነቶችን በመፈራረም ተጠቃሚ ለመሆን በቅታለች። የአሜሪካ የልኡካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ችላለች። በዚህም የኢትዮጵያና የአሜሪካ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ሊጀመር ችሏል። ሁለቱ ሀገራት የመደጋገፍና ኢትዮጵያም ምርቶቿን ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች በመላክ ወደ ገበያ እንድትገባ ያደረገ ታሪካዊ ድል ነው።

ዘመኑ የታጠቁ የነጭ ኃይሎች አፍሪካን በቅኝ ግዛት ስር አድርገው የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት ትልቅ ርብርብ ያደረጉበት ወቅት ነበር። ኢትዮጵያንም በቀላሉ እንገዛለን ብለው የመጡበትና በመጨረሻም የተሸነፉበት ታሪክ ነው። ይህም ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች አንገታቸውን ቀና እንዲያደርጉና ዓለም በአዲስ እይታ እንድትታይ ያስቻለ ነው። ዓድዋ ለጥቁር ሕዝቦች የኩራትና በራስ የመተማመን መንፈስ የሰጠም ነው።

በእንግሊዝ ሀገር በሎንዶን ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ ሕዝብና ባህል ጥናት ውስጥ መምህር የነበሩትና የዓለም አቀፍ የጥቁር ሕዝቦች የታሪክ፣ የቅርስና የትምህርት ማእከል የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙዩኒኬሽን ኃላፊ አቶ ያለው ከበደ በበኩላቸው፤ ዓድዋ ጥቁርን ያስተሳሰረ ድል ነው።

እንደ አቶ ያለው ገለጻ፤ የጥቁር ሕዝቦች ማእከል መሠረቱ የዓድዋ ድል ነው። ዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ የታየበትና ለዓለም ሕዝቦች እኩልነትና መስዋእትነት የተከፈለበት ድል ነው።

የጥቁር ሕዝብ በየትኛውም ቦታ እንደ ሕዝብ ራሱን መከላከል እንደሚችል የታየበት ነው ያሉት አቶ ያለው፤ ዓድዋ ከኢትዮጵያ ውጪ የአፍሪካና የዓለም ጥቁር ሕዝብ የልብ ኩራት ነው ብለዋል።

በተለይ በቅኝ አገዛዝ የተሰበረውን የጥቁር ሕዝብ ሞራል እንዲነሳ ያደረገ፤ ነጭን ማሸነፍና በነፃነት መኖር ይቻላል የሚለውን ያረጋገጠ ድል ነው። ለጥቁር ሕዝብ አንዱና ትልቁ እሴት ነው። ከመቼውም ጊዜ በላይ ዓድዋ ጎልቶ እየታየ ነው፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም መገንባቱ ለአባቶቻችን ተጋድሎ ክብር መስጠቱን ያመለክታል።

ዓድዋ እንደ አዲስ ጎልቶ እየወጣ ነው ያሉት ኃላፊው፤ የዘንድሮው 128ኛው የዓድዋ ድል ሲከበር ከዓድዋ ድል መታሰቢያ እና ከዓለም አቀፍ የጥቁር ሕዝቦች የታሪክ፣ የቅርስና የትምህርት ማእከል አበርክቶዎች ጋር መሆኑንም ጠቅሰዋል።

የጥቁር ሕዝቦች ማዕከል አመሰራረቱ ዋናው ዓላማ በዓለም የታወቀ ዓለም አቀፍ የጥቁሮች ሙዚየም በኢትዮጵያ መገንባት ሲሆን፤ የአፍሪካ ሀገሮች የራሳቸውን እሴት ለሙዚየሙ ይሰጣሉ። በመላ ዓለም ያለው በሁሉም ዘርፍ ታዋቂ ጥቁር ዲያስፖራ ደግሞ ሽልማቶቻቸውንና መገለጫዎቻቸውን በስጦታ መልክ እንዲሰጡ ይደረጋል። በዚህ መሠረት ኢትዮጵያን የቱሪዝም የስህበት ማዕከል ለማድረግ አልሞ እየተሠራ ነው። ይህም ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ድል ነው።

እንደ አቶ ያለው ማብራሪያ፤ የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ በጥቁሮች መነገር አለበት፤ ለዚህ ምሳሌዋ ደግሞ ኢትዮጵያ ናት። ዓድዋን ለማጉላት ዓለም አቀፍ የጥቁሮች ማዕከል በኢትዮጵያ እንዲሆን ብዙ ሥራ በመሥራት ማሳካት ተችሏል። ይህም ለሀገር ገጽታ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

ዓድዋ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ሂደት ውስጥ ለሀገራችን ክብር አጎናጽፏል ያሉት አቶ ያለው፤ የዓድዋ ተጋድሎ ኢትዮጵያንና በመላው ዓለም በባርነት ያለውን የጥቁር ሕዝብ ክብር ያጎናጸፈ እንደሆነም ገልጸዋል። ኢትዮጵያን የነፃነት፣ የተጋድሎና የአርዓያነት ምልክት እንድትሆን ማስቻሉንም ጠቁመዋል።

በዓድዋ የኢትዮጵያ የአርበኝነት ተጋድሎ ለዘመናዊ የዲፕሎማሲ ጅማሮ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነበረው ያሉት ኃላፊው፤ በርካታ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር ዘመናዊ የሁለትዮሽ ግንኙነት ለመፍጠር ተነሳሽነት እንዲኖራቸው አድርጓል ብለዋል።

በዲፕሎማሲው ዘርፍም ከፍተኛ ሚናን እየተጫወተ መሆኑንና በአሁኑ ጊዜ መላው ጥቁር ሕዝብ ዓድዋን የራሳቸውና የአርበኝነት ቅርስ አድርገው በመውሰድ በራሳቸው እንዲኮሩ ያደረገ መሆኑን በመጥቀስ፤ ዓድዋ ከኢትዮጵያ አልፎ በዲፕሎማሲው ረገድ የጥቁር ሕዝብን ንቃተ ህሊናን ያሳደገና መመኪያ መሆን የቻለ ድል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከዓድዋ ድል ማግስት ጀምሮ ኢትዮጵያ ከበርካታ የአውሮፓ ሀገራት ጋር መደበኛ ግንኙነት ጀምራለች። ነፃ የሆነችና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምስረታ ውስጥ ለመሳተፍ በቅታለች። እንደ ሉዓላዊ ሀገር በመቆጠርና እውቅና በማግኘት በርካታ የሁለትዮሽ ስምምነቶችን በመፈራረም ጥቅሟን አስጠብቃ ቆይታለች። ከሀገሮች ጋር የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በመመስረት እስከ አሁን ድረስ በዓለም ደረጃ ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ለመሆን የበቃች አፍሪካዊት ሀገር ሆናለች ሲሉም ምሁራት ገልጸዋል።

# የዓድዋ ድል የተነጣይነትን ስሜት የገደለና አብሮነትን በጽኑ መሠረት ላይ ያኖረ ነው ሲሉ አፈ-ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል የተነጣይነትን ስሜት የገደለ፣ የወል እውነትንና አብሮነትን በጽኑ መሠረት ላይ ያኖረ ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ።

አፈጉባኤ አገኘሁ የዓድዋ ድልን 128ኛ ዓመት ክብረ በዓል አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያን ለማንበርከክ የውጭ ወራሪ ኃይሎች በተለያዩ ዘመናት መለስ ቀለስ እያሉ ሲተነኳኮሷት የነበሩ ቢሆንም ጀግኖች አባቶቻችን ጠላትን እንዳመጣጡ እየመከቱ በመመለስ ሀገራችንን ከቅኝ ተገዥነት ለማዳን በቅተዋል።

ፋሽስት ጣሊያን ከሌሎች ወራሪ ኃይሎች ከፍ ባለአደረጃጀት እና እቅድ ግዛታችንን ሰብሮ በመግባት ግልጽ ወረራ ፈጽሞብናል። ይህን የተመለከቱት የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመሪያቸውን አፄ ምኒልክ ጥሪ ተቀብለው ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከሁሉም የሀገራችን ጫፍ በኅብረት በመትመም የጠላትን ኃይል ዓድዋ ላይ ድባቅ በመምታት ድልን ተቀዳጅተዋል። የቅኝ ገዥዎችንም ሕልም እስከ ወዲያኛው እንዲጨናገፍ አድርገዋል። ይህ ድል የመላው ጥቁር ሕዝቦች ድል ሆኖም እንዲታወስ አድርገዋል ብለዋል።

አቶ አገኘሁ እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል የአብሮነት ሱታፌ ውጤት ነው፤ ኅብረት ገኖ የታየበት፣ መሪና ተመሪ የተናበቡበትና ከእኔነት ይልቅ እኛነት ተዳምረውና ተጋምደው ኃያል ክንድ የፈጠሩበት አውድ ነው። አብሮነት፣ መናበብና አንድነት ሲደመሩ ወኔን፣ ጉልበትንና ጥበብን ይፈጥራሉ፤ ከሚታለመው ግብ ለመድረስም ጉዞን ያፋጥናሉ። እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጀመርነውን ሁለንተናዊ የለውጥ ጉዞ ከግቡ ለማድረስ አብሮነትና የጋራ ርእይ ሊኖረን ይገባል የምንለው ከዓድዋ ብዙ ስለምንማር ነው።



የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ እንደሀገር በዓለም አደባባይ ስሟ ገኖ እንዲታይ የሆነበት፣ ኢትዮጵያዊነትም ለኢትዮጵያዊያን የክብር መጠሪያና በባርነት ለሚማቅቁ ጥቁር ሕዝቦች ደግሞ ስንቅና ትጥቅ ሆኖ ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ወኔ የሰነቁበት የሁሉም መጀመሪያ ነው።

የዓድዋ ድል ከሌሎች ድሎች ሁሉ ልቆ ታሪኩ ሳይደበዝዝ ዘመናትን እየተሻገረ የመቀጠሉ ምስጢር የአይቻልምን መንፈስ በመስበር «የሰው ልጅን» እኩልነት በዓለም አደባባይ የመሰከረ በመሆኑ ነው። የነጮች የበላይነት ያደረ እውነት «Universal Truth» ተደርጎ በሚታመንበት በዚያ የጨለማ ዘመን የዓድዋ ድል አዲስ እውነትን ያዘለች ፀሐይ በሰንሰለታማው የዓድዋ ተራሮች አናት ላይ ወለል ብላ እንድትወጣ ሆናለች። ጨለማን በብርሃን የገሰሰች፣ ሀሰትን ለእውነት ያስገበረች፣ የበላይነትን ክፉ እሳቤ ሰብራ እኩልነትን ያነበረች የአይበገሬነት ፀሐይ በዓድዋ ላይ ለመላው ዓለም ወጥታ ታይታለች ብለዋል።

የዓድዋ ድል የተነጣይነትን ስሜት የገደለ፣ የወል እውነትንና አብሮነትን በጽኑ መሠረት ላይ ያኖረ፣ በዘመናዊው ዓለም የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል ነጮች በጥቁሮች ላይ የነበራቸውን የኃያልነት እና በተለምዶ እውነት የሚመስለውን የነጭ የበላይነት የሀሰት ትርክት በእውነተኛው የእኩልነት ትርክት የቀየረ የዓለም ጉልህ የታሪክ ክስተት መሆኑንም አፈጉባኤ አገኘሁ ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል በኢትዮጵያዊያን ልብ ውስጥ ላለፉት 128 ዓመታት የማይዳሰስ ሐውልት ሆኖ ቆይቷል። ይህ የማይዳሰስ ሐውልት ከ128 ዓመታት በለውጡ መንግሥት ሕያው ሆኗል። የዘንድሮው የዓድዋ ድል በዓል ድምጽ አውጥቶ የራሱን የተሰነደ ታሪክ የሚናገር ታሪካዊ ሙዚዬም ተገንብቶ በተመረቀበት ማግስት የሚከበር በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል።

ሙዚዬሙ የዛሬው ትውልድ የተገነባበትን የታሪክ፣ የባህልና የማንነት ድርና ማግ እንዲገነዘብ፣ በተሰነዱ ታሪኮች ላይ በላቀ ደረጃ በመመራመር ለመላው ዓለም እንዲያስተዋውቅ የራሱን አበርክቶ ለማሳረፍ እድል ይፈጥራል ሲሉም ገልጸዋል።

የዓድዋ ድል በዓል የኅብረብሔራዊት ኢትዮጵያ ዘመን የማያደበዝዘው በዓል በመሆኑ የዓድዋ ታሪክ በተሰነደ መልኩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ታሪኩን በሚመጥን ደረጃ የአፍሪካ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ሙዚዬም መገንባቱ ትውልዱ ከአባቶቹ ታሪክ ተምሮ ጠንካራ ሀገረ መንግሥት በመገንባት የራሱን ታሪክ እንዲያስመዘግብ ያስችለዋል።

አቶ አገኘሁ፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከዓድዋ ድል ሕዝባዊ ፍቅርን፣ ወንድማማችነትንና እህትማማችነትን፣ ተምረን ሁሉም ዜጋ በነፃነት የሚኖርባት፣ የበለጸገች ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በመገንባት ሂደት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ የማበርከት ሥራችሁን አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ ሲሉም መልዕክት አስተላፈዋል።



ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር)

# የኢትዮጵያን ዲጂታል ኢኮኖሚ ለማፋጠን የኅብረተሰቡን የቴክኖሎጂ ግንዛቤ ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ዲጂታል ኢኮኖሚ ለማፋጠን የኅብረተሰቡን የቴክኖሎጂ ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ እንደሚሠራ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር) ገለጹ። የመጀመሪያው የዲጂታል ኢትዮጵያ ሳምንት የግንዛቤ ማስጨበጫ የማጠቃለያ መርሀ-ግብር ትናንት ተካሂዷል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ በዲጂታል ሳምንቱ የአይሲቲና የቴክኖሎጂ ዘርፍን ለሚመሩ የክልልና የከተማ አስተዳደር አመራሮች የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን አቅም ማሳየት ተችሏል። እንዲሁም ማህበረሰቡ ለቴክኖሎጂ ያለው ግንዛቤ እንዲሻሻልና አጠቃቀሙ ውጤታማ እንዲሆን በትኩረት እየተሠራ ነው።

ኢትዮጵያን ወደ ዲጂታል ኢኮኖሚ ልማት ለማስገባትና የታቀደውን የ10 ዓመት መሪ የልማት እቅድ ለማሳካት በቅንጅት መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ቀጣዩ ትውልድ ዲጂታል ቴክኖሎጂ የበለጸገች ኢትዮጵያን መረከብ እንዲችል ለሀገር በቀል እውቀት ቅድሚያ ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

በዘርፉ የበቃ የሰው ኃይል የማፍራት፣ የሕግ ማዕቀፎችን የማሻሻል ሥራዎች እንደሚሠራም አመልክተዋል።

በዲጂታል ሳምንቱ የኢትዮጵያን የዲጂታል ሽግግር ለማፋጠን የሚያስችል ግብዓት መገኘቱን ጠቅሰው፤ ሀገር በቀል የቴክኖሎጂ ሥርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ የሳይበር ደህንነትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

ቀልጣፋ የዲጂታል ግብይቶችን ለማከናወንና የመንግሥት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ የተደገፉ እንዲሆኑ አስቻይ ሁኔታዎች የማመቻቸት ሥራም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስረድተዋል።

በዝግጅቱ ላይ የተሳተፉ አመራሮች በዲጂታል ዘርፍ የተከናወኑ ሥራዎችንና ያገኙትን እውቀት ወደ ክልል ሲመለሱ ተግባራዊ ሊያደርጉ እንደሚገባ ይሽሩን (ዶ/ር) አመልክተዋል።

በዲጂታል ሳምንቱ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ፤ ኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ፣ ወረዳኔት፣ የግል ዳታ ጥበቃ፣ የኤሌክትሮኒክስ መንግሥት ስትራቴጂ፣ የመንግሥት የኢንተርፕራይዝ አርክቴክቸር፣ የኤሌክትሮኒክስ ግብይት አዋጅና የዳታ አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት መደረጉን ገልጸዋል።

በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግብርና፣ ቱሪዝምና የአምራች ዘርፉን ዲጂታለይዝድ ለማድረግ በትኩረት እየሠራ መሆኑንም አስረድተዋል።

የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025ን እቅድን ለማሳካት የኤሌክትሪክ ኃይልና ኢንተርኔት እስከ ቀበሌ ድረስ የመዘርጋትና የተለያዩ አስፈላጊ መሠረተ ልማቶች እየተከናወኑ ነው ብለዋል።

በተጨማሪም ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025ን እውን ለማድረግ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባለፈ ከሁሉም የመንግሥት ተቋማትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

# የዓድዋ ድል በአፍሪካ ደረጃ ሊከበር ይገባል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል ለአፍሪካዊያን ነጻነት ካበረከተው አስተዋጽኦ አንጻር በአፍሪካ ደረጃ እንዲከበር ኢትዮጵያ ተጽዕኖ ልትፈጥር ይገባል ሲሉ የታሪክ ምሁራን ገለጹ። የዓድዋ ድል ለመላው ጥቁር ሕዝቦች ለነጻነት ጎህ የቀደደና ለፓን አፍሪካኒዝም ውልደት ምክንያት የሆነ መሆኑን ምሁራኑ ገልጸዋል።

የታሪክ ምሁርና ተመራማሪ ኤምሬትስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዓድዋ ድል በአፍሪካ ደረጃ እንዲከበር ኢትዮጵያ ተጽዕኖ መፍጠር ይገባታል።

የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም መገንባቱ አንድ እርምጃ ወደፊት የሚያራምድ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ባህሩ፤ በአፍሪካ ኅብረት ላይም ድሉን ለመዘከር የሚረዳ ነገር እንዲቀመጥ ሃሳብ ሰጥተዋል።

የዓድዋ ድል በዓል በመላው አፍሪካ ለመዘከር የአፍሪካ ቀን ብሎ ማክበር ተገቢ እንደሆነም ነው ፕሮፌሰር ባህሩ የተናገሩት።

የዓድዋ ድል ለአፍሪካ ነጻነት ያበረከተው አስተዋጽኦ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ ለአብነትም በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች ዘንድ መነቃቃት ፈጥሯል ብለዋል።

እንደ ፕሮፌሰር ባህሩ ገለጻ፤ ፋሽስት ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ጊዜ በተለያዩ ክፍለ ዓለም የሚኖሩ የጥቁር ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ጎን ተሰልፈው ከፍተኛ ድጋፍ አድርገዋል። ይህም የዓድዋ ድል የነበረው አወንታዊ ተጽዕኖ ነው።



መምህር በላይ ደሳለኝ



ኤምሬትስ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

በአህጉሪቱ ስለ ዓድዋ የሚጽፉ ብዙ ምሁራን በመኖራቸው የነሱን ፈለግ ተከትሎ ዓድዋ በአፍሪካ ደረጃ እንዲታሰብ ሥራዎች መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር መምህር በላይ ደሳለኝ በበኩላቸው፤ ድሉ ለአፍሪካዊያን የጋራ ድል እንደመሆኑ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በአፍሪካ ኅብረት በኩል ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት ተጽእኖ መፍጠር አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል።

መምህር በላይ አክለውም፤ ዓድዋን በተመለከተ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን በማጠናከር የአፍሪካ ኅብረት አምኖ እንዲቀበል ማድረግ ይገባል ብለዋል። የመሪዎች ጉባዔም ከዓድዋ በዓል ጎን ለጎን የሚደረግበት መንገድ መፍጠር ተገቢ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚህ በፊት የዓድዋ ድል ለሁሉም አፍሪካዊ ነጻነት መሆኑን የማስገንዘብ እሳቤ ያለውና ስለ አፍሪካ ሀገራት ግንኙነት ትምህርት የሚሰጥበት ዓድዋ ላይ የፓን አፍሪካን ዩኒቨርሲቲ እንዲከፈት ተደርጎ እንደነበር ያስታወሱት መምህሩ፤ አሁንም ይህን ማጠናከር እንደሚገባ አመላክተዋል።

እንደ መምህር በላይ ገለጻ፤ የዓድዋ ድል የጥቁር ተሟጋቾች እንዲፈጠሩ ከማድረጉም በላይ ፓን አፍሪካኒዝም እንዲወለድ አድርጓል። በተጨማሪ ከፍተኛ የሆነ ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ይዞ የመጣ ድል ነው።

በዚህ ረገድ ምሁራንና የመገናኛ ብዙኃንም በየጊዜው አጀንዳ በመፍጠር ዓድዋ ለመላው ጥቁር ሕዝቦችና ለአፍሪካዊያን ነጻነት ያበረከተው አስተዋጽኦ ግንዛቤ መፍጠር እንዳለባቸው ምክረ-ሃሳባቸውን አቅርበዋል።

# “ኅብረ ብሔራዊ አንድነት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቢያንስ አራቱን ታላላቅ የዓድዋ ድል ዕሴቶች ለሀገር ግንባታ ልንጠቀምባቸው የግድ ይለናል ብለዋል።

ከዓድዋ ድል ዕሴቶች የመጀመሪያው ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የኢትዮጵያ ዋናው መልኳ መሆኑን ከዓድዋ ዘመቻ በተሻለ ለማሳየት የቻለ ክስተት በዘመናዊ ታሪካችን አናገኝም ሲሉ አመላክተዋል።

ዛሬ በምናውቃት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ማኅበረሰቦች መካከል ወደ ዓድዋ ያልዘመተ ወገን የለም ብሎ መናገር እውነትን መናገር ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ሁለተኛው ክስተት ደግሞ የዓድዋ ድል በተገኘ በሰባት ዓመቱ የዓድዋ በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ሲከበር ትርዒቱን ያቀረቡት ከተለያዩ የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች የመጡ የኢትዮጵያ ጦር አባላት መኖራቸውን ጠቁመው፤ በዚህ ትርዒት ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊት ሀገር መሆንዋን በአደባባይ ሰልፈኛው አሳይቶ ነበር ብለዋል።

ይሄንን በዓድዋ ዘመቻና በዓል የተንጸባረቀ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት አጽንተን ልንይዘው እንደሚገባ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ማለት ኅብረ ብሔራዊ ማንነት ያላቸው ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር ናት፤ በእያንዳንዱ ጉዞዋ ይሄንን እያረጋገጠች መጓዝ አለባት።

ሁለተኛው ዕሴት ለታላቅ ሀገራዊ ዓላማ ሲባል ንኡስ ፍላጎቶችን መሰዋት መሆኑን አንስተው፤ ወደ ዓድዋ የዘመቱ ሁሉ በወቅቱ በነበረው ሥርዓተ መንግሥት የሚስማሙና የተደሰቱ እንዳልነበሩ አስታውሰዋል።

እንኳን ዛሬ ብዙ ዓይነት መረጃ፣ ዕውቀትና የሃሳብ መንገዶች ባሉበት ዘመን ቀርቶ ከመቶ ዓመት በፊትም ሰዎች ልዩ ልዩ ፍላጎቶች እንደነበሯቸው አንስተው፤ በፍላጎቶቻቸው የተነሳም ቅራኔዎችና ግጭቶች መኖራቸውንና ሁሉንም ለአንድ ዓላማ የምታስተሳስር ዓላማ ሀገር የምትባለው ናት ሲሉ አስረድተዋል።

ዛሬም ንኡስ ፍላጎቶቻችን ከኢትዮጵያ አይበልጡም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ዛሬም የትልቁ ዓላማ የኢትዮጵያ ህልውና ማስከበሪያ እንጂ የንኡስ አካባቢያዊና ግላዊ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ሊሆን አይገባም ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳመላከቱት፤ ዘመኑ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉት ሁሉ ብዙ የመፍትሔ አማራጮችም አሉት። መከራከር፣ መነጋገር፣ መወያየት፣ በሕግ መዳኘት፣ አንዱ ሌላውን መሸከም፣ የትየለሌ አትራፊ መንገዶች አሉት።

ትልቁ ዓላማ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ስንል ንኡስ ዓላማዎቻችንን እያመሙን እንኳን ቢሆን መሰዋት አለብን ሲሉ ተናግረዋል፤

ሦስተኛው ዓድዋ ዕሴት የጦርነትን ምርቅና ፍትፍት ማወቅ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ጦርነት ምንም ያህል በአሸናፊነት ቢጠናቀቅ የሚያስከፍለው ዋጋ መኖሩን ገልጸዋል።

ጦርነት ተገድደን ብቻ ለትልቁ ዓላማ ስንል የምንገባበት የመጨረሻ አማራጭ እንጂ ከደረት ኪሳችን ቶሎ የምንመዘው አይደለም ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ እዚህም እዚያም የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በጠመንጃ ለመፍታት መነሳት የዓድዋ ዘማቾችን ኀዘን አለመጋራት መሆኑን ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስረዱት፤ አራተኛው የዓድዋ ዕሴት ትዕግሥት፣ ዝግጅት እንጂ ፍርሐት አለመሆኑን ያሳየበት ነው።

በወቅቱ ኢትዮጵያ እየተገፋች እንኳን ቢሆን ታግሳለች፤ ትዕግስቷ ግን ከዐቅመ ደካማነቷ የመጣ አይደለም ሲሉ አስረድተው፤ ለባሰው ነገር እየተዘጋጀች ስለነበር ነው፤ በመጨረሻ ግን የትዕግስቷን ውጤት በዓድዋ ተራሮች ላይ ማሳየቷን አንስተዋል።

ኢትዮጵያ ዛሬም ትታገሳለች። እየተገፋችም እንኳን ቢሆን ትታገሳለች። የምትታገሰው ስለሚያቅታት አይደለም። ለባሰው ነገር ስለምትዘጋጅ ነው። ያ የባሰው ነገር ሲመጣ የዓድዋውን ድል በብዙ እጥፍ ትደግመዋለች ብለዋል።

ዘንድሮ ዓድዋን የሚመጥን ታሪኩንም ዕሴቱንም የምናስብበት መታሰቢያ ዘመቻው በተጀመረበት ሥፍራ ባስገነባን ማግሥት ነው በዓሉን የምናከብረው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይሄም ለዘንድሮው በዓል ሞገስና ክብር እንደጨመረለት ተናግረዋል።

ዛሬ መታሰቢያውን በከበረ ሁኔታ አከናውነናል፤ ነገ ግን የዓድዋን ዕሴቶች በሚገባ በመጠቀም እንደ ዓድዋ ተራሮች የጸናች ኢትዮጵያን መገንባት ይቀረናል፤ ያ ደግሞ የሁላችንንም ስክነት፣ ብስለትና ጥምረት ይፈልጋል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የጥቁሮችን የጨለማ ዘመን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በላይ ደሳለኝ ይባላሉ። በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የታሪክና የቅርስ አስተዳደር መምህር ናቸው። የዓድዋ ድል የኢትዮጵውያን የአንድነት፣ የአሸናፊነትና የሉዓላዊነት ማረጋገጫ፤ የጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት ተምሳሌት ነው ይላሉ።

ዓድዋ ወታደራዊ ድል የተመዘገበበት ብቻ ሳይሆን ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ታሪክ በደማቁ የተጻፈበት ነው። ጀግኖች አባቶች ጣሊያንን በማንበርከክ የሀገራቸውን ሉዓላዊነት በጽኑ መሠረት ላይ አኑረዋል። ሀገራዊ ፍቅርና የስነልቦና አንድነት ለአሸናፊነታቸውና ድል አድራጊነታቸው ምክንያት ሆኗቸዋል ሲሉ ይናገራሉ።

ዓድዋ ጣሊያን ፋሽስት የተንበረከከበት ኢትዮጵያውያን ድል የተቀዳጁበት ነው። ድሉ የጥንት አባቶቻችንና እናቶቻችን የደም ዋጋ ነው። ዓድዋ ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው ኅብረትን፣ መተባበርንና ሀገራዊ አንድነትን መርህ ማድረግን አስተምሮናል።

አሁን አሁን የኢትዮጵያን የጋራ የድል ታሪክ ወደ ጎን በመተው የጎጠኝነት ዝንባሌዎች እየተፈጠሩ ነው። ወጣቶች፣ ጀግኖች አባቶችና እናቶች ለሀገራቸው ሲሉ ከፈፀሙት አኩሪ ገድል ሊማሩ ይገባል። አክራሪነት፣ ብሔርተኝነትና ጎጠኝነትን ወደ ጎን በመተው፤ ቅድመ አያቶቻችን የሠሩትን ታሪክ በማወቅ ወቅታዊ ፈተናዎችን



በላይ ደሳለኝ



መብራቱ ጌርጊሶ

በጥበብና በእውቀት ማለፍ ይገባል ይላሉ።

ትውልዱ ኢትዮጵያ በየጊዜው የሚነሱባት ጠላቶቿን እንድትመክትና ሽንፈት እንዲቀዳጁ ምክንያት የሆናቸውን ምስጢር ሊረዱ ይገባል። ይህንንም ለማስተማር የታሪክ ምሁራን፣ አርበኞችና ታላላቅ ሰዎች የታሪክ ባለአደራ ናቸው ሲሉ ይገልጻሉ።

መብራቱ ጌርጊሶም የታሪክ ምሁር ናቸው። ዓድዋ ጀግኖች ሀገራቸው በቅኝ ገዥ እንዳትያዝ ለማድረግ ከጣልያን ፋሽስት ጦር ጋር አንገት ለአንገት ተናንቀው የተዋደቁበትና የነጭን ወራሪ ድል ያደረጉበት ነው፤ በዚህም ጦርነት በርካቶች ደማቸውን አፍሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው በደማቅ ቀለም የኢትዮጵያን ታሪክ ለዓለም በሚያንፀባርቅ መልኩ ጽፈዋል ይላሉ።

ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን፣ ለአፍሪካዊያንና ለመላው ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ዓርማ ነው። ልዩነትን አስወግዶ በአንድነት ያጋመደ አንጸባራቂ የድል ማማ ነው ይላሉ።

ዓድዋ የነጮች የበላይነት በጥቁሮች የተገለጠበት ነው። ለፓን አፍሪካኒዝምና ለአፍሪካ ኅብረት መነሻነት መሠረት ጥሏል። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም አስከብሯል። ስሟንም በዓለም አደባባይ ላይ በደማቁ አጽፏል። አሜሪካን ጨምሮ በሌሎች ኃያላን ሀገራት የጥቁሮች ታሪክ እንዲዘከር አድርጓል።

በዓድዋ ድል አድራጊነት የተገኘው ከ100 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በአንድነት በመዝመታቸው ነው። እኝህ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ከአንድ ሺህ በላይ ኪሎ ሜትሮችን በእግራቸው ተጉዘዋል። በአንድነታቸው የጣሊያን ፋሽስትን አንበረከኩ። ኢትዮጵያን ብሎም አፍሪካን ከፍ አድርገዋል።

መምህሩ እንዳሉት፤ የቀደመውን የአንድነት ታሪክ በመዘንጋት ሀገሪቱ በውስጥ ችግር እንድትፈተን በርካቶች ይኳትናሉ። ስልጣንና የኢኮኖሚ የበላይነት ለመያዝ ፍላጎት ባላቸው ኃይሎች ሴራ አንድነት ላልቶ የእርስ በርስ ግጭት ተበራክቷል።

ዳሩ ግን ኢትዮጵያን የገጠማት ፈተና በዓድዋ ጦርነት ከገጠማት ችግር አይበልጥም። ወጣቶች የታሪክ ባለእዳ መሆናቸውን ተገንዝበው ሀገርን ለመታደግ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ዓድዋ የሁላችንም የድል በዓል መሆኑንም አምኖ መቀበል ግድ ይላል ነው ያሉት።

የጋራ ጠላት በጋራ ለመመከት፣ የሀገር ኢኮኖሚን በጋራ ለመገንባት፣ አንድነትን ለማጠናከር ትውልዱ ከዓድዋ አንድነትን ሊማር ይገባል ይላሉ።

የዓድዋ ድል 128 ዓመታትን አስቆጥሯል። የዘንድሮው በዓል ልዩ የሚያደርገው እንደ ድሉ ዘመን ተሻጋሪ የሆነ የዓድዋ ድል መታሰቢያ በአዲስ አበባ መገንባቱ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

# የዓድዋ አደራ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል መምህርና ተመራማሪ ፀጋዬ ዘለቀ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል ፓን አፍሪካኒዝምን አሜሪካ ውስጥ ለጀመሩት የበለጠ መነቃቃትን የፈጠረ ነው። የመጀመሪው የፓን አፍሪካ ኮንፈረንስ ተብሎ የሚጠራው በ1900 ላይ የተካሔደው እና በዊሊያም ሔነሪ ሲልቪስተር ስም ለተሰየመው ኮንፈረንስ ድሉ አንዱ ትልቅ ግብዓት ሆኗል።

የዓድዋ ድል በ1919፣ 1921፣1923 እንዲሁም በ1945ም ለተካሔዱት የፓን አፍሪካ ኮንፈረንሶች ሁሉ ትልቅ ሚና ነበረው። በኋላም ከዳያስፖራው በተጨማሪ አፍሪካ ውስጥ ያሉት እነኩዋሜ ኑኩሩማ፣ ጆሞ ኬኒያታ፣ ጁሊየስ ኔሬሬ እና ሌሎችም ተሳትፈው አፍሪካ ከአውሮፓውያን ነፃ እንድትወጣ ሲጠይቁም የዓድዋ ድል አንዱ ግብዓት ሆኗል።

የዓድዋ ድል ጥቁሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙት አንፀባራቂው ድል ነው የሚሉት የታሪክ ምሁሩ፤ ከዓድዋ ድል በፊትም ሆነ በኋላ ተመሳሳይ እና ተወዳዳሪ በዓድዋ ደረጃ ድል እንዳልተገኘ ይናገራሉ። የዓድዋ ድል ጥቁር ሕዝብ እንደሸቀጥ የሚሸጥበት እና የባሪያ ንግድ የነበረበት፤ ጥቁሮች የበታች ተደርገው አውሮፓዎች አፍሪካን ለመቀራመት የመጡበት እና አብዛኛው አፍሪካ በእነሱ እጅ ውስጥ በወደቀበት ጊዜ የተገኘ ድል በመሆኑ ጥቁሮች በነጮች ላይ ያገኙት የመጀመሪያው ድል መሆኑን ይጠቅሳሉ።

ተመራማሪው እንደሚያብራሩት፤ የዓድዋ ትሩፋት ብዙ ነው። ሀገርን ወይም ሀገረ መንግሥት በመገንባት ላይ ሚናው ከፍተኛ ነው። ሉዓላዊነትን ማስከበር ከመቻል እና መንግሥትን ከመገንባት አንፃር የተገኘው ትሩፋትም ተጠቃሽ ነው። በሌላ በኩል ዓድዋ ኢትዮጵያውያን የጋራ ትርክት እንዲኖራቸው አድርጓል።

የዓባይ ንጉሶች ሚዲያ ባለቤትና በኢትዮጵያ እውነቶች ላይ ተሟጋች የሆኑት ዑስታዝ ጀማል በሽር ዓድዋ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ብሔሮችና ብሔረሰቦች የጋራ ድል መሆኑን ይገልጻሉ። በወቅቱ በሃሳብ እንኳን የተለያዩ ሰዎች ከውጭ የመጣና የጋራ የሆነ ጠላትን ያሸነፉበትና ድል ያደረጉበት አጋጣሚ ነው። ይህ አጋጣሚ በሚከበርበት ወቅት ውስጡ ካሉት ወሳኝና የማይረሱ ጉዳዮች አንዱና ዋናው አብሮነት መሆኑንም ይናገራሉ። ጠላትን በጋራ የመመከትና በጋራ ጉዳዮች ላይ አብሮነት እንደሚያስፈልግ ማሳያ የሆነ ድል ነው ይላሉ።

ይህ ለአዲሱ ትውልድ ሌላ አደራ ይዞ የመጣ መሆኑን የሚጠቅሱት ዑስታዝ ጀማል፤ ጠላትን ከመገፍተር ውጪም በሀገሪቷ ላይ ያሉ የጋራ የሆኑ ብዙ የሚሠሩ ጉዳዮች መኖራቸውን አዲሱ ትውልድ ሊማርበት እንደሚገባ ይገልጻሉ። ልክ እንደ ዓባይ ግድብና የባህር ጉዳይ እንዲሁም ድንበር የመጠበቅና ሌሎች የጋራ ጉዳዮች ላይ በአብሮነት መቆም ለአዲሱ ትውልድ የተሰጠ አደራ መሆኑንም ያመላክታሉ።

“እንዲህ አይነት የጋራ ጉዳዮች የፖለቲካም፣ የብሔር አልያም የመንግሥት ልዩነቶች ሊያግዱን የሚገቡ አይደሉም። እነዚህን ሁሉ ተሻግረው የሚሄዱ ናቸው” በማለት ነው የሚናገሩት።

“በዓባይ ግድብ ያሰቡት ሌሎች ናቸው። የተገበሩት ሌሎች ናቸው። እያስፈጸሙ ያሉት ሌሎች ናቸው። ይህ ወደፊትም በእንዲህ መልኩ ይቀጥላል። በኢትዮጵያ መሰል ጉዳዮች በርካታ ናቸው። ዓድዋ የእነዚህ ሁሉ የጋራ ጉዳዮች ተምሳሌት ነው። ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለጥቁር ሕዝቦች እንዲሁም ለማንኛውም ነፃነትን ለሚፈልግ አካል በሙሉ ትልቅ ምሳሌ ነው” ይላሉ ዑስታዝ ጀማል።

አንድ ሰው ጎበዝ የሚባለው “አባቴ እንዲህ ነበር ስላለ ብቻ አይደለም፤ የእርሱን ጉብዝና ሊመዝኑ የሚችሉ ተግባራትን ሲያከናውን እንጂ” የሚሉት ዑስታዝ ጀማል፤ ይህ ትውልድ “ አባቶቼ እንዲህ ሠርተው ነበር” ከሚለው ትርክት ባሻገር ከአባቶች የተገኘውን ነገር ትምህርት ወስዶ የራሱን አሻራ ሊያኖር እንደሚገባ ይመክራሉ።

ዑስታዝ ጀማል እንደሚሉት፤ ምን ሠራህ ተብሎ የሠራውን ነገር በተጨባጭ የሚያሳይ ትውልድ ሊፈጠር ይገባል። “ይሄን ሠርተናል ብለና የምንናገርለት ነገርና ኮርተን ለማለፍ መጣር ያስፈልጋል።” ይህ ለአሁኑ ትውልድ ብቻ ሳይሆን ለቀጣዩም ትውልድ የሚዘከር ይሆናል። የኢትዮጵያን ከፍታና ትልቅነት ሊያሳዩ የሚችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ትውልዱ በአብሮነት የመሥራት ሀገራዊ ኃላፊነት አለበት።

በዓባይ ግድብ ዙሪያ የኢትዮጵያን እውነቶች በማሳወቅና በተለይም በአረቡ ዓለም ስለ ግድቡ የሚሞግተው መሐመድ አልአሩሲ እንደሚለው፤ የዓድዋ ድል በኢትዮጵያና በአፍሪካ መካከል ያለውን አንድነት ያጸና ነው። በወቅቱ ብዙ ልዩነቶች ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም ዜጋ ልዩነቱን ትቶ ብሔራዊ ጥቅምን በማስቀደም ለሀገር ህልውና ቆሟል። የጋራ ጉዳይ ለሆነው የሀገር ጥቅም አብሮነት ታይቶበታል። ልዩነቶች ስለ አንድነትና አብሮነት ከማሰብ አላገዳቸውም ነበር። ሁሉም ሀገሩን ከልዩነቱ በላይ አስቀምጦ ነው ጠላትን ለመፋለም የተነሳው። ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ያህል በአንድነት ላይ እንደማይደራደር ያሳየ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በየትኛውም ዘመን ለሀገር አስፈላጊ በሆኑ አጀንዳዎች ላይ ከልዩነት ይልቅ አንድነትና አብሮነትን ያስቀድማል ያለው መሐመድ አልአሩሲ፤ ምንም እንኳን መልከ ብዙ ችግሮችና ልዩነቶች ቢኖሩም ሀገር ችግር በገጠማት ጊዜ ሁሉ ከግላዊ ጥቅም ይልቅ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም የማስቀደም የቆየ ታሪክ ያለው ሕዝብ መሆኑንም ይጠቅሳል።

እንደ ቀደሙት አባቶች ሁሉ የአሁኑ ትውልድም ልዩነት ሳይበግረው ለሀገር መስዋዕትነትን መክፈል፣ ችግሮችን በጋራ መጋፈጥና የሀገር ጥቅምን ማስከበር ላይ በጋራ መሥራት እንዳለበት ይመክራል። “ይህን አደራ ሲወጣ ነው እንደ ዓድዋ ጀግኖች ታሪክ የሚዘከረው” ብሏል።

ቀደምት አባቶች ለሀገር ህልውና ተዋድቀው እንዳስከበሩን፤ ሁሉም ሀገሩ ሰላም እንድትሆን መተባበርና በአንድነት መቆም እንዳለበት፤ ኢትዮጵያ ለሁሉም ጎረቤት ሀገራት በሁሉም መስክ ተምሳሌት ሆና እንድትቀጥል አዲሱ ትውልድ የዓድዋ አደራ እንዳለበትም ገልጿል።

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# «የበጋው መብረቅ» ጃገማ ኬሎ ቀኝ እጅ ሴንሴ ኬሎ

**አስመረት ብስራት**

ጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች ማኅበር ለስራ ጉዳይ በተገኘሁበት አገጣሚ ነበር ስለ "የበጋው መብረቅ" ጃገማ ኬሎ ቀኝ እጅ ሴንሴ ኬሎ የሰማሁት። በወቅቱ የጃገማ ኬሎ ሴት ልጅ ለጉዳይ ወደ ማኅበሩ ፅህፈት ቤት ጎራ ብላ ተገናኘተን ስንጨዋወት ነበር ስላልተዘመረላት ጀግና አክስቷ ያጫወተችኝ።

በወቅቱ ወንድሟን ብላ የሞቀ ቤቷን ጥላ አምስት ዓመት ጫካ ውላና እድራ የተዋጋችውን የዚህችን ሴት ታሪክ ከማን ልሰማ እንደምችል ስጠይቅ ወይዘሮ ብርቱካን ወንድም አገኝሁ የተባሉ የወይዘሮ ሴንሴ ልጅን ላገኛቸው እንደምችል ተነጋግረን ከእሳቸው ጋር ለመገናኘት በቅተናል።

"ማን ይናገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" ነውና ነገሩ ወይዘሮ ብርቱኳን ከእናታቸው እግር ስር ተቀምጠው ሲሰሙ ያደጉትን ታሪክ በዚህ መልኩ አጫውተውናል። መልካም ቆይታ።

ወሩን በውል እንደማያውቁት የሚናገሩት ወይዘሮ ብርትኳን እናታቸው 1911 ዓ.ም በጅባትና ሜጫ አውራጃ ፣ በደንቢ ዮብዲ ወረዳ፣ ልዩ ስሙ ዮብዶ በሚባል ቦታ ከአቶ ኬሎ መወለዳቸውን ይናገራሉ። ገና በአፍላው የልጅነት እድሜያቸው እናትና አባታቸውን በሞት ያጡት የአቶ ኬሎ ልጆች እንደ ማንኛውም ወላጅ አልባ ልጅ ለማደግ ወደየዘመዶቻቸው ተበተኑ። ሴንሴ አክስቷ ጋር ስትሄድ ሕጻኑ ጃገማ ኬሎ ደግሞ አጎታቸው ጋር ይኖር ጀመር።

በሀብት እና በድሎት ያደጉት እነዚህ ልጆች ምንም እንኳን ምቹ ሁኔታ ላይ ባይሆኑም አድገው ለመገናኘት ተስፋን ሰንቀው የዛሬ መለያየታቸውን በናፍቆት እያሰቡ ይኖሩ ነበር። ሴንሴ ለአቅመ ህይዋን ሳትደርስ ገና በአስራ ሁለት ዓመት እድሜዋ ነበር ተድራ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት የሄደችው። በወለጋም የሞቀ የትዳር ህይወት እየመራች እያለች ነበር መለያየታቸው የእገር እሳት የሆነባት እህት ታናሽ ወንድሟ ጃገማ ዕድሜቸው 15 እንደሆነም ማለትም በ1928 ዓ.ም ነበር አገር በጠላት የተወረረችው።

አፍላ ወጣትነት እድሜ ላይ የነበሩት ጃገማ እንደ ሕፃን ውሃ ከመራጨት ይልቅ ጠላትን ጥይት ለመርጨት፤ እንደ ዕድሜ እኩዮቻቸው አፈር ከመፍጨት ይልቅ የጠላትን አጥንት ለመፍጨት ጨርቄን ማቄን ሳይሉ በጠላት ላይ ሸፍተው ጫካ የገቡት። ገና በአፍላ እድሜያቸው የሀገር ወዳድነት ስሜት ከውስጣቸው እየገነፈለ አላስቀምጥ ያላቸው ትንሹ ጃገማ ለታላቅ ገድል ጫካ ገቡ።

በወቅቱ የስምንት ወር ነፍሰ ጡር የነበረችው የጃገማ ኬሎ ታላቅ እህት ሴንሴ ኬሎ የወንድሟን መሸፈት ስትሰማ ባሏን ፈታ፤ የሞቀ ቤቷን ትታ፤ ወንድሟን ለማገዝ ጫካ ገባች።

አግብታ ወለጋ ጠቅላይ ግዛት ትኖር የነበረችውም ሴንሴ ወንድሟን ለመርዳት ሀብት ንብረቷን ትታ ከወለጋ ወደ ጊንጪ ለማምራት መንገድ ጀመረች። ስንቋን በጀርባዋ ልጇን በሆዷ ተሸክማ የምታመራውን ነፍሰ ጡር ሴት ጣሊያኖች ድንገት መንገድ ላይ ይይዟታል።

አልገዛም ባዩ የሀበሻ ሕዝብ ቆሽቱን ያደበነው ጣሊያን ሴት የለ ወንድ፤ ሕፃን የለ ነፍሰ ጡር ያገኘውን አቅም አልባ እያፈሰ እስር ቤት መከተትን ስራዬ ብሎ ተያይዞት ነበር። ያኔ የወንድሟ ናፍቆት የሀገር መወረር ቁጭት ሲያንገበግባት የኖረችው ይች ሴትም የጣሊያኖቹ የእስር ቤት በትር አርፎባት ለሁለት ወራት በእስር ትቆያለች። እስር ቤት እያለች ልጇን የተገላገለችው ይች ሴት በዛው እስር ቤት የአብራኳን ክፋይ ታጣለች።





የጀግና ጃገማ ኬሎ እህት ጀግናዋ ሴንሴ ኬሎ ከግርማዊና ቀዳማዊ አፄ የኃይለ ስላሴ እጅም የተለያዩ ሁለት ኒሻኖችን ተቀብለው ነበር፣

ይህን ጉዳይ የሰሙት አጎቷ ከጣሊያኖቹ ጋር መልዕክት በመላላክ እንድትፈታ ያድርጓታል።

ቁጭት ቁጭትን እየወለደ ከወንድሟ ናፍቆት፤ የሀገር መደፈር ቁጭት፤ የአብራኳን ክፋይ በእስር ቤት ማጣቷ ተደራርቦ ፍም ያቀፈች አርበኛ ሊያደርጋት ሴንሴ ኬሎ እልህ ከውስጧ እንደ ቋያ እሳት እየተንተገተገ ነበር ወንድሟ የሚመራው የጦር ሰፈር የደረሰችው።

የጀግንነት ደም ውስጣቸው የሚንተከተከው የዚህ ቤተሰብ አባላት፤ ማለትም ሻለቃ ፈንጌሳ ኬሎ፤ ሻንበል ጊዴ ኪሎና ትንሹ የአባ ኬሎ ወንድ ልጅ ጃገማ ኬሎ በአንድ ሆነው ጣሊያንን ሲያርበደብዱ አገኘቻቸው። ይች ሴት ወትሮም መለየያታቸው እንጂ በአንድነት ታሪክ ሰሪ መሆናቸውን ታውቅ ስለ ነበር የራሷን መቶ ሰዎች በማደራጀት ግልጋሎቷን በስፋት መስጠት ጀመረች።

በወቅቱ የጃገማ ኬሎን ወኔ ገና ከጅምሩ የተረዱ ወጣቶችም የእርሳቸውን እግር ተከትለው "እምቢ ለአገሬ" እያሉ በጠላት ላይ ሳያንገራግሩ ሸፈቱ። በዚህም ሳቢያ ጃገማ ኬሎ ገና በአፍላ ዕድሜቸው የ3ሺ500 አርበኞች አለቃ ለመሆን ችለው ነበር።

ያን ጊዜ በምዕራብ ሸዋ የነበረውን የፋሽስት ጦር መግቢያ መውጫ በማሳጣትና ሰቅዞ በመያዝም "የበጋው መብረቅ" የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ። አምስት ዓመታትን በፈጀው ጦርነትም በታላላቅ አውደ ውጊያዎች ላይ ጦራቸውን ሰብቀው የተካፈሉት "ጃገማ ዘአንበሳ" ከማሸነፍ በቀር ለአንዴም ቢሆን ሽንፈትን አያውቋትም ነበር።

ጠላትን ድል ነስተው የጠላት ግምጃ ቤት ሰብረው አርበኞችን ባስታጠቁ ቁጥርም እንዲህ ይወደሱ ነበር።

"ገዳይ በልጅነቱ
ዶቃ ሳይወጣ ባንገቱ
ጃጌ ጃገማቸው
እንደ ገጠመ የሚፈጃቸው
አባት እናቱ ከኦሮሞ
ግዳዩን አስቆጠረ ከምሮ ከምሮ" ተብሎ ተገጥሞላቸው ነበር፡፡

ሴንሴ የጃገማን ኬሎ ፀጉር በመስራት፤ ምግብ በማቅረብ አንድም ቀን እንኳን ከጎናቸው ባለመለየት የተሳካና በድል የታጀበ ጦርነት እንዲያካሂዱ አድርጋቸው ነበር።

ስንቁን በአይነት በአይነት በማደራጀት፤ ከጦርነቱ ፈርቶ ሊመለስ ያለውን አርበኛ በሙሉ መሳሪያ በመያዝ "እኔ ሴቷ ዘምቼ ሀገር ስትጠፋ ወዴት ትመለሳለህ ?" በማለት በማደፋፈር ሰራዊቱ ሳይበተን በወኔ እንዲዋጋ የጃገማ ኬሎ ቀኝ እጅ በመሆን ስታገለግል ቆይታለች።

የጃገማ ኬሎ ሰራዊት ከሸዋ እስከ ጅማ በመዝመት ጠላት ባዩ ቁጥር ግዳይ እንዳዩ ነብር ወደ ጠላት እየተወረወሩ ጠላትን አስጨንቀዋል። እጅግ አደገኛ የሆኑ የፋሽስት ምሽጎች ሰባብረዋል። በዚህ ወቅትም የሚወድቁ ቁስለኞችን በማንሳት የማከም ስራ፤ ውሃ ለጠማው ውሃ ማጠጣት ድካም ለተሰማው ብርታት መሆን የሴንሴ ኬሎ ተግባር ነበር።

ሴንሴ ወንድሟ እንዳይሞትባት መጠበቁ ታላቁ ኃላፊነቷ ነበር፡፡ ከባድ ወጊያ ተካሄዶ ጦሩ ተበታትኖ እስኪሰበሰብ ድረስ መሳሪያ በመያዝ ከወንድሟ ጋር ጠላትን የምትመክተው እሷ እንደነበረች ይናገራሉ።

ጃገማ ኬሎ ከእነ ደጃች ገረሱ ዱኪ ጋር በመሆን በምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ አርበኞችን እስከ መጨረሻው ማለትም እስከ 1933 ዓ.ም በመምራት፣ በማስተባበርና ተዋግቶ በማዋጋት ጣሊያንን ቁም ስቅል ነስተው ከኢትዮጵያ ምድር የውርደት ካባ አጎናፅፈው ወደ መጣበት ሸኝተዋል። የእሳቸው ጀግንነት ሲነሳ አንድም ቀን ከአጠገባቸው ያልተለየቻቸው የታላቅ እህታቸው የወይዘሮ ሴንሴ ኬሎ ታሪክም መዘንጋት አይኖርበትም።

ጃገማ ኬሎ ከድል በኋላም በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ምክር ዘመናዊ የጦር ትምህርትን በሆለታ የጦር ትምህርት ቤት እንዲሁም አሜሪካን አገር ድረስ ተጉዘው የተማሩ ሲሆን ወደ አገራቸውም በመመለስ ዕልፎችን ዘመናዊ የጦር ትምህርት ስያስተምሩ ሴንሴ ትዳር በመያዝ ቤተሰብ መስርታ ልጆችን አፍርታለች።

ጃገማ ከግርማዊና ቀዳማዊ አፄ የኃይለ ስላሴ እጅም የሌፍተናንት ጀነራልነትን ማዕረግን የተቀበሉ ሲሆን በንጉስ ነገስቱም የስምንቱ ጠቅላይ ግዛቶች የሰራዊት ኃላፊ እንዲሆኑ ሲሾሙ ሴንሴ ለወንድማ የነበራት ከባድ ፍቅር ቤቷን አስትቶ እያስኮበለለ ወንድሟ ጋር ሲወስዳት ትዳሩ በፍቺ ይጠናቀቃል። ያኔ ወደ ትውልድ ቀየዋ ጊንጪ በመሄድ እርሻ ታሳርስ እንደነበረ የወይዘሮ ሴንሴ ልጅ ተናግረዋል።

ወይዘሮ ብርትኳን እንደሚሉት ከጀነራል ጃገማ ኬሎ ታሪክ ውስጥ የሚደንቀኝ የማረኩትን ነጭ የጣሊያን ወታደር መቶ ብር ሸጠዋል። ከእሳቸው መቶ ብር የገዛው ደግሞ ጣሊያኑን 5000 ብር ሸጦታል። ባርነት በቆዳ ቀለም መጥቆር የተነሳ የሚጫን ቀንበር አለመሆኑን ለምዕራባውያኑ ከማስገንዘብ በተጨማሪ አውሮፓውያን ጥቁሮች ላይ የፈፀሙትን በደል በተራቸው በጥቂቱም ቢሆን እየጎመዘዛቸው እንዲቀምሱት ማድረግ የቻሉበት ነው።

ወይዘሮ ብርትኳን እንደሚሉት የጀግና ጃገማ ኬሎ እህት ጀግናዋ ሴንሴ ኬሎ ከግርማዊና ቀዳማዊ አፄ የኃይለ ስላሴ እጅም የተለያዩ ሁለት ኒሻኖችን ተቀብለው ነበር።

ከጦርነት መልስ በትዳር መኖር ያልሆነላቸው ቀሚስ መልበስ የማያውቁት ሴንሴ ኬሎ በሬ ጠምደው በማረስ ልጆቻቸውን ያሳድጉ የነበረ ሲሆን ሰው መርዳት ለተቸገረ መድረስ ተቀዳሚ ተግባራቸው መሆኑን ልጃቸው ይናገራሉ።

ጀነራል ጀጋማ ኬሎም በዛ በልጅነታቸው ወቅት እንደ እናት ተንከባክበው ላቀይዋቸው እህታቸው ውለታ ምላሽ ለጆቻቸውን እየወሰዱ ያሳደጉላቸው እንደነበር የሚናገሩት ወይዘሮ ብርትከዋን እሳቸውና ወንድማቸውም በአጎታቸው በጀነራል ጃገማ ኬሎ እጅ ማደጋቸውን ያስታውሳሉ።

ዓመታትን ለሀገራቸው ዋጋ የከፈሉ ከሞት ጋር ተናንቀው ነፃነቷን አስጠብቀው የቆዩቱ እናት አርበኛ ሴንሴ ኬሎ ከዚህ ዓለም በሞት እስከሚለዩ ድረስ የራሳቸው መኖሪያ ቤት እንኳን ያልነበራቸው እንደሆኑ ልጃቸው ይናገራሉ።

ትናንትናችንን ስናስታውስ በደማቁ የደም ዋጋ የከፈሉ ለነፃነታችን አንገታቸውን ለሰይፍ ደረታቸውን ለጥይት የሰጡ ጀግኖቻችንን የሚጋባውን ክብር መስጠት ይገባናል ባይ ነኝ። እንደማንም ተራ እቃ በየቦታው ወደቀው የምናያቸው በአንድ ወቅት ለሀገር ባለውለታ የነበሩ አርበኞችና ቤተሰቦቻቸው የት ናቸው ብሎ መመልከት ተገቢ ነው እላለሁ።

ኋላው ከሌለ የለም የፊቱ ነውና ነገሩ ትናንትን እያከበርን ዛሬ የሚጠበቅብን የወቅቱን የአርበኝነት ተግባር እናከናውን በሚል መልእክት ልሰናበታችሁ ወደድኩ። ቸር ይግጠመን።

# ‹‹ትውልድ የገጠመውን የሥነ-ልቦና ወረራ የሀገሩን ታሪክ በማወቅ ሊወጣው ይችላል ››

**- ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ እርገጤ**
**የፊትአውራሪ ተሰማ እርገጤ ልጅ**

ሰሚራ በርሀ እና መክሊት ወንደሰን

ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ እርገጤ ይባላሉ። በጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር በታሪክ ኃላፊነት እና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ለሰባት ዓመታት ያህል በኃላፊነት አገልግለዋል። በአሁን ሰዓት ደግሞ የኢትዮጵያን የጀግንነት እና የአርበኝነት ታሪክ ከሚያጠኑ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የጥናት ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ ።

የዛሬው እንግዳችን ልጅ ጀርሚያስ ተሰማ እርገጤ የቤተሰቦቻቸውን ታሪክ በዓድዋ ታሪክ ለእሳቸው ያለውን ትርጉም እና ወጣት ትውልድ እንዴት አድርጎ የሀገሩን ሉዓላዊነት መጠበቅ ይገባዋል። በሚሉ ጉዳዮች ላይ ሀሳባቸውን አካፍለውናል ።

**አዲስ ዘመን ፡- የአርበኛ ልጅ እንደመሆንዎ ወደኋላ ተመልሰው የአባትዎን እና የአያትዎን የአርበኝነት ታሪክ ቢነግሩን?**

**ልጅ ጀርሚያስ፡-** ወደኋላ መለስ ለማለት የደጅአዝማች ተሰማ እርገጤ አባት ባሻ እርገጤ በዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት የግቢው መቶ አለቃ ነበሩ። የጣሊያንን ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን ለመውረር እና ቅኝ ግዛት ለማድረግ ጦር አሰናድቶ ሲመጣ ከዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በተላለፈው የክተት አዋጅ በታላቁ የዓድዋ ጦርነት ሲዘምቱ የእሳቸው ልጅ የሆኑት የእኔ አባት ስመጥር ቀዳሚ ጀግና ፊታውራሪ ተሰማ እርገጤ በጊዜው ወጣት መኮንን ሆነው በዘመኑ የነበረው ‹‹የጎምላ ደም›› ለየት ያለ የጦር ቡድን ውስጥ መቶ አለቃ ሆነው በቤተመንግሥት ውስጥ አገልግለዋል ።

ሽንፈቱን ያላመነው የጣሊያን ጦር በናቀው የጥቁር ሕዝብ በመሸነፉ ከ40 ዓመታት ያክል ጊዜ ሲሰናዳበት እና ለበቀል ሲዘጋጅ ቆይቶ ተመልሶ ለወረራ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ አባቴ ደጅአዝማች ተሰማ እርገጤ በማይጨው ጦርነት ከወንድማቸው እስጢፋኖስ እርገጤ እና ጓደኞቻቸው ጋር ሆነው ዘምተዋል። በማይጨው ሰፍሮ የነበረው የጣሊያን ጦር ውጊያ በሚያደርግበት ሰዓት በኢትዮጵያውያን አርበኞች እና ተዋጊዎች ሽንፈት እየገጠመው መሆኑን የተረዳው የጣሊያን ጦር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከለከለውን መርዛማ ኬሚካል በመጠቀም ወደ መሐል አገር መንቀሳቀስ በጀመረበት ወቅት የእኔ አባት ከማይጨው ወደ አዲስአበባ በሚወስደው መንገድ ላይ ጣሊያን አልፎ እንዳይገባ የቻሉትን እንዲያደርጉ፣ ሕዝቡ በቻለው አቅም እንዲከላከል የቀሰቅሱ ነበር።

የአካባቢው ሕዝብም አባቴን የጎበዝ አለቃ አድርገው መረጧቸው። እሳቸውም ‹‹እኔን ከመረጣችሁን እንግዲያውስ እኔ የምላችሁን አድርጉ›› ብለው ሕዝቡን ጠንባበር ዋሻ ከሚባለው ስፍራ ጭራሜዳ ( አይገብር፣ ትርጉሙም ለጠላት አንገብርም ማለት ነው) እስከ ሸዋሮቢት ድረስ ያለውን ስፍራ ሕዝቡ ያለውን መጥረቢያ ያለው መጥረቢያ ጎራዴ ያለው ጎራዴውን ይዞ እንዲሰለፍ አድርገዋል ።

የጄኔራል ባዶሊዮ ጦር በማይጨው ጊዜያዊ ድል አግኝቶ ወደ መሐል ሀገር እየገሰገሰ በቦታው ሲደርሱ የገጠሙት ሲሆን፣ በጦርነቱም 75 ካሚዎን (የጭነት ወታደር) የነጭ ወታደር ተመትቷል። ከዛም በኋላ የጣሊያን ጦርም ወደ አዲስአበባ እንዳይገባ በየደረሱበት መንገድ በመዝጋት የተቻላቸውን አድርገዋል፣ ለዚህም ከአጼ ኃይለሥላሴ ምስጋና ተችሯቸዋል ።

ሽንፈት እየገጠመው መሆኑን የተረዳው ጣሊያን የአየር ላይ ድብደባ ማድረግ ሲጀምር እሳቸውም ሕዝቤን መጨረስህን የማትተው ከሆነ ብለው በምርኮ የያዟቸውን ወታደሮች ላይ እርምጃ በመውሰድ አሳይተዋል። በዚህም ‹‹የጥቁር ጭቃው ተሰማ እርገጤ ነጩን አረደው እንደወጠጤ›› ተብሎ ተገጥሞላቸዋል። በኋላም ጦርነቱ ካበቃ እና ከተረጋጋ በኋላ ንጉሡ ጣሊያኖች ደርሰው እኛን እንዳይዙን መንገድ የዘጋልን ባለውለታ ነው ብለው አመስግነዋቸዋል።


ፎቶ- በረሁ ታደሰ

ተሰማ እርገጤ የተሰማቸውን ነገር በቀጥታ ፊት ፊት በመናገርም ይታወቃሉ። ከአምስት ዓመት በቆየው ውጊያ ላይም ዘጠኝ ቦታ ቆስለዋል፤ በፍጹም ጀግንነት ተዋግተዋል ወንድማቸው እስጢፋኖስ ተሰማ እርገጤም በጀግንነት አልፈዋል። ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ነፃነቷን ታግኝ እንጂ በጎንደር የነበረው የጣሊያን ጦር ምሽግ መሽጎ አልወጣም ነበር እና ከመሐል ሀገር ኃይል ያላቸው አርበኞች እንዲሄዱ ሲታዘዝ ተሰማ እርገጤ በፊታውራሪነት ማዕረግ ሦስት ሺህ በላይ ጦር ይዘው በጎንደር ከሚገኙ ተዋጊዎች ጋር በመመካከር በሦስት ምሽጎች የተቀመጠው የጣሊያን ጦር ምሽጉን ዙሪያውን በቦምብ በማጠሩ ሕዝብ እንዳይጨርስ ከበባ ካደረጉ በኋላ ኢትዮጵያን ሊያግዝ የገባው የእንግሊዝ ጦር ጋር በመሆን ተዋግተዋል ። የጣሊያኑ የጦር መሪም እጄን ለጥቁር አልሰጥም ብሎ እጁን ለእንግሊዞች ሰጠ ።

ፊትአውራሪ ተሰማ እርገጤም የማረኩት መሣሪያ የጀርመን ስሪት ነውና እንግሊዞች መሣሪያውን ለማግኘት ቋምጠዋል ነገር ግን ተሰማ እርገጤ እሱም ከነጭ የማረኩትን ለነጭ አልሰጠም ብለው ለመስጠት ፍቃደኛ አልነበሩም ። በዚህም ምክንያት የጣሊያን ጦር ሊገድላቸው ሰው አሰማርቶባቸው ነበር ። ፊታውራሪ ከመሣሪያው ባሻገር 80 ሺህ በርሜል የጣሊያን ነዳጅ ማርከዋል።

**አዲስ ዘመን ፡- የአርበኛ ልጅ የልጅነት ጊዜው ምን ይመስላል እርስዎስ ከዚህ ታሪክ ምን ተማሩ ?**

**ልጅ ጀርሚያስ፡-** እኔ ለቤተሰባችን አራተኛ ልጅ ነኝ /በአጠቃላይ ሰባት ልጆች ነን/ ከልጅነቴ ጀምሬ ሳዳምጥ አባታችን በባንዳዎች ምክንያት ተገፍተው መተዳደርያ አጥተው በቤታቸው አዝነው የተቀመጡ አርበኞችን በቤታችን አስቀምጠው ይጦሩ ነበር። ከታላቆቼ ጋር ሆነን እነሱ ስር ታሪክ እየሰማን ነው ያደግነው።

አባታችንም በልጅነታችን ውጭ ሀገር ሊልኩንም ፍላጎት አልነበራቸውም። በእረፍት ሰዓታችን ወደ ክፍለሀገር በመሄድ አደን እንድናድን፣ ዒላማ እንድተኩስ ያደርጉን ነበር። በዘጠኝ ዓመቴ ከወንድሜ ጋር ዒላማ ስለማመድ ወንድሜ በጥይት መትቶኝ በንጉሡ እና በአልጋወራሹ አማካኝነት ወደ ውጭ ሀገር ሄጄ እንድታከም ቢሞከርም አባቴ ግን ጣሊያኖች በእጅ አዙር ልጄን ይገሉብኛል ብለው ከልክለዋል። አባቴ በጣም ጠንቃቃ እና የሀገራችንን ታሪክ የምናውቅ ተጋዳይ፣ ጨዋና ሥነ-ምግባር ያለው አድርገው አሳድገውናል ።

ታላቅ የሆነችውን የኢትዮጵያን ታሪክ ነው እየሰማን ያደግነው። ጀግናና አርበኛ ሀብት የለውም ምክንያቱም ባንዳዎቹ ገንዘብ ላይ እና ጥቅማቸው ላይ ሲያሯሯጡ እነሱ ግን ሀገርና ሕዝብን ለማዳን ስለነበረ ዓላማቸው የነበራቸው ቤት እንኳን እየተቃጠለ ነበር ወደ ጦርሜዳ የሚዘምቱት። የሚያሳዝነው ለሀገር ውለታ የሠሩ፣ ሀገርን አላስገዛም ያሉ ጀግኖች የሚገባቸውን ክብር እና ምስጋና ሳያገኙ እንክብካቤ ሳይደረግላቸው አልፈዋል ።

የዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ያሉ የጥቁር ሕዝቦችን ጭምር አንገት ቀና ያደረገ የጣሊያን ጦር በገጠመው ሽንፈት ሳቢያ ራሳቸው ጣሊያኖች ( ቪቫ ሚኒልክ ቪቫ ጣይቱ) በማለት እንዲመሰክሩ አድርጓቸዋል። በዚህም ኢትዮጵያውያን የጥቁር ሕዝቦችን ነፃነት በማወጅ ኢትዮጵያ ፋና ወጊ ፈር ቀዳጅ ሀገር አድርገዋታል ።

**አዲስ ዘመን ፡- ዛሬ ላይ ያለፉ ታሪኮቻችን የግጭት መንስኤ ሲሆኑ ይስተዋላል። ይህ ከምን የመነጨ ነው ?**

**ልጅ ጀርሚያስ** ፡- ወደኋላ ነገሩን ስንመለከተው የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩትም በጥናት ደረጃ ሰፊ ነው። ኢትዮጵያ ኃያል ሀገር እና ኃያላን መንግሥታት የነበሯት መሆኑ ዳግም በዓድዋ ጦርነት ላይ እስከአፍንጫው ድረስ ታጥቆ የመጣውን ወራሪ ሠራዊት በመዋጋት ዳግም አሳይተዋል። ከዛ በኋላም ቢሆን የኢትዮጵያ ዘመናዊ ጦር የሠላም አስከባሪ ኃይል በመባል በዓለም ላይ የታወቀ ጠንካራ ሠራዊት የገነባች ሀገር ሆና በኮሪያ፣ ኮንጎ ላይ በመዝመት ጀግንነታቸውን እና ወዳጅነታቸውን አሳይተዋል።

በዚህን ጊዜ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ገና ከቅኝ ግዛት ባልወጡበት ወቅት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረት አድርጋለች። ይህም በሌሎች ሀገራት በስጋት እንድትታይ አድርጓታል። የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመሥረት ላይ ኢትዮጵያ ያበረከተችው አስተዋፅዖ ላቅ ያለ ነው ። በኋላም የአፍሪካ ኅብረት ጽሕፈት ቤት መቀመጫው በኢትዮጵያ እንዲሆን በሚሞግቱበት ወቅት ኢትዮጵያን መሪዎች ልዩነቶቻቸውን ወደ ጎን ትተው በመሪነት ጊዜያቸው አንድ የሆኑበት ነው ።

ኃያላን የሚባሉ ሀገራት ደግሞ ይህች ሀገር ወደፊት ያላትን ሀብት የመጠቀም ደረጃ ላይ ስትደርስ የምታሰጋ ትሆናለች በማለት የኢትዮጵያን ታሪክ የሚያነሱ አብዛኛው የታሪክ መዛግብትና መጽሐፎቻችን በሌሎች ሀገራት ዜጎች እና ጸሐፊያን የተጻፉ ናቸው። እነዚህ ታሪኮችም በጥቅሉ የኢትዮጵያን ታላቅነት የሚያረጋግጡ አንዳንድ ታሪኮችን በታማኝነት እንደማይጽፏቸው ይገልጻሉ።

ከመደበቅም ባሻገር የሌሎች ጀግኖችን ታሪክ የራሳቸው አስመስለው ይጽፋሉ። በመሆኑም ወደሀገራችን ስንመጣ የዓድዋ ታሪክን ጨምሮ ከዓድዋ በኋላ ያሉ ታሪኮቻችን ራሱ በአግባቡ አልተጻፉም አልተመዘገቡም። ፈረንጆቹ የእኛን ታሪክ ጠንቅቀው ያውቁታል፣ ይገረሙበታል ለኛ ሲነግሩን ግን አሳንሰው ያቀርቡታል ።

ኢትዮጵያ ያላትን ጥንካሬ ሰብረው መግባት ያልቻሉት ጠላቶቿ እንደ አማራጭ የተጠቀሙት የተለያዩ አካላትን እና መልዕክተኞችን ከሀገር ውስጥ አንዳንድ ባንዳዎች ጋር በመመሳጠር ያላትን ሰፊ የሆነ ሕዝብ ቁጥር የባሕል፣ የቋንቋ፣ ልዩነት ተጠቅመው የእርስ በርስ ግጭት፣ መከፋፈል እንዲኖር ማድረግ ነበር። ለዚህም የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሟል። የጎሳ እና የዘር ልዩነት እንዲሰፍን ተደርጎ አንዱ ባንዱ ላይ እየተተቻቸ ኢትዮጵያን ወደኋላ ለመመለስ ብዙ ተሠርቷል ለዚህም ቢሆን ኢትዮጵያን ይህንን በመመከት አንድነታቸውን በተለያየ ጊዜ አሳይተዋል ።

በአሁን ሰዓትም ዋልታ ረገጥ ያልሆነ ጽንፈኛ ያልሆነ ወደ አንዱ ያላደላ ጥናት የሚያደርጉ ታሪክ ጸሐፊዎች ተሰባስበው ጥናት ቢደረግ እና ታሪካችን በኛው ቢጻፍ ጥሩ ነው። በተጨማሪም በዚህ የአርበኝነት ታሪክ ውስጥ ያለፉ ጀግኖች ባለታሪኮች ታሪክን ባለመደበቅ መጋራት ይኖርባቸዋል። ያልተዘመረላቸው ያልተነገረላቸው ጀግኖችን እንዲሁ ፈልጎ ማግኘት ላይም ሊሠራ ይገባል፣ ለዚህም የሚዲያ አካላት ድርሻቸውን መወጣት ይገባቸዋል ።

**አዲስ ዘመን ፡- ወጣቱ ትውልድ የአያት የአባቶቹን ታሪክ በምን መድገም አለበት፤ የሀገሩን ሉዓላዊነት በምን መልኩ አስጠብቆ ይቆይ ይላሉ ?**

**ልጅ ጀርሚያስ** ፡- አንኳር ጉዳዮችን ብናነሳ የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያ በኃይልና በጦርነት የማትቻል ሀገር መሆኗ በተጨባጭ ታይቷል። ሁለተኛ ሕዝቦቿን በዘር በሃይማኖት በመከፋፈል የተደረገ ጥረት ነው አልተሳካም ። አሁን እየሆነ ያለው ሀገሪቱ በውስጧ ያሉ ባሕል፣ እምነት እና የሞራል እሴቶችን፤ ያልተጻፉ ሰውን ሰው የሚያሰኙ ማንነት ያላቸው የሥነ-ምግባር ሕጎች፣ ታማኝነት እና እውነትን ከትውልዱ ልብ እና አዕምሮ ላይ በመፋቅ በቋንቋው፣ እና በራሱ ማንነት የማይኮራ ግፋ ሲልም ሀገሩን የማያውቅ ትውልድ ለመፍጠር ነው ።

ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ራስን ለመቻል በምታደርገው ጉዞ ሌሎች ያደጉ ሀገራት ያላቸውን የኢኮኖሚ እድገት ተጠቅመው በማማለል ዜጎቻችን ስደትን አማራጭ እያደረጉ ከራሳቸው እና ከሀገራቸው እየራቁ እንዲሄዱ ነው፤ ማንነታቸውን እንዲረሱ ማድረግ ነው ።

እነዚህን ተግዳሮቶች ለመሻገር ሀገር ተረካቢው ወጣቱ ትውልድ ወደኋላ ተመልሶ የሀገሩን ታሪክ ኢትዮጵያ ምን ያህል ታላቅ ሀገር እንደነበረች እና እንደ ሆነች፤ የአባት የአያቶቻቸውን ታሪክ ማጥናት እና ማወቅ ይኖርበታል። በተለያዩ አጋጣሚዎች/መድረኮች የሚፈጠሩ የልዩነት ምንጭ የሆኑ አጀንዳዎችን በሰከነ መንፈስ የመልካም ሀሳብ ምንጭ ለማድረግ መሥራት አለበት።

ሌላኛው ይህ ትውልድ በቋንቋው በአለባበሱ የሥነ-ልቦና ወረራ ተደርጎበታል። የራሳቸውን ቱባ ባሕል ተጠቅመው የራሳቸውን ፈጠራ በማከል በማዘመን እንጂ ጨርሶ መጣል እና የሌላ ሀገር ባሕል ተከታይ መሆን የለበትም ። የሀገራቸውን ቋንቋ በእኩል ዓይን ተመልክተው ጥንቅቅ አድርገው ማወቅ፤ የሌላውንም ዓለም ቋንቋ ማወቅ እንጂ አደባልቀው እና አፋልሰው መናገር የለባቸው። ታሪካቸውን ካወቁ እና እርስ በእርሳቸው መተባበር ከቻሉ የዚህን ዘመን እየተካሄደብን ያለውን የሥነ-ልቦና ወረራ መመከት እንችላለን ።

**አዲስ ዘመን ፡- አመሰግናለሁ**

**ልጅ ጀርሚያስ** ፡- እኔም አመሰግናለሁ

# ዓድዋን ያነበሩ እና ያደመቁ ጥበባት

ዋስልኝ አየለ

ኪነ ጥበብ የገሃዱ ዓለም ነፀብራቅ ነው ከመሆኑ አንጻር የአንዲት አገር ሕዝብ የኪነ-ጥበብ ሥራዎች የዛችን አገር ምንነት ገላጭ ናቸው ፡፡ ሃያል የሚባሉ አገራት ገናናነትን ያገኙት በአብዛኛው በኪነ ጥበብ ስራዎቻቸው ራሳቸውን መግለጥ በመቻላቸው ነው ፡፡ ለምሳሌ አሜሪካና ህንድን የምናደንቃቸው፤ አሜሪካም ወይም ህንድ ሄደን አይደለም፤ የአገራቸውን ባሕልና ታሪክ በመኖር አውቀነው አይደለም፤ በኪነ ጥበብ ሥራዎቻቸው (በተለይም በፊልሞቻቸው) ነው፡፡

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፤ አብዛኛው ማኅበራዊ መስተጋብሮቻችን በኪነ ጥበብ ይገለጻሉ፤ ዘፈኑ፣ እንጉርጉሮው፣ ፉከራው፣ ቀረርቶው ..ወዘተ የዚሁ እውነታ መገለጫ ናቸው፡፡ ለዛሬው ግን የአድዋ 128 ዓመት በዓልን በማስመልከት እለቱን በሚመለከቱ የጥበብ ሥራዎች ለማየት እሞክራለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ የኖረች አገር መሆኗን ዓለም ያውቃል፡፡ ከእነዚህ የጀግንነት መገለጫዎቿ አንዱ ደግሞ የዓድዋ ድል ነው። በርግጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ጀግንነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ ከመጡ የስነ ቃል ትውፊቶች መረዳት እንችላለን፡፡ ይህ ከዓድዋ በፊትም ሆነ ከዓድዋ በኋላ የነበረና ያለ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ነው፡፡

የዓድዋን ድል የተመለከቱ በርካታ የኪነ ጥበብ ሥራዎች አሉ፡፡ የመድረክ ቴአትሮች፤ ፊልሞች አሉ፡፡ በአብዛኛው ግን የቃል ግጥሞችና የመድብል ግጥሞች ናቸው። እነዚህ ዓድዋን የተመለከቱ የኪነ ጥበብ ሥራዎች በዓድዋ ጦርነት ወቅትና ከጦርነቱ በኋላ ኩራትን ለመግለጽ የተሰነኙ ናቸው፡፡

አንዳንዶቹ በጦርነቱ ወቅት የጦርነቱ ተሳታፊዎች የገጠሟቸው ናቸው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ በዚያው በጦርነቱ ወቅት ሕዝቡ አርበኞችን ለማበረታታትና የደስታ ስሜቱን ለመግለጽ የገጠማቸው ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ ታዋቂ ድምጻውያን የዓድዋን ድል ለማወደስ የዘፈኗቸው ናቸው፡፡ በወቅቱ ከነበሩት እንጀምር፡፡

አንዳንዶቹ በቅኔ የሚነገሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ አንዱ ቅኔ እንዲህ የሚል ነበር፡፡

**እስኪ ስጣሊያኖች መዲሃኒት ስጧቸው**
**የሚያስቀምጥ ሳይሆን የሚያስመልሳቸው**

የዚህን ግጥም ትርጉም በወቅቱ ዓውድ እንረዳው፡፡ ዘመናዊ ሕክምና ባልነበረበት በዚያ ዘመን ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉት ከቅጠላ ቅጠልና ሥራ ሥር የሚዘጋጁት የባሕል መዲሃኒቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መድሃኒቶች ሕመምን የሚፈውሱት ወደታች (በዓይነ ምድር መልክ ማለት ነው) እና ወደላይ (በማስመለስ) ነው፡፡

የዚህ ግጥም ሰም ጣሊያኖች ታመዋልና መድሃኒት ስጧቸው ነው፡፡ መድሃኒቱ ግን በመቀመጥ (በዓይነ ምድር ማለት ነው) ሳይሆን በማስመለስ (በአፍ) የሚፈውስ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ዋናው ትርጉም ያለው ግን ወርቁ ላይ ነው፡፡

ጣሊያኖች ታመዋል፡፡ ጤነኛ ቢሆኑ ኖሮ እንደ ኢትዮጵያውያን አይነት ጀግና ሕዝብ እንወራለን ብለው አያስቡትም ነበር፡፡ የእነዚህ ሰዎች መድሃኒት ቅጠላ ቅጠልና ሥራ ሥር ሳይሆን፣ ጎራዴና ጥይት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀመጡ ሳይሆን በመጡበት እግራቸው ወደ አገራቸው የሚመልስ መሆን አለበት የሚል ነው።

ጣሊያን ኢትዮጵያን ለመውረር ያሻትን በመኪና ያሻትን በፈረስ እየሄደች ነበር። የጣሊያን ወታደሮችም ሰውነታቸው ከኢትዮጵያ ተዋጊዎች ጋር ሲነጻጸር የለሰለሰና ያማረባቸው ናቸው፡፡ ዳሩ ግን ምን ዋጋ አለው እንዲህ ሆነ!

**የሞሶሎኒ አሽከሮች ሁሉም ሎጋ ሎጋ**
**ሲመጡ በፈረስ ሲመለሱ በአልጋ**

እንግዲህ በፈረስ ሲንሸራሸር የነበረ ሸበላ የጣሊያን ጦረኛ ፈረሱን መቀማቱ ሳያንስ በእግሩ እንኳን እንዳይሄድ በጥይት አንካሳ አደረጉት ማለት ነው፡፡ የሞተው ሞቶ የቆሰለውም በአልጋ እንዲወሰድ ተደረገ ማለት ነው፡፡ ይህ ስንኝ ግን ለዓድዋ ሳይሆን ለአምስት ዓመቱ የጣሊያን የወረራ ሙከራ የተፎከረ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ሞሶሎኒ የጣሊያን መሪ የሆነው ከዓድዋ ድል 27 ዓመታት በኋላ በ1915 ዓ.ም (እ.አ.አ 1922) ነው፡፡

የዓድዋ ድል አስገራሚ ታሪክ የሆነው ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ያላት ጣሊያን «ኋላ ቀር» እያሉ በሚሳለቁባት ኢትዮጵያ መሸነፏ ነው፡፡ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ ወታደር ባኅላዊ ጎራዴና ጋሻ በያዘ ወታደር መማረኩ ነው፡፡ ጣሊያን በራሱ መሳሪያ መወጋቱ ነው። ራሱ ይዞት በመጣው መሳሪያ ተገደለ፡፡ ለዚህም ነው የወቅቱ ከያኒያን እንዲህ ያሉት፡፡

**በሰራው ወጨፎ ባመጣው እርሳስ**
**ተፈፀመ ጣሊያን ሐበሻ እንዳይደርስ**

በዓድዋ ጦርነት ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ጀግኖች ተወድሰዋል፡፡ እነዚህን ጀግኖች በማወደስ ለሌሎች ጀግኖች ተጨማሪ ሞራል መስጠት ተችሏል፡፡ ከእነዚህም አንዱ ራስ አሉላ አባ ነጋ ናቸው፡፡ ራስ አሉላ አባ ነጋ በርካታ የጦር ገድል ነው ያላቸው፡፡ በኩፊት፣ በዶጋሊ፣ በጉንደት፣ በጉርዓ፣ በሰሀጢ፣ በመተማ እና በዓድዋ ከወራሪዎች ጋር ተፋልመው አንፀባራቂ ድሎችን ያስመዘገቡት ናቸው፡፡ በዚህ ጀግንነታቸው እንዲህ ተብሎላቸዋል፡፡

**ጣሊያን ሰሀጢ ሳይ እግሩን ቢዘረጋ**
**እንደ ገብስ ቆላው አሉላ አባ ነጋ**

ይቺኛዋ ስንኝ ዓድዋ በመጣ ቁጥር በየመድረኩና በየመገናኛ ብዙኃኑ ተደጋግማ ትነገር እንጂ ስለአሉላ አባ ነጋ ሌሎች የውዳሴ ግጥሞችም አሉ፡፡

**ዮሐንስ መብቱን ሳሉሳ ቢሰጠው**
**እንደ ቀትር እሳት ቱርክን ገላመጠው**
**ጣልያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው**
**አጭዶና ከምሮ እንደ ገብስ አሰጣው!**
**አሉሳ አባነጋ የደጋ ሳይ ኮሶ**
**በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተኩሶ!**
**አሉሳ አባነጋ ካስመራ ቢነሳ**
**ቢችግረው ጣሊያን አስ ፎርሳ ፎርሳ፡፡**
**ጣሊያን በሀገርህ አልሰማህም ወሬ?**
**የበዝብዞች አሽከር የነ ሞት አይፈሬ**
**ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጎፈር አውሬ!**

ሌላኛው ጀግና ደግሞ ፊት አውራሪ ገበየሁ ናቸው፡፡ ፊት አውራሪ ገበየሁ በጦርነት መሃል እየገቡ የሚፎክሩ ነበሩ፡፡ በዚህ ጀግንነታቸው ጣሊያንን ሲያርበደብዱ ነበርና እንዲህ ተባለላቸው፡፡

**የዓድዋ ሥላሴን ጠላት አረከሰው**
**ገበየሁ በሞቴ ግባና ቀድሰው!**

ፊት አውራሪ ገበየሁ በተፋፋመ ጦርነት ውስጥ ገብተው ሲዋጉ በጣሊያን መድፍ ተገደሉ፡፡ ዳሩ ግን ጣሊያን ኢትዮጵያውያንን ማሸነፍ አልቻለም፡፡ ቆራጥ ጀግኖች እነ ባልቻ ሳፎ (ባልቻ አባ ነፍሶ) ሃይለኛ የመድፍ ተኳሽ ሆነው ጣሊያንን አጥረገረጉት፡፡ ወዲያውም እንዲህ ተባለ፡፡

**ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ**
**መድፍ አገላባጭ ብቻ ስብቻ!**

የዓድዋ በዓል በመጣ ቁጥር የሚታወሱት ሌሎች ግጥሞች ደግሞ ራሳቸው ንጉሱን አጼ ምኒልክን የተመለከቱት ናቸው፡፡ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ በብልህነታቸው፣ በጀግንነታቸው፣ በአጠቃላይ በነበራቸው የአመራር ብቃት ኢትዮጵያን ከጣሊያን ወረራ ታድገዋል። እነሆ ብቸኛዋ በቅኝ ያልተገዛች የአፍሪካ ነፃ ሀገር እየተባለች እንድትጠራ አደረጉ። ሕዝቦቿ በራሳቸው ባሕልና ወግ እንዲኮሩ አደረጉ፡፡ ለዚህም ነው እንዲህ የተባለው፡፡

**ምኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ**
**ግብሩ እንቁሳል ነበር ይህን ጊዜ ሐበሻ**

እስኪ አሁን ደግሞ በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርዱ ሲወራረዱ ከመጡት እንውጣና ወደ ሌሎች ሥራዎች እንሂድ፡፡ እነዚህኞቹ ባለቤት ያላቸው ናቸው፡፡ በዓድዋ ታሪክ ውስጣቸው ሀሴት ያደረገ ከያኒያን የሰሯቸው ናቸው፡፡ ገጣሚያንና ድምጻውያን ማለት ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የዓድዋ በዓል በመጣ ቁጥር ሁላችንም ከዓድዋ እኩል የምናውቃት ድምጻዊት እጅጋየሁ ሽባባው (ጂጂ) ናት፡፡

የጂጂ የዓድዋ ዘፈን እያንዳንዱ ስንኝ የምትተነተን ናት፡፡ ጥልቅ መልዕክት ያለው ነው፡፡ «ምን ማለት ይሆን?» ብለን ስናስብ እያደር እየተገለጠልን የሚሄድና የሚመስጥ መልዕክት ያለው ነው፡፡ እስኪ ከስንኞቹ ውስጥ «ሰው ሞቷል ሰው ሊያድን» የሚለውን ቃል እንውሰድ፡፡ አንድ ጀግና ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ አልሞትም ብሎ አይደለም፡፡ የሚሄደው ወገኑን ለማዳን ነው፡፡ ራሱ ሞቶ ሌላውን ማዳን ማለት ነው፡፡

**ሰው ሞቷል ሰው ሲያድን**
**ሰውን ሲያከብር**
**በደህንነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ**
**በክብር ይሄዳል ሰው ሲኖር ሰው ሞቶ**
**የተሰጠኝ ሕይወት ዛሬ በነፃነት**
**ሰው ተከፍሎበታል ከደም እና ከአጥንት**
**አድዋ ዛሬ ናት አድዋ ትላንት**
**መቼ ተነሱና የወዳደቁት።**

«ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት» አዎ! ይህ የዓድዋ ድል የተገኘው በልመና ወይም በግዥ አይደለም፡፡ በሰው ሕይወት ነው የተገኘው፤ የብዙዎች አጥንት ተከስክሶበትና ደም ፈሶበት ነው፡፡ ይህ የድል ታሪክ ዛሬም ነገም ይወደሳል፤ የጀግኖቻችን ውለታ ነውና! መቼ ተነሱና ነው የምንተወው?

እነዚህ ተወዳጅ አርቲስቶች በዘመን ተሻጋሪ ሥራዎቻቸው ጀግኖቻችን እንዳይረሱ አድርገዋል፡፡ ሥራዎቻቸውን ለትውልድ አስተላልፈዋል፡፡ ከእነዚህ ዘመን ተሻጋሪ ድምጻውያን አንዱ ተሾመ አሰግድ ነው። «እንዲያው ዘራፌዋ» በሚለው ዜማው ጀግኖችን እንዲህ ያስታውሳል፡፡

**መቅደላ አፋፉ ላይ ጎበዝ ወንድ ሆነበት**
**በመተማም ጎራ ጀግኖች አንድ ሆኑበት**
**እንዳይሞት ሆነ እንጂ ስሙን እንዳይቀብሩት**
**የመቅደላን መንደር የዶጋሊን ሜዳ**
**የማይጨው ዓድዋን የመተማን ሜዳ**
**ተዳኘበት እንጂ መች ዋኘበት ባንዳ**
**አፄ ቴዎድሮስ አባ ታጠቅ ካሳ**
**እምዬ ምኒልክ ጥራኝ የእኔ አንበሳ**
**በደም ታዋጋለህ በአካል ባትነሳ!**

ተሾመ አሰግድ በዚህ ዜማው ኢትዮጵያ ጥንትም የጀግኖች አገር እንደሆነች ይናገራል። አጼ ቴዎድሮስ፣ አጼ ዮሐንስ፣ አጼ ምኒልክ እና የጦር አርበኞችን ያወድሳል፡፡ ድል ያደረጉባቸውን ቦታዎች ይጠቅሳል፡፡ ጠላት ከእነዚህ ድሎች መማር እንዳለበት ይነግረናል፡፡

ሌላኛዋ ከያኒ ራሄል ዮሐንስ ናት፡፡ «ምኒልክ» በሚለው ዜማዋ እንዲህ ትላለች፡፡

**ብወጣው በእግሬ እንጦጦን**
**አላገኝም ወይ ጣይቱን**
**ፍቅሩን አብዝቶ ያስ ልክ**
**ዛሬም ይባላል ምኒልክ**
**እስኪ ወደ አንኮበር ተነሱ እንዝለቀው**
**እኛ አናየውም ወይ ምኒልክ ቢለቀው**
**የጣይቱን ማጀት ቢፈልጉት እዛ**
**አይጠፋም እስከ አሁን የጥጃ መዓዛ**
**እስኪ አንተ ሰውዬ እንደ አባትህ ሥራ**
**ከኮዳ እንድትቀዳው ወተቱን በእንስራ**
**ያገኙህ እንደሆን ግቢን ከአዲስ አባ**
**የደግ አዳራሽ ነው ሰተት ብለህ ግባ**
**አይቆረቁረውም እንግዳ ደጁን**
**ገብቶ ይጥገብ እንጂ ሥጋና ጠጁን**
**ያ ሁሉ ደስታ ፊቴ ይደቀናል**
**ሰው እንዴት በሄደው ባለፈው ይቀናል**
**ያ የፍቅር ጊዜ ያ የደስታ ቀን**
**ደግሞ በአይኔ መጥቷል እፊቴ ሲደቀን**

ይህ የራሄል ዮሐንስ ዘፈን የአጼ ምኒልክና የእቴጌ ጣይቱን ዘመን ያሳየናል፡፡ ደግነታቸውን ይነግረናል፡፡ ይሄን ደግነታቸውን ልናስታውስላቸው እንደሚገባ ይገልጻል፡፡

«አንኮበር» በሚለው የገነት ማስረሻ ዜማ ውስጥ ደግሞ ይሄን እናገኛለን፡፡

**እሱማ መቼ ጠፋው ብልሃቱ**
**ከበስተግራው አለች ፀሐይቱ**
**ደግ ሰው ነበር አመለ ምቹ**
**ፍቅር መጋቢ ለወገኖቹ**
**ከእንጦጦ ጋራ ዓድዋ ድረስ**
**ሰራዊት ይዞ በእግር በፈረስ**
**ስንት ቀን ይሆን የፈጀበት**
**ስንት በጋና ስንት ክረምት**
**ቀና ነው ልበ ቀና**
**የወገን ቤት ያቀና**
**አዛኝ ነው አመዛዛኝ**
**ሃቀኛ ብርቱ መዛኝ**
**እምዬ አባ ዳኛው**
**በፍቅር የተቃኘው**
**ቋንቋ ሃይማኖት ሳያግደው**
**መሃሉን ከዳር ያገናኘው**
**ሕዝቡን አንድ አርጎ ሄደ ስምሪት**
**በአንድ ባንዲራ በአንድ ነጋሪት**
**እምዬ ዳኛው ልበ ተራራው**
**በከዘራ ነው ጦሩን የመራው**
**ምን ቢባል ምን ቢወራ**
**ህያው ነው የሱ ሥራ**
**ያ ቢሄድ ያ ቢመጣ**
**እሱስ ከልቤ አይወጣ**
**የጎራዴው ብልጭታ**
**ጠላትን ድባቅ መታ**
**አንኮበር ሳይ ደገሰው**
**ዓድዋ ሳይ ለኮሰው!**

«እሱማ መቼ ጠፋው ብልሃቱ፤ ከበስተግራው አለች ፀሐይቱ» ይላል የገነት ማስረሻ ዘፈን፡፡ ከበስተግራው ማለት እቴጌ ጣይቱ የአጼ ምኒልክ ሚስት መሆናቸውን ለመግለጽ ነው፤ በልማድ ሚስት ግራ ጎን ተብላ ትጠራለች፡፡ ለአጼ ምኒልክ ስኬት ሁሉ የእቴጌ ጣይቱ ብልህነት እንዳለበት ይነገራል፡፡

«ቋንቋ ሃይማኖት ሳያግደው መሃሉን ከዳር ያገናኘው»፤ የዓድዋ ድል የተገኘው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ከጫፍ እስከ ጫፍ ተጠራርተው በመሄድ ነው፡፡ አንድ ልብ፣ አንድ ሀሳብ ሆነው፤ ለአንድ ዓላማ ከአራቱም አቅጣጫ እየተመሙ ሄደው ጠላትን ድባቅ አድርገው መጡ፡፡ አንኮበር ላይ የተደገሰው የዓድዋ ጦርነት ዓድዋ ላይ ተለኮሰ፤ ዓድዋ ላይ የተለኮሰው እሳት ጠላትን ለብልቦ መለሰ፡፡

እቴጌ ጣይቱ ጀግንነትን ከብልህነት ጋር የያዙ ናቸው። በጦርነት ጊዜ ቁጣና ችኩልነት ብቻ እንደማያዋጣ፤ ይልቁንም ብልህነት መኖር እንዳለበት አሳይተዋል፡፡ ይህን የእቴጌ ጣይቱን ብልህነትና ጀግንነት የሚገልጸውን የቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ስንኝ መሰናበቻ አድርገነዋል፡፡ ክብር ለጀግኖቻችን!

**የቀፎው ንብ ሲቆጣ ስሜቱ**
**ከፊት ሆና መራችው ንግስቲቱ !**

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# ዓድዋን ያከበረ የስነ ጥበብ አውደ ርዕይ

ዳግም ከበደ



በጣሊያን ወራሪ እብሪት ተሸናፊነትና በጀግኖች ኢትዮጵያውያን አርበኞች ድል አድራጊነት የተጠናቀቀው የዓድዋ ድል ድፍን 128 ዓመታትን አስቆጠረ። የታሪክ ሰነዶችም ለትውልድ ‹‹የሰው ልጆችን እኩልነት የበየነ፤ የነጭና የጥቁር የበላይነት ግንብ ያፈረሰ ድል ከወደ ኢትዮጵያ የዓድዋ ተራሮች ተመዘገበ›› በማለት የዓድዋን ድል ከተቡ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ትውልድ ከታላቁ የዓድዋ ድል ብዙ ቁምነገሮችን ተምሯል። በየዘመኑ የነበሩ የማኅበረሰቡ መሪዎች፣ ተፅእኖ ፈጣሪዎች፣ መምህራን ዓድዋን የሰው ልጅ የስብእና መለኪያ፣ የፍትህ ሚዛን፣ የነፃነት ምሳሌ አድርገው ትውልድ እንዲማር መክረዋል። ዛሬም በተመሳሳይ ዓድዋን በመዘከር መጪው ትውልዱ አያሌ ቁምነገር እንዲጨብጥ፣ የአባቶቹን ታሪክ ጠንቅቆ እንዲያውቅ የሚሞክሩ በርካቶች ናቸው። ከእነዚህ መካከል የስነ ጥበብ ባለሙያዎች (ሰዓሊያ) ይገኙበታል።

ሕብር የሰዓሊያን ቡድን ይባላል። በ14 ወጣት ሰዓሊያን ከስድስት ዓመት በፊት የተመሰረተ ነው። የስዕል ስራዎቻቸውን በዓድዋ ድል ላይ በማድረግ ተተኪው ትውልድ የአባቶቹን ገድልና ኢትዮጵያዊ አንድነትን በጥበብ እየተዝናና እንዲያውቅ የማድረግ ዓላማን አንግበው ተነስተዋል። በተጨማሪ የዓድዋ ድል በተለያዩ መስኮች ከሚተረከው በተጨማሪ በስዕል አማካኝነት ያልተዘመረላቸውን ኢትዮጵያዊ ጀግኖች በማወደስ፣ ታሪካቸው ቋሚ ቅርስ ሆኖ ለትውልድ እንዲተላለፍ ይሰራሉ።

የዓድዋን ታሪክ በስዕል አማካኝነት ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ ይሻሉ። ይህ ሁነት ቀጣይነት ኖሮት ዘመን ተሻጋሪ ስራዎችን ለትውልድ ለማሻገር፤ ሕብር የስነ ጥበብ ማዕከል በማቋቋምና ኢትዮጵያዊነት ሁሌም እንዲዘመርለት ቀለሙን፣ ማንነቱን፣ ባሕሉን ብሎም ወጉን ጠብቆ የትውልድ መኩሪያና መመኪያ እንዲሆን ለማስቻል፤ የዓድዋ ገድል ከኢትዮጵያ አልፎ የመላው ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ በመሆኑ በስዕል አማካኝነት ተተኪው ትውልድ ገድሉን በሚገባው እንዲረዳው፤ ታሪኩም በስዕል ለመጭው ትውልድ በቋሚ ቅርስነት እንዲተላለፍ በማሰብ እየሰሩ መሆኑን የቡድኑ አባላት ይናገራሉ።

ሰዓሊ አለምሰገድ በኃይሉ ይባላል። የሕብር የሰዓሊያን ቡድን አባል ነው። ባለፉት ስድስት ዓመታት በልዩ ልዩ ቦታዎች በተካሄደው የዝከረ አድዋ አውደ ርዕይ ላይ ተወዳጅ ስራዎችን አቅርቧል። አርቲስቱ በስዕል ስራዎቹ በተለየ በቅርፅ፣ ቀለማት፣ እንዲሁም በእይታ ላይ የኢትዮጵያን አሳሳል ዘይቤ ወደ ዘመናዊው ስልት ለማሻሻል በርከት ያሉ አስተዋፅዎችን ማበርከት ችሏል።

አለምሰገድ ከሙሉ ጊዜ የስቱዲዮ ሰዓሊነቱ ባሻገር የተለያዩ ሰብአዊ ጉዳዮች ላይ አተኩረው የሚሰሩ ድርጅቶች ጋርም ሰርቷል። የአማኑኤል የአእምሮ ሕክምና ተቋምን ማንሳት ይቻላል፡፡ በዚህ ተቋም ውስጥ ‹‹አርት ቴራፒ›› አሊያም በስዕል ሕሙማንን ማከም በሚል ፕሮጀክት ውስጥ ተሳታፊ መሆን ችሏል።

አርቲስት አለምሰገድ በርካታ የቡድን አውደ ርዕይ ዝግጅቶች ላይ ተካፍሎ ስራዎቹን ማቅረብ ችሏል። በተለይ የሕብር ሰዓሊያን ቡድን መስራችና አባል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘንድሮውን ጨምሮ በስድስቱም አውደ ርዕይ ላይ ተካፋይ እንደሆነ ይገልፃል። ከዚያ ባሻገር ሰዓሊው በብሄራዊ ሙዚየም፣ በዩኤን ዲፒ፣ በአፍሪካ ሕብረት፣ እንዲሁም ከሁለት መቶ በላይ አርቲስቶች በየዓመቱ የሚሳተፉበት ትልቅ አውደ ርዕይ ላይ ተሳታፊ በመሆን ተወዳጅነትን አትርፏል።

‹‹የሕብር የሰዓሊያን ቡድን አድዋን በስዕል ስራዎች ለመዘከር የተመሰረተው 2011 ዓ.ም ላይ ነው›› የሚለው ሰዓሊ ዓለምሰገድ፤ ዘንድሮም በሜትሮፖሊታንት ጋለሪ እስከ መጋቢት አንድ ድረስ የሚቆይ አውደ ርዕይ የካቲት 15 ቀን መከፈቱን ይናገራል። ይህ አውደ ርዕይም ለስድስተኛ ጊዜ መካሄዱን ይገልፃል። 27 ሰዓሊያን የተሳተፉበት አውደ ርዕይ ‹‹1888›› የሚል ርዕስ እንዳለው በመግለፅ፤ በዚህ ቁጥር መሰየም ያስፈለገው ጦርነቱ የተካሄደበትን ጊዜ ለማስታወስ በማሰብ መሆኑን ይናገራል።

ሰዓሊ ዓለም ሰገድ አድዋን በልዩ ሁኔታ የሚዘክረው የስዕል አውደ ርዕይ የቡድኑ አባላት ብቻ የሚሳተፉበት አለመሆኑን ይገልፃል። ባለፉት አራት ተከታታይ ዓመታትም የተለያዩ ሰዓሊዎችን (በሕይወት ያሉትም ሆነ የሌሉትን) አድዋን የሚገልፁ የስዕል ስራዎቻቸውን በመሰብሰብና በመጋበዝ በጋራ መደረጉን ይናገራል።





የአድዋን ድል ታሪኮች በስዕል ለተከታታይ ዓመት በመስራትና ለዕይታ በማብቃት ሕብር የሰዓሊያን ቡድን ስኬታማ ውጤት አስመዝግቧል የሚለው ሰዓሊ አለም ሰገድ፤ እስካሁን ድረስ ለትውልድ የሚሻገሩ፣ በቅርስ መልክ የሚቀመጡና የታሪክ ማስረጃ የሚሆኑ ከ150 በላይ ስዕሎች በቡድኑ አባላትና ተጋባዥ አቅራቢያም መሰራቱን ይገልፃል። ዋና ዓላማውም ለድሉና ለድሉ ባለቤት አርበኞች የሚገባቸውን ክብር መስጠትና ታሪክን በሚገባ መሰነድ መሆኑን አመላክቷል።

‹‹የሕብር ሰዓሊያን ቡድን የሚያዘጋጀው አውደ ርዕይ ላይ በርካታ ታዳሚዎች በየዓመቱ ይሳተፋሉ››የሚለው ሰዓሊ አለምሰገድ፤ ማኅበረሰቡ ከአውደ ርዕይም በላይ የአባቶቹን ታሪክ፣ ጀግንነት፣ በጊዜው የነበራቸውን ፅናትና ሌሎችም ሁነቶችን ለመዘከር ጭምር እንደሚገኝ ይገልፃል። ሰዓሊያኑም ያንን በማሰብ በየዓመቱ በአዳዲስ ስራዎች ተዘጋጅተው ስራዎቻቸውን ይዘው እንደሚመጡ ያስረዳል።

ሰዓሊ ዓለም ሰገድ ስዕል ታሪክን በሚመች መንገድ ለመግለፅና ለትውልዱ ለማስተማር ምቹ የጥበብ ዘርፍ መሆኑን ይናገራል። በስዕል ወደኋላ በመሄድ ሀሳብን ለመግለፅ የሚያስችል እድል ማግኘት እንደሚቻል በመናገርም ይህንን የጥበብ አቅም ተጠቅሞ የአድዋ ድል ከፍ ብሎ እንዲዘከርና ለትውልዱ እንዲተላለፍ የሕብር የሰዓሊያን ቡድን በተነሳሽነት እየሰሩ መሆኑን ያስረዳል።

በተለይ አሁን ያለው ትውልድ እድሜያቸው ገፋ ካለ አርበኞች አሊያም አዛውንቶች ታሪኩን መስማት ወይም መረዳት ቢችልም ቀጣይ ትውልድ ግን ይህንን እድል ላያገኝ ስለሚችል ስዕልና ሌሎች የጥበብ ስራዎችን ተጠቅሞ የአድዋን የድል ታሪክ ማሻገር እንደሚያስፈልግ ያስረዳል። በተለይ በጦርነቱ ወቅት በምስል ያልተቀረፁ አሊያም በፅሁፍ ብቻ የተቀመጡ ታሪኮችን በስዕል በሸራ ላይ ማስፈር ታሪኩን ለመረዳት እንዲሁም በምናብ ወደኋለ መለስ ብሎ ለመቃኘት እድል ይከፍታል የሚለው ሰዓሊ አለምሰገድ፤ ይህንን አጋጣሚ ለመፍጠር ሕብር የሰዓሊያን ቡድን በዓላማ ተነሳሽነት እየሰራ መሆኑን ያነሳል።

ሰዓሊ አለምሰገድ፤ እርሱን ጨምሮ የቡድን አባላቱ በዓድዋ ጦርነት ወቅት የነበሩ ክስተቶችን ቀለምና ሸራቸውን በማዋሃድ ሕያው አድርገው እንደሚሰሩ ይገልፃል። የጦር መሪዎችን፣ አርበኞችን፣ ጦርነቱ የተካሄደበት ዓድዋ ተራሮችን፣ በስድስት ሰዓቱ ውስጥ የተካሄዱ ገድሎችን፣ በልዩ ሁኔታ በታሪክ የሰፈሩ የአርበኞች ገድልን እንዲሁም ልዩ ልዩ የዓድዋ ድል ታሪካዊ ክስተቶችን የሰዓሊያን ቡድኑ በርዕስነት በመምረጥ በየራሳቸው የአሳሳል ዘዴ በሸራዎቻቸው ላይ ያሰፍሯቸዋል።

ለምሳሌ ያህል ሰዓሊ ዓለም ሰገድ በሜትሮ ፖሊታንት ጋለሪ እየተካሄደ ባለው አውደ ርዕይ ላይ እቴጌ ጣይቱን በዋና ርዕሰ ጉዳይነት ይዞ ቀርቧል። ንግስቲቷ በመቀሌ ከተማ የጣሊያን ሰራዊት ውሃ የሚያገኝበትን ስፍራ በማስቆም የወሰዱትን የጦር ስልት እና የአመራር ጥበብ የሚዘክር የስዕል ስራ ለታዳሚያን አቅርቧል።

‹‹1888››በሚል ስያሜን ያገኘው የዘንድሮው የሕብር ሰዓሊያን ቡድን አውደ ርዕይ በተጋባዥነት 16 ሰዓሊያንን አሳትፏል። ከአባላቱ ውስጥ ደግሞ 11 ሰዓሊያን አንድ ወይም ሁለትና ሶስት ስዕሎችን በማቅረብ ተሳታፊ ሆነዋል። ከዚህ ቀደም በነበሩ ዝግጅቶች ላይ ሕፃናት ሰዓሊያን እንዲሳተፉና ልምድ እንዲያገኙ መደረጉን የሚናገረው አለም ሰገድ፤ ዘንድሮ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይጋበዙ መቅረታቸውን ያነሳል። በቀጣይ ጊዜያት ግን አገር ተረካቢ የሆኑ ታዳጊዎች መሰል ልምድ እንዲኖራቸው እነሱን የሚያሳትፍ ዝግጅት እንደሚካሄድ ይናገራል።

ሰዓሊ አለም ሰገድ ሕብር የሰዓሊያን ቡድን አባላት ይህንን አውደ ርዕይ ከዚህም በተሻለ በማሳደግ ዓድዋን እና ጀግኖች አርበኞች ያስመዘገቡትን ድል ለመዘከር እንደሚሰሩ ይናገራል። ቡድኑ ከዓድዋ ድል ባሻገር ‹‹ውብ ኢትዮጵያ›› የሚል ስያሜ ያለው አውደ ርዕይ ለሁለት ጊዜያት ማዘጋጀታቸውን ገልፆ፤ ኢትዮጵያዊነትን ከፍ የሚያደርጉ፣ ታሪክን የሚዘክሩና ለትውልድ የሚያሻገሩ በርካታ አውደ ርዕይዎችን በጥራትም በብዛትም ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ይናገራል።

እንደ መውጫ

ታላቁ የጥቁር ሕዝብ ድል ዓድዋ የጀመረው ከጦርነቱ በፊት ሕዝቡ የንጉሰ ነገስቱን ጥሪ ሰምቶ ከጫፍ ጫፍ በተመመበት ዕለት ነው። አዋጁም ገና ከመነሻው ላይ የድል አድራጊነት መንፈስ እንደደረበበት የሚያመላክት የክተት አዋጅ የተላለፈበት ነው። ይህን ታላቅ ገድል እና ስነ ልቦና ለትውልድ ማጋባት ያስፈልጋል። ለዚህ ሁነኛ መንገድ ደግሞ የጥበብ ስራዎች ናቸው።

የካቲት ታላላቅ ገድሎች የተፈጸሙበትና አንፀባራቂ ድሎች የተመዘገቡበት ወር ነው። የካቲት ወር ለኢትዮጵያውያን፣ ለመላው አፍሪቃ ብሎም ለመላው ጥቁር ሕዝቦች ድል በደማቁ የታተመበት የአድዋ ድል የተበሰረበት ወር ነው። በመሆኑም በተለያዩ ሙያ ላይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በየሙያዎቻቸው የዓድዋን ድል በተለያዩ ክንውኖች በድምቀት ሲያከብሩት ይገባል። የዘንድሮው 128ኛው ዓመት የዓድዋ ድልም በዛሬዋ እለት በዚህ መንፈስ ሊከበር ይገባል፡፡

ሕብር ሰዓሊያን ቡድን ‹‹ የኛ የክተት አዋጅ አባቶች ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸው ከስክሰው ያቆዩንን ሀገር ፈጣሪ የቸረንን ጥበብ ተጠቅመን ታሪካቸውን ለመጭው ትውልድ የማስተላለፍ ጥሪ ነው›› በማለት በየዓመቱ ለተከታታይ ስድስት ጊዜያት ስራዎቻቸውን ለታዳሚያን አቅርበዋል። ዋና ዓላማቸውም የዓድዋ ገድል ከኢትዮጵያ አልፎ የመላው ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ በመሆኑ በስዕል አማካኝነት ተተኪው ትውልድ ገድሉን በሚገባው እንዲረዳው ታሪኩም በስዕል ለመጭው ትውልድ በቋሚ ቅርስነት እንዲተላለፍ በማሰብ መሆኑን ገልፀውልናል። የዝግጅት ክፍላችንም ‹‹1888›› የመሰሉ ዓድዋን ያከበሩ የስነ ጥበብ አውደ ርዕይ እንዲበዙ እየተመኘን በዚሁ አበቃን። ሰላም !!

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስጋራ ትርክቶቻችን ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ብሔራዊ አንድነታችንን እናጠናክር

የአንድ ሀገር ህልውናም ሆነ ቀጣይ እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዛች ሀገር ሕዝቦች ነባራዊ እውነታ እንደሆነ ይታመናል። በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ ያላቸው ሕዝቦች ይህንን ታሪካቸውን ለማስቀጠል በትውልዶች መካከል በሚኖረው ቅብብሎሽ ዙሪያ ሰፊ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ህብረ ብሔራዊነትን የተላበሱ፤የተለያዩ ሃይማኖቶች ፣ ባህሎች እና ማንነቶች ያሉባቸው ሀገራት ሕዝቦች ፣ ዘመናትን የተሻገሩባቸውን እሴቶቻቸውን በተደራጀ መንገድ ለትውልዶች የሚያስተላልፉበትን ተጨባጭ እውነታ መፍጠር ካልቻሉ፤ በየዘመኑ ሊፈጠሩ የሚችሉ ተግዳሮቶች ሀገራዊ ህልውናቸውን ስጋት ላይ ሊጥሉ ይችላሉ።

በተለይም እንደ ሀገር አጽንተው ሊያቆሟቸው የሚችሉ የጋራ ትርክቶቻቸው ላይ ትኩረት ሰጥተው መሥራት ፣ እነዚህን የጋራ ትርክቶቻቸውን በትውልዶች ልብ ፣ አእምሮና መንፈስ ውስጥ መጽናት ካልቻሉ፤ የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ለአደጋ ተጋላጭ መሆናቸው የማይቀር ነው ።

ይህ እውነታ ላለፉት ስድስት አስርት ዓመታት እንደ ሀገር ለእኛ ለኢትዮጵያውያን የሰላምና የመረጋጋት ፈተና ሆኖ ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል። ከዛም አልፎ ዛሬ ላይ ለጀመርነው አዲስ የለውጥ ጉዞም ዋነኛ ተግዳሮት በመሆን ወደ ኋላ እየጎተተን፤ አለፍ ሲልም የማንነት መደበላለቅ እየፈጠረብን ነው።

ቀደም ባሉት ጊዜያት አንድም ለወል ትርክቶቻችን በቂ ትኩረት መስጠት አለመቻላችን፤ ከዛም ባለፈ በትርክቶቹ ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ አለመድረሳችን፤ የትላልቅ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ትርክቶች ባለቤት ሆነን፤ እራሳችንን በዛ ልክ መግለጥ የሚያስችል ማንነት መፍጠር ሳንችል ቀርተናል።

ለዚህ ደግሞ ትልቁ ማሳያ የዓድዋ ድል ነው ።ይህ ድል የቀደሙት አባቶቻችን ለነጻነትና ለፍትህ የከፈሉት ትልቅ አንጸባራቂ ድል ነው። ለድሉ ያበቃን የነፃነትና የአልገዛም ባይነት መንፈስም በጭቆና ቀንበር ውስጥ ለነበሩ የዓለም ሕዝቦች እኩልነትን ያወጀ የነፃነት ማነቃቂያ ደውል ነው። እኛንም እንደ ሕዝብ እና ሀገር በዓለም አቀፍ ደረጃ የነፃነት ሰንደቅ ያደረገን ነው።

ይህ በብዙ መስዋእትነት በደም የተጻፈ የአባቶቻችን የተጋድሎ ታሪክ፤ ለነፃነትና ለፍትሕ ቀናኢ በሆኑ ሕዝቦች ዘንድ ከፍ ያለ ከበሬታን ቢያጎናጽፈንም፤ እኛ ግን በብዙ መስዋእትነት ለተጻፈው ታሪካችን ተገቢውን ከበሬታ በማጣታችን ባልተገቡ የልዩነት ትርክቶች ባልተገባ የታሪክ ምእራፍ ውስጥ እንገኛለን። ዛሬ ላይ እየተሠራ ያለው ዘርፈ ብዙ ተግባርም ይሄንን የተዛባ ትርክትና ሂደት ለመለወጥና የተባበረ ማህበረሰብን ለመፍጠር ነው።

ዓድዋ እንደ ሀገር ለዘመናት የዘለቀው የሀገረ መንግሥት ታሪካችን ምስጢር አካል ነው። ስለ ሀገር ያለን ፍቅር ፣ ለነፃነትና ለፍትህ ያለን ቀናኢነት ተጨባጭ መገለጫ ነው፤ የትኛውም ዓይነት ልዩነት ብሔራዊ አንድነታችንን ሆነ የሀገረ መንግሥት ታሪካችንን የሚገዳደር አቅም እንደሌለው ያመላከተ ነው።

የድሉ ምስጢር ከሁሉም በላይ በተደመረ ሀገራዊ ማንነት፤ ፈተናዎችን በአሸናፊነት የመወጣት እሳቤ ነው። የዚህ እሳቤ መሰረቱ ጥልቅ የሀገር ፍቅር ፣ ለፍትህና ለነፃነት የተገዛ ማንነት ፣ ለሀገራዊ ነገዎች እና ለመጪው ትውልዶች የተሻለ እጣ ፈንታ ከመሻት የሚመነጭ ትውልዳዊ ኃላፊነት ነው።

ይህ ኃላፊነት የሚመነጨው እንደ ትውልድ ትናንቶችን በተገቢው መንገድ አውቆ ከመረዳት፣ ዛሬን በትናንት መሠረት ላይ በመገንባት ፣ ነገዎችን በጊዜ ሂደት ሙሉነት አጣጥሞና አቻችሎ ማሰብና መንቀሳቀስ ሲቻል ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ በየዘመኑ መጥቶ የሚሄደው ትውልድ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል።

የዛሬውን የዓድዋ በዓል ስናከብርም፤እንደ ትውልድ ለትናንት የጋራ ትርክቶቻችን ተገቢውን ትኩረት በመስጠት፤ ብሄራዊ አንድነታችንን በሚያጠናክር መልኩ ሊሆን ይገባል። ትናንትን በትናንት ዓይን እያየን ፤ በዛሬ መነፅር ልንረዳው ያስፈልጋል ።ለዚህ ደግሞ እንደ ትውልድ ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠር ያስፈልገናል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# “የዓድዋን ዕሴቶች በሚገባ በመጠቀም እንደ ዓድዋ ተራሮች የጸናች ኢትዮጵያን መገንባት ይቀረናል”

**- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ**

**እንኳን ለ128ኛው የዓድዋ ድል በዓል አደረሳችሁ!**

እናቶቻችንና አባቶቻችን ታላቁን የዓድዋ ድል ከሰጡን 128 ዓመታት አስቆጥረናል። የዓድዋ ድል የሰጠንን ዕሴቶች ግን በሚገባ የተጠቀምንባቸው አይመስለኝም። ቢያንስ አራቱን ታላላቅ የዓድዋ ድል ዕሴቶች ለሀገር ግንባታ ልንጠቀምባቸው የግድ ይለናል።

የመጀመሪያው ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ነው። ኅብረ ብሔራዊ አንድነት የኢትዮጵያ ዋናው መልኳ መሆኑን ከዓድዋ ዘመቻ በተሻለ ለማሳየት የቻለ ክስተት በዘመናዊ ታሪካችን አናገኝም። የዓድዋ ዘመቻ ሁለት ጊዜ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን አሳይቷል። የመጀመሪያው በጦርነቱ ዘመቻና ድል ጊዜ ነው።

ዛሬ በምናውቃት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ማኅበረሰቦች መካከል ወደ ዓድዋ ያልዘመተ ወገን የለም ብሎ መናገር እውነትን መናገር ነው። ሁለተኛው ክስተት ደግሞ የዓድዋ ድል በተገኘ በሰባት ዓመቱ የዓድዋ በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ ሲከበር ትርዒቱን ያቀረቡት ከተለያዩ የሀገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች የመጡ የኢትዮጵያ ጦር አባላት ነበሩ። በዚህ ትርዒት ኢትዮጵያ ኅብረ ብሔራዊት ሀገር መሆንዋን በአደባባይ ሰልፈኛው አሳይቶ ነበር።ይሄ በዓድዋ ዘመቻና በዓል የተንጸባረቀ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት አጽንተን ልንይዘው ይገባል።

ኢትዮጵያ ማለት ኅብረ ብሔራዊ ማንነት ያላቸው ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባት ሀገር ናት። ኅብረ ብሔራዊነታቸው ከፈጣሪ ሲያገኙት ነው። አንድነታቸውን ደግሞ እነርሱ ራሳቸው በዘመናት ትስስርና መስዋዕትነት ገንብተውታል። ኢትዮጵያ እነዚህ ሁለቱን ነገር፣ ግን አንዱ ከሌላው ጋር ሳይነጣጠል የሚኖሩትን መገለጫዎቿን ትታ ኢትዮጵያ አትሆንም። በእያንዳንዱ ጉዞዋ ይሄንን እያረጋገጠች መጓዝ አለባት።

ሁለተኛው ዕሴት ለታላቅ ሀገራዊ ዓላማ ሲባል ንኡስ ፍላጎቶችን መሰዋት ነው። ወደ ዓድዋ የዘመቱ ሁሉ በወቅቱ በነበረው ሥርዓተ መንግሥት የሚስማሙና የተደሰቱ አልነበሩም። አንዳንዶቹ እንዲያውም ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ግጭትም ቅራኔም ነበራቸው። አንዳንዶቹም በነበረው ሀገራዊ ሁኔታ ቅር ተሰኝተው ከጠላት ጋር የሚሠሩ ነበሩ። ነገሩ የሀገር ጉዳይ ሲሆንባቸው ግን ሁሉም ንኡስ ፍላጎቶቻቸውን ትተው፣ ለታላቁ ፍላጎት ለሀገር ህልውና መስዋዕት ለመሆን መጡ። ማንኛውም ፍላጎት ከሀገር ፍላጎት በታች መሆኑንም አሳዩን።

እንኳን ዛሬ ብዙ ዓይነት መረጃ፣ ዕውቀትና የሃሳብ መንገዶች ባሉበት ዘመን ቀርቶ ከመቶ ዓመት በፊትም ሰዎች ልዩ ልዩ ፍላጎቶች ነበሯቸው። በፍላጎቶቻቸው የተነሳም ቅራኔዎችና ግጭቶች ነበሩ። ሁሉንም ለአንድ ዓላማ የምታስተሳስር ሀገር የምትባለው ናት። ዛሬም ንኡስ ፍላጎቶቻችን ከኢትዮጵያ አይበልጡም።

ኢትዮጵያን የሚያዳክም፣ የሚያሳንስና የሚያሳጣ መንገድ ከትልቁ ዓላማ የሚጋጭ መንገድ ነው። ጦርነት የትልቁ ዓላማ የኢትዮጵያ ህልውና ማስከበሪያ እንጂ የንኡስ አካባቢያዊና ግላዊ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ሊሆን አይገባም። ጦርነት ለትንሽ ነገር የሚወጣ ወጪ አይደለም።

ዘመኑ ብዙ ፈተናዎች እንዳሉት ሁሉ ብዙ የመፍትሔ አማራጮችም አሉት። መከራከር፣ መነጋገር፣ መወያየት፣ በሕግ መዳኘት፣ አንዱ ሌላውን መሸከም፣ የትየለሌ አትራፊ መንገዶች አሉት። ትልቁ ዓላማ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ ስንል ንኡስ ዓላማዎቻችንን እያመሙን እንኳን ቢሆን መሰዋት አለብን።

ሦስተኛው ዕሴት የጦርነትን ምርቅና ፍትፍት ማወቅ ነው። ጦርነት ምንም ያህል በአሸናፊነት ቢጠናቀቅ የሚያስከፍለው ዋጋ አለው። የዓድዋ ዘማቾች ሀገር ሆኖባቸው፤ ሉዓላዊነት ሆኖባቸው፤ የታላቅ ዓላማ ጉዳይ ሆኖባቸው እንጂ ጦርነት የመጀመሪያ አማራጫቸው አልነበረም። ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ነገሩ በሰላም እንዲቋጭ ደጋግመው ጽፈዋል፤ ለምነዋል፤ አልሆነም። የዓድዋ ዘመቻ በኢትዮጵያ አሸናፊነት ተጠናቀቀ።

የኢትዮጵያ ዘማቾች ግን ከድል የተመለሱት በደስታ ብቻ አይደለም። ከፊታውራሪ ገበየሁ ጀምሮ አያሌ ጀግኖች ለትልቁ ዓላማ ለኢትዮጵያ ህልውና ሲሉ ተሠውተዋል። የሄዱት ሁሉ አልተመለሱም። የኢትዮጵያ ሠራዊት በድልና በኀዘን ነው የተመለሰው። ብዙዎችም በየአካባቢያቸው በፌሽታ አልነበረም ድሉን ያከበሩት። እንኳን በራሳቸው ወገኖች፣ በጣልያኖች መሞት ኢትዮጵያውያን አዝነዋል።

ጦርነት ተገድደን ብቻ ለትልቁ ዓላማ ስንል የምንገባበት የመጨረሻ አማራጭ እንጂ ከደረት ኪሳችን ቶሎ የምንመዘው አይደለም። እዚህም እዚያም የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በጠመንጃ ለመፍታት መነሣት የዓድዋ ዘማቾችን ኀዘን አለመጋራት ነው። የዓድዋ ዘማቾች ድልን ብቻ ሳይሆን ጦርነት የሚያስከትለውን መከራም ጭምር አስተምረውን አልፈዋል።

አራተኛው ትዕግስት፣ ዝግጅት እንጂ ፍርሐት አለመሆኑን ነው። ጣልያኖች ከሦስት ዓመታት በላይ ኢትዮጵያን ሲገፏት ነበር። በሀገሪቱ የደረሰውን የእንስሳትና የሰዎች ማለቅ ምክንያት አድርገው ትንኮሳውን አባብሰው ነበር።

ኢትዮጵያ እየተገፋች እንኳን ቢሆን ታግሳለች። ትዕግስቷ ግን ከዐቅመ ደካማነቷ የመጣ አይደለም። ለባሰው ነገር እየተዘጋጀች ስለነበር እንጂ። እህል እስኪደርስ፣ ሰው እስኪያገግም፤ የተገዛው መሣሪያ እስኪደርስ፣ የደረሰው መሣሪያ ከጦሩ ጋር እስኪላመድ ታግሳለች። በመጨረሻ ግን የትዕግስቷን ውጤት በዓድዋ ተራሮች ላይ አሳይታለች።

ኢትዮጵያ ዛሬም ትታገሳለች። እየተገፋችም እንኳን ቢሆን ትታገሳለች። የምትታገሰው ስለሚያቅታት አይደለም። ለባሰው ነገር ስለምትዘጋጅ ነው። ያ የባሰው ነገር ሲመጣ የዓድዋውን ድል በብዙ እጥፍ ትደግመዋለች። እነዚህን ዕሴቶች ዘወትር ማሰብ፣ አስበን መተግበር እንድንችል የሚያስታውሰን ነገር ያስፈልግ ነበር። ዓድዋን የሚመጥን ታሪኩንም ዕሴቱንም የምናስብበት መታሰቢያ ዘመቻው በተጀመረበት ሥፍራ ባስገነባን ማግሥት ነው በዓሉን የምናከብረው። ይሄም ለዘንድሮው በዓል ሞገስና ክብር ጨምሮለታል።

ዛሬ መታሰቢያውን በከበረ ሁኔታ አከናውነናል። ነገ ግን የዓድዋን ዕሴቶች በሚገባ በመጠቀም እንደ ዓድዋ ተራሮች የጸናች ኢትዮጵያን መገንባት ይቀረናል። ያ ደግሞ የሁላችንንም ስክነት፣ ብስለትና ጥምረት ይፈልጋል።

በድጋሚ መልካም የዓድዋ ድል በዓል ይሁን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**የካቲት 22/2016 ዓ.ም**

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# «ታሪክን ጠለቅ አድርጎ ለተገነዘበ ሰው ዓድዋ ብዙ ምስጢሮችን ያዘለ ነው»

**- ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር)**
**የታሪክ ምሁርና ተመራማሪ**

አስቴር ኤልያስ

**ዛሬ 128ኛው የጥቁር ሕዝቦች ድል በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበርበት ታላቅ ዕለት ነው፡፡ እለቱ ለነጻነት እና ለፍትህ የተከፈለ አንጸባራቂ ድል ከመሆኑ አንጻር እስካሁንም አቻ ያልተገኘለት ሆኖ ዘልቋል። ድሉ የጥቁር ሕዝቦች አንገት ቀና ያለበት፤ ለኢትዮጵያውያንና ለመላ ጥቁር ሕዝብ የማይረሳ ቀንና ታላቅም ኩራት የፈጠረ ነው፡፡ ከዚህ ታላቅ ድል ጋር ተያይዞ አዲስ ዘመን ከተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር) ጋር ቆይታ አድርጎ ተከታዩን አጠናቅሯል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ የተመረቀው የዓድዋ መታሠቢያ ሙዚየምን ሲያዩ እንደ አንድ የታሪክ ተመራማሪ ምን ተሰማዎት?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** የታሪክ ተመራማሪ እንደመሆኔ የዓድዋ መታሠቢያ ሙዚየም ለምረቃ በመብቃቱ በጣም ደስ ብሎኛል፡ ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከታሪክ አንጻር አገራችን እየገጠማት ያለ አወዛጋቢ ነገር ባለበት በዚህ ጊዜ ታሪክ ያለው ተቋም ተገንብቶ ለምረቃ በመብቃቱ ታላቅ ኩራት ነው፡፡ ይህ መሆኑ ለታሪክ ያለንን ክብር እና ለታሪክ መስጠት የሚገባንን አክብሮት መስጠታችንን የሚያንጸባርቅ ሙዚየም ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

የሙዚየሙ ሕንጻ በአንድ በኩል ከ128 ዓመት በፊት በተደረገው ጦርነት ላይ ያገኘነውን ድል ለመያዝ ሲባል የተዘጋጀ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከ128 ዓመት በፊት እና ከ128 ዓመት በኋላ ያለው በተለይ የድህረ ዓድዋ የሚባለው ምን መምሰል አለበት የሚለውን ያጠቃለለ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የዓድዋ ድልን የሚገልጹት እንዴት ነው?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** የዓድዋ ድልን ታሪክ ጠለቅ አድርጎ ለተገነዘበ ሰው ዓድዋ ብዙ ምስጢሮችን ያዘለ ነው፡፡ ዓድዋ ለምሳሌ አንድ አራት የጣሊያን ብርጌድና ከመቶ እስከ ሁለት መቶ ሺ የሚገመቱ ኢትዮጵያውያን ሜዳ ላይ ገጥመው ተዋግተው ኢትዮጵያውያኑ ያሸነፉበት ብቻ አይደለም። ዓድዋ ብዙ ተምሳሌትነት አለው። በገዛ መሬታችን ዓድዋ ላይ ከሩቅ አገር የብስንና ባሕር አቋርጦ የመጣውን ጠላት የተዋጋንበት የእኛን ብቻ ነጻነት ለማስከበር ሳይሆን በዚያች ጊዜ የተንሰራፋውን የቅኝ አገዛዝ ስርዓት የገረሰስንበት ነው፡፡ ጣሊያን ወደአገራችን የመጣው ቅኝ አገዛዙን እኛም ላይ ለመጫን ነበር፡፡ ጣሊያን እኛ ዘንድ የመጣው ሌሎቹን አውሮፓውያኑን ማለትም ጀርመንን፣ ፈረንሳይን፣ እንግሊዝን ለመምሰልም ጭምር ነው፡፡

የዓድዋ ድል የመጣው አውሮፓውያኑ በዚያን ጊዜ ‹‹ካለእኛ ማንም ኃያል የለም፤ እኛ ነጮች ነን›› ባሉበት ጊዜ እና ብዙ የአፍሪካ አገሮችን በቁጥጥራቸው ስር ባደረጉበት ወቅት ነው፡፡ ይህ ድል ትልቅ ተምሳሌትነቱ ‹‹ቅኝ አገዛዝነት የዘላለም አይደለም›› የሚለውን መልዕክት ማስተላለፉ ነው፣ የዚህ እውነታ የመጨረሻውም የመጀመሪያውም ምዕራፍ የተጻፈበት ነው፡፡

ከዚያም በፊት ሆነ ከዚያ በኋላ ቅኝ አገዛዝን ለማጥፋት ብዙ ንቅናቄዎች ነበሩ፡፡ ዓድዋ ደግሞ ይበልጥ አበረታች ድል ሆናቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ዓድዋ በጣም ትልቅ ድል ነው፡፡ የወቅቱ አሸናፊነት እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም፡፡ ነገር ግን በወቅቱ በነበረው ርዕዮተ ዓለም የነጭ የበላይነትን ካየነው ከፍ ያለ ነው፡፡

አፄ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ ለመሸነፋቸው ምክንያቱ እንግሊዞች ያሏቸው ጠብመንጃ እርሳቸው ስለሌላቸው ነው፡፡ እነ ፊት አውራሪ ገብርዬ በዚያን ጊዜ የነበረው ጠብመንጃ እጃቸው ላይ ስለወደቀ ነው። አፄ ምኒልክ ይህንን ተረድተው የራሳቸውን ፋብሪካ አቋቁመው ባይሰሩትም፣ ከፈረንሳይ፣ ከጣሊያን፣ ከቱርክ፣ ከራሺያ መሳሪያም ጥይትም ገዝተዋል፡፡ ሁሉን ነገር አዘጋጅተው ኢትዮጵያውያኑ በመረጡት ቦታ ሔደው ተዋግተው ድል አድርገው ታሪክ ጽፈዋል፡፡ ከዚህ የተነሳም አፄ ምኒልክ በጣም የታወቁና የተደነቁ ንጉስ መሆናቸውን ዓለም ሁሉ ሊያውቀው ችሏል፡፡

በወቅቱ የተገኘው ድል ያኮራው አፍሪካውያኑን ብቻ ሳይሆን ጥቁር ሕዝቦችን ጨምሮ ብዙዎቹንም ነው፡፡ ካራቢያን ደሴቶች፣ በደቡብ አሜሪካ በቅኝ አገዛዝ ስር የነበሩት ሁሉ ብዙዎቹ ነጻነታቸውን ያገኙት ከዛ በኋላ ነው፡፡ እርግጥ ትግሉን ያካሔዱት ራሳቸው ናቸው፡፡ በጥቅሉ ግን ‹‹ኢትዮጵያ ካደረገችው እኛም እናደርገዋለን!›› በሚል ተበረታትተዋል፡፡

ለኛም የዓድዋ ድል በዓለም ላይ እውቅና አምጥቶልናል፡፡ ከዛ በፊት ግን ኢትዮጵያ የምትባለው አገር ዓለም የሚያውቃት በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ስሟ ከ40 ጊዜ በላይ በመጠቀሱ ነው፡፡ ይህንን ኢትዮጵያ በመባል የሚታወቀውን ስም ጥቁር አሜሪካውያኑና ካረቢያን ደሴት ውስጥ የነበሩ አፍሪካውያን ተጠቅመውበታል፤ በባርነት ቀንበር ስር በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያኒዝም (ኢትዮጵያዊነት) የሚባል እንቅስቃሴ በመፍጠር ነጻ ለመውጣት ትግል አድርገውበታል፡፡

በዚህም ተመስርተው የራሳቸውን ነጻ የሆነ ቤተክርስትያን ለመመስረት ችለዋል፡፡ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ከመታወቅ በተጨማሪ በዓድዋ ድል ለመታወቅ በቃ፡፡ ከዚህ የተነሳ የዓድዋ አስተሳሰብ ዓለም አቀፍ የሆነበት እድል ተፈጠረ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ያልወደቀችበት ምስጢሩ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** የእኛ ማሸነፍ እጅግ በጣም ብልህ እና አስተዋይ የሆኑ የአመራር ኃይሎች በመኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ አመራሮች ጦሩን አደራጅተውና ዘመቻውን አስተባብረው የመሩ ናቸው፡፡ በተለይ ጠላት ደግሞ ምን አይነት መሳሪያ እንደያዘ፣ ምን አይነት አጃቢ እንዳለውና መሰል የጦር ስትራቴጂያቸውን ሁሉ አጥንተው የመጨረሻ የውጊያ ስልት አውጥተው በመንቀሳቀሳቸውም ጭምር ነው። በወቅቱ ያወጡት ስትራቴጂ አገራችንን ባለማስደፈር የኢትዮጵያን ነጻነት ማስከበር ነው፡፡ የመጣውን ጠላት እንዴት ልንመልሰው እንችላለን በሚል ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ናቸው፡፡

በወቅቱ አፄ ምኒልክ፣ ወራሪውን ጣሊያን ለመዋጋት የሄዱት በአገር ውስጥ የነበረውን ችግር ከፈቱ በኋላ ነው፡፡ በወቅቱ የበመጨረሻ አስቸግሯቸው የነበሩት የወላይታው ንጉስ ካዎ ጦና ናቸው፡፡ ከእርሳቸው ጋር ያደረጉት ትግል ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ በደጅ ያለው የጣሊያን ወራሪ አንድ ሁለት ሶስት ቦታ ገብቶ ይዞ የነበረ ቢሆንም በኋላ ላይ ኢትዮጵያ በማበሯ ሊለቅ ችሏል፡፡

በቅድመ ዓድዋ ወቅት የአገር መስፋፋት ነበር። በዚያን ወቅት ግብር እቀበላለሁ ያለ በአገዛዙ ስርዓት ውስጥ ገብቶ አገዛዙ እንዲቀጥል አደረገ፡፡ አሻፈረኝ ያለው ደግሞ ጦርነት ገጥመው ያስገብሩት ነበር፡፡ አፄ ምኒልክ፣ ወደ ዓድዋ የዘመቱት ተስማምቶ የገባውን መግባቱን ካረጋገጡ በኋላ “ድንበር ጠብቅ” ብለው ነበር፡፡

ከዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ ዋናው የማሸነፍ ምስጢሯ፤ የመናበብ ስራ በመኖሩ ነው፡፡ አፄ ምኒልክ አንድ ያደረጉት ነገር ቢኖር ሁሉን በውይይት ማስኬድ በመቻላቸው ነው፡፡ እርሳቸው ኢትዮጵያን ብቻቸውን አልገዙም፡፡ አፄ ምኒልክ የገዙት ከባለሟሎቻቸው ጋር በመሆን ነው፤ በተለይም ከእቴጌ ጣይቱ ጋር በመሆን ነው። ሰውን በክተት አዋጅ ከኢትዮጵያ ሊያሰባስቡ የቻሉትም በጥበብ ነው፡፡

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ስለኢትዮጵያዊነቱ የተገነዘበው ነገር አለ፡፡ ከቋንቋው፣ ከኃይማኖቱ እና ከዘሩ አልፎ የተገነዘበው ትልቅ ነገር አለ፡፡ አፄ ምኒልክም፣ የክተት አዋጅ ሲያውጁ ለሁሉም በሚገባ ቋንቋ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያኑም ያንን አዋጅ ተቀብለው ገሚሱ ቤተሰቡን በሙሉ ይዞ፣ ገሚሱ ደግሞ ስንቁን ይዞ፣ ሌላው ደግሞ ያለ የሌለ ንብረቱን ጭምር ይዞ በመዝመቱ ድሉን ሊቀዳጅ ችሏል፡፡ ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያውያን ሲተባበሩና አንድ ሲሆኑ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በዓድዋ የታየ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትናንት ቅኝ ገዥዎችን በብርቱ ክንዷና ጥበቧ ያሸነፈች አገር፤ አሁን ላይ ድህነት እና ኋላቀርነትን ማሸነፍ ለምን አቃታት? ይህንን ችግር ለመሻገር መፍትሔው ምን መሆን አለበት?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** ይህ ዋናውና አንገብጋቢው ጥያቄ ነው ብዬ አስባለሁ። የዓድዋን ጦርነት ድል ማድረግ የተቻለው ጌታውም ሎሌውም፣ ባላባትም አሽከርም አንድ ሆነው ተዋግተው ነው፡፡ ዓድዋ ላይ የተደረገው ድርጊት ኢትዮጵያን ቀይሯታል፡፡ ኢትዮጵያን የቀየረውና ድል የነሳው በተደረገው መስዋዕትነት ነው፡፡ መስዋዕት የሆነው እንዳልኩሽ አሽከሩም ሎሌውም ነውና አሽከሩም በአሽከርነቱ ሎሌውም በሎሌነቱ ሊቀጥል አይችልም፡፡

ድሉን ካገኘን በኋላ ግን ፈጣን በሆነ ሁኔታ ወደፊት መራመድ ነበረብን፡፡ አፄ ምኒልክም ሰብሰብ አሉ፤ መኳንንቱን በያሉበት ሔደው እንዲገዙ አደረጉ፡፡ የጭሰኝነት ስርዓቱም ይቀጥሉ አሉ፡፡ ይህ በመሆኑ አካሄዱ ወደኋላ ጎተተን። ”የነብር ጭራ አይዙም፤ ከያዙም አይለቁም” በሚል መንፈስ ወደፊት ቀጥለው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ልክ እንደ ደቡብ ኮሪያ፣ ማሊዥያ፣ እንደብራዚልና መሰል አገሮች እንሆን ነበር፡፡ ይህ የእኔ ግምት ነው፡፡

በመቀጠል ኢትዮጵያን የመሩ አፄ ኃይለስላሴን ጨምሮ ሌሎቹም መሪዎች እንደ አፄ ምኒልክ አይነት የየራሳቸው የሰሩት ስራ ይኑር እንጂ መሰረታዊ ለውጥ አላመጡም፡፡ ደርግም መጣና መሬት ላራሹ አለ፡፡ ይሁንና መሬት ላራሹ ተብሎ፤ መሬት የመንግስት ሆኖ አገኘነው። መሬት የመንግስት ካድሬዎች መጠቀሚያ ሆነ እንጂ አራሹ የመሬት ባለቤት ሆኗል ብለን መናገር አንደፍርም። በመሆኑም በኢኮኖሚ እንዳናድግ የጎተቱን እነዚህና መሰል ምክንያቶች ናቸው፡፡

መንግስት፤ እንደ አንድ አገረ መንግስት አንድ የሆነ ደረጃ ላይ ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት። አደገኛ የሆኑ ርምጃዎችንም ሆነ ውሳኔዎችን ማሳለፍ መቻል አለበት፡፡ በአሁኑ ወቅት በለጸጉ የተባሉ አገራት ያንን በማድረጋቸው ነው ዛሬ ላሉበት ደረጃ የበቁበት፡፡

ጣሊያን እንኳ ከዓድዋ ሽንፈት ተምራ 40 ዓመት የጦር መሳሪያዎችን ራሷ ማምረት ጀመረች። አውሮፕላኑን፣ መትረየሱንም ሆነ መድፉን፣ ታንኩንና ሌላውንም የመሳሪያ አይነት አዘጋጅታ በምንም አይነት እኛ እንጂ ኢትዮጵያ ማሸነፍ የለባትም ብላ ለሁለተኛ ጊዜ ኃይሏን አስተባብራ መጥታለች ፡፡

እርግጥ ነው፤ አፄ ምኒልክም ሆኑ አፄ ኃይለስላሴ ብዙ አስገራሚ ስራዎችን ሰርተዋል፡፡ ይሁንና አፄ ኃይለስላሴ ለረጅም ዘመን የባላባት ስርዓት አስከባሪ ነበሩ፡፡ በወቅቱ የነበሩ ተማሪዎች ስርዓቱ መቀጠል የለበትም በሚል ተነሳሽነቱን ወስደው ስርዓቱ እንዲፍረከረክ አደረጉ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታዩ ግን መሪዎቻችን ቁጥብ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡

ወደመፍትሔው ሲመጣ የመጀመሪያው ዓድዋን ያሸነፍነው ለምንድን ነው? ከተባለ ጥሩ አመራር ስለነበረን ነው፡፡ ሕዝቡ ደግሞ የአገር ፍቅር ስለነበረው ነው፡፡ ሕዝቡ አገር ምን ማለት ነው? የሚለውን ተገንዝቧል፡፡ በዚያን ጊዜ አብዛኞቹ የዘመቱትና ሕይወታቸውን የሰውት ደግሞ በእድሜ ደረጃ ሲሰላ ከ18 እስከ 30 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ናቸው። እነዚህም ወጣቶች አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ ነጋዴዎች እና በዛ የወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ

**ወደ ገጽ 17 ዞሯል**


ፎቶ - ሐዲስ አብርሃ

# «ታሪክን ጠለቅ አድርጎ ለተገነዘበ...

ከ16ኛው ገጽ የዞረ



ያሉ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት በዚህ የእድሜ ክልል ውስጥ ያለው ወጣቱ ኃይል በምን አይነት ሁኔታ ውስጥ ነው ያለው? ብሎ መጠየቁ አግባብ ነው፡፡ ምላሹ በጣም ቀላል ነው፤ ምክንያቱም እርስ በእርሳችን እየተናቆርን ነው፡፡ እሱ ደግሞ የሚያሳየን በዚያን ጊዜ 18 ዓመት እድሜ ላይ ያለው ወገን የዓድዋ የክተት አዋጅ ሲታወጅ እንዴት መረዳቱን አገኘ? ከምንም በላይ አገር መቅደም አለባት እንዴት አለ? በዚያ እድሜ ክልል ውስጥ ያለው ያ ሰው ለአገሬ ሉዓላዊነት እሰዋለሁ ብሎ ሲወስን ምን አይነት ብልህነት እና አስተዋይነት ነው? ብሎ ለመጠየቅ የሚያስገድድ ነው፡፡ ምን አይነት የአገር ፍቅር ነው? ማለትም ግድ ይላል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያጣነው ያንን ነው፡፡

አሁን ላይ የሌለን ነገር ቢኖር እሱ ነው፡፡ የአገር ፍቅር ምን ማለት ነው? የሚለው ግንዛቤ ከሌለንና የአገር ፍቅር ግድ ብሏቸው መስዋዕት ከከፈሉ ወገኖች ታሪክ መረዳት ካልቻልን አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ዝም ብለን በአፋችን አንድነት አንድነት ብንል የምንመኘው አንድነት ሊመጣ አይችልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በአብሮነት መቆም ለአገር እድገት ዋና መሰረት ነው፤ በዓድዋ ዘመን የነበረውን አንድነት ወደአሁኑ ትውልድ በማምጣት ለአገር እድገት እንዴት መጠቀም ይቻላል? ከዚህ አኳያ ለወጣቱ ምን ይላሉ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** በዓድዋ ዘመን የነበሩ ሰዎች ከፍተኛ ትዕግስት ያላቸው ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡ በዚያን ዘመን ከጥቅምት አንስተው እስከ የካቲት ወር ድረስ በባዶ እግራቸው ተጉዘው፣ የየራሳቸውን ስንቅ ተሸክመው፣ የመዋጊያ ጠብመንጃ አንግበው ሲንቀሳቀሱ ነበር፡፡

በተለይ ሴቶቹ ደግሞ የማብሰያ ቁሳቁስ ይዘው በቀን ስምንት፣ ስምንት ሰዓት ይጓዙ የነበሩ ናቸው። መጓዝ ብቻ ሳይሆን በየደረሱበት ምግብ ማሰናዳቱ ኃላፊነታቸውም ነበር፡፡ አካባቢውን ለቅቀው ሲነሱ እንዲሁ ሁሉንም ቁስ ለረጅም ሰዓት ተሸክመው ይሔዱ ነበር፡፡ ይህን ሁሉ ተግባር ለመፈጸም ከፍተኛ ትዕግስትን ይጠይቃል፡፡

በአሁኑ ወቅት ስናጤን ደግሞ አሁን ያለነው ትውልዶች በትንሽ ነገር ብዙ ጥቅምን ማግኘት የምንሻ ነን፡፡ የአንድ አገር ሕዝብ ሆነን አንዳችን አንዳችንን የምናየው በጠላትነት ነው፡፡ አንዳችን አንዳችንን ለማጥፋት የምንጠቀምበት ስልት ከዚህ ቀደም ታሪካችንን ውስጥ የሌለ ነው፡፡

እኔ ሳስተውል አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ የግል ጥቅሙን አሳዳጅ መብዛቱ ነው። ይህ በግለሰብ ሆነ በቡድን ደረጃ የሚስተዋል ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት እየጎዱን ያሉት እነዚህ ናቸው፡፡ ስለዚህ መረባረብ ያለብን እዚህ ላይ ይመስለኛል፡፡ አሁን አሁን አዲስ ያመጣነው ነገር ቢኖር በብሔር ራስንና ማንነትን መከለል ነው፣ በመካከላችንም የማይገፋ ግድግዳ እየገነባን ነው ማለት ነው፡፡ በጥቅሉ ግን እኔ ሳስበው የጥቅም ፍላጎት ታሪክን ወደማዛባት እያደረሰን እርስ በእርስ እንዳንግባባ እያደረገን ነው፡፡ ጥቅም ፈላጊዎች ደግሞ ሕዝቡን ስሜታዊ እንዲሆን የሚገፉፉ ናቸው፡፡

ሌላው ወጣቱ የሚማረው ትምህርትም መጤን አለበት ባይ ነኝ፡፡ የእኛ ትምህርት ባሕል ተኮር አይደለም፡፡ የራሳችን ታሪክ ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ ሁል ጊዜ ገልባጮች ነን፡፡ ስንገለብጥ ደግሞ በስርዓት አንገለብጥም። ቋንቋም ስንማር በስርዓት አንማረውም፡፡ የራሳችንንም በስርዓት አንይዘውም፡፡ ስለዚህ የውጭ አገር ዜጎች እየመጡ እየተጫወቱብን ለመሔድ ይሞክራሉ፡፡ እዳ በእዳም የሆንነው ለዚያ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡

ችግሮችን ስርዓት ባለው መንገድና ትዕግስት ባለው መንገድ መፍታት ይጠበቅብናል፡፡ ሕዝብ ተኮር የሆነ ፖሊሲ እያወጣን ፤ ሕዝቡ ተሳታፊ እንዲሆን እያደረግን መንቀሳቀስ አለብን፡፡ ዝም ብሎ ስራ ተሰርቶ ሕዝብ መጥቶ እንዲያጨበጭብ ማድረጉ በቂ አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ያንን ሁኔታ ማስተካከል ይኖርብናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትውልዱ የዓድዋን ማንነት እንዲላበስ ምን ማድረግ ይኖርብናል ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** እኛ/ትውልዱ የዓድዋ ማንነት መላበስ ያቃተው ወይም የዓድዋ ልጆች መሆን ያቃተው በሁለት ምክንያት ነው፡፡ አንደኛው የዓድዋን ድል እንደ ባለቤትነት አለመውሰድ፣ አለመያዝ እና አለመቀበል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ከአንድነት ይልቅ የእኔነት መንፈስ በመጉላቱ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በዓድዋ ጊዜ አንድነትና ኅብረት እንደነበረው ዛሬ ላይ ያለመታየቱ ምስጢር የትብብር አለመኖር ነው፡፡ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የውጭ ጠላት መጣ፤ ያንን የውጭ ጠላት ደግሞ "አገሬን አላስደፍርም" በሚል የክተት አዋጅ ታወጀ፤ በዚያን ሰዓት ከሁሉም አቅጣጫ በመምጣት ጠላትን ድል ማድረግ ተቻለ፡፡ በዚያ የአብሮነት ድርጊታቸውም ኢትዮጵያውያን የአንድነት መንፈስ እንዳላቸው ማስመስከር ተቻለ፡፡

አንድነትላለመኖሩዋናችግርእርስበእርሳችን ያለመስማማታችንና ያለመግባባታችን ጭምር ነው፡፡ የእርስ በእርስ ጦርነት ላይ መሰማራታችን እና ታሪካችን በአግባቡ ያለመገንዘባችን ነው። ታሪካችንን በአግባቡ ብንገነዘብ ኖሮ ቶሎ ወደእርቅና ወደሰላም ብሎም ወደመግባባት እንመጣ ነበር፡፡ ይሁንና በአሁኑ ወቅት እያየን ያለነው ሽኩቻ ነው፤ ይህ ሽኩቻ ደግሞ የግል ጥቅም ከማሳደድ ፍላጎት የመነጨ እንጂ የአገርን ጥቅም የሚያስጠብቅ አይደለም፡፡፡

መፍትሔው ሊሆን የሚችለው፤ የቀድሞ ታሪካችንን ወጣቱ በአግባቡ ይረዳው ዘንድ ግንዛቤ ማስያዝ ነው፡፡ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ድል ያደረጉት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ናቸው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከሁሉም

**ይህ ድል ትልቅ ተምሳሌትነቱ «ቅኝ አገዛዝነት የዘላለም አይደለም» የሚለውን መልዕክት ማስተላለፉ ነው፣ የዚህ እውነታ የመጨረሻውም የመጀመሪያውም ምዕራፍ የተጻፈበት ነው**

አቅጣጫ የመጡና የተለያየ ብሔር እና ኃይማኖት ያላቸው ናቸው፣ የተዋደቁትም ለጋራ አገራቸው ሉዓላዊነት ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነታቸውንም በሚገባ የተገነዘቡ ዜጎች ናቸው፡፡ በዚያን ጊዜ የነበረው የኢትዮጵያዊነት ግንዛቤ ዛሬ ላይ ግን የተሸረሸረ ሆኗል። ይህ ጉድለት በመሆኑ መሟላት አለበት።

በሌላ በኩል ከመንግስት የሚጠበቀው የአገር ፍቅርን የሚቀሰቅስ፣ የሚያፈልቅና የሚያመነጭ አቅጣጫን ሁል ጊዜ መስጠት መቻል ነው፡፡ በተለይ ዜጋው ከእርስ በእርስ ጦርነት የሚወጣበትን መንገድ ማበጀት የግድ ነው፡፡ ይህንን የእርስ በእርስ ግጭት አካሔድ ማስቆም ከመንግስት የሚጠበቅ ነው። እንዲህ ሲባል ጉዳዩ የመንግስት ብቻ ነው ማለት ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለሰላም መስፈን ማሰብ እንዳለበት አለበት፡፡

ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ናት፤ ለሁሉም የምትበቃ ናት፡፡ በመካከል ልዩነት የሚኖር ከሆነ ያንን ልዩነት በሰላማዊ መንገድ መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ይህም በመወያየትና በመነጋገር ሊከናወን የሚችል ነው፡፡ ልዩነትን በውይይት ለመፍታት መሞከርም ትልቅነት ነው፡፡

አንድነታችን በአንድም ይሁን በሌላ መጠበቁ አይቀሬ ነው፡፡ ሰላም፣ ዋጋ አስከፍሎን ከመምጣቱ በፊት ግን ከወዲሁ አንድነታችንን ብንጠብቅ ተመራጭ ነው፡፡ ያንን መስዋዕትነት ከመክፈላችን በፊት እኛው ራሳችን ለአንድነታችንም ሆነ ለሰላማችን ዘብ መቆም አለብን፡፡ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በሰላም አገሩን ለመገንባት እና አገሩን ወደተሻለ ደረጃ ለማድረስ የሚያልምና የሚጥር ነው፡፡ ለዚህ የታሪክ ምስክርነትም አለ፡፡ ሁሉም ጨለማ ነው ብሎ ተስፋ መቁረጥ አያስፈልግም፡፡

መልካሙ ነገር እንዲመጣ እና ሰላም እንዲሰፍን ዳር ቆሞ መጠበቅ ግን አያዋጣም፡፡ ሁሉም የየበኩሉን ድርሻ መውሰድ ይኖርበታል። ሁሉም ለሰላም ያለውን አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት፡፡ አንድነቱና ኅብረቱ ይመጣ ዘንድም ኃላፊነት ወስዶ የድርሻን መወጣት ያስፈልጋል፡፡

ዜጋው፣ በጦርነት የሚመጣ ሰላም እና አንድነት እንደማይኖር መረዳት ይጠበቅበታል። ምክንያቱም ጦርነት መልሶ ቁርሾ ውስጥ የሚከትና ቂም የሚያስይዝ ነው፡፡ ዛሬም ድረስ እየበጠበጠን ያለው ከ30 እና ከ40 ዓመት በፊት የተቋጠሩ ቂሞች ናቸው፤ እዚህ ላይ ብልሆች ልንሆን ይገባል፡፡ ለዚህ ሁሉ ግን ትዕግስት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዓድዋ እና ፓንአፍሪካ ኒዝምን የሚያመሳስላቸው ምንድን ነው ይላሉ?**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** ዋናው ቁም ነገር ሁለቱም በታሪክ የተሳሰሩ መሆናቸው ነው፡፡ ዋናው ጠቃሚ የሆነው ጥያቄ ለመተሳሰራቸው ምን ማስረጃ አለ? የሚለው ነው፡፡ ዓድዋ የተካሔደው በእኛ በየካቲት ወር ሲሆን፣ በፈረፈንጆች ስናሰላው ደግሞ ያኔ መጋቢት ይገባል፡፡ በእኛ 1888 ዓ.ም በእነርሱ ደግሞ እኤአ 1896 ነው፡፡ እርሱ በተካሔደ በአራተኛ ዓመት እኤአ በ1900 የመጀመሪያ ፓንአፍሪካን ኮንፈረንስ ለንደን ላይ ተካሂዷል። ይህ ኮንፈረንስ ከዓድዋ ድል ጋር ምን ምን ግንኙነት አለው? ይበሉ እንጂ ግንኙነት አለው።

የፓንአፍሪካ እንቅስቃሴ ጥልቀት ሊኖረው የቻለው እና ተፋፍሞ እንደ አፍሪካ አንድነት አይነት ድርጅት ሊፈጠር የቻለው በተለይ ኢትዮጵያ ከ1928 ዓ.ም እስከ 1935 ዓ.ም የጣሊያን ወረራ በተካሄደበት ወቅት ወረራውን በመቃወም የተነሱበትና ከኢትዮጵም ጋር የነበራቸው ቅርበት በጣም የዳበረበት ጊዜ ነው፡ ፡ በዚያን ጊዜ ፓንአፍሪካኒዝም በጣም ጠንካራ የሆነበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሁል ጊዜ ተባባሪያችን ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር) ስለሰጡን መረጃ ከልቤ ሳመሰግንዎ እወዳለሁ፡፡**

**ተባባሪ ፕሮፌሰር አየለ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# "ዓድዋ ስለ ፍትሕና ነፃነት
# የተደረገ የሰው ልጆች ሁሉ ድል ነው"

- መምህር በቃሉ ዋቺሶ
የፖለቲካል ሳይንስ መምህር

እፀገነት አክሊሉ

ሀገራችን በበርካታ ድልና የአርበኝነት ታሪኮች በዓለም መድረክ በሰፊው ትታወቃለች። በዚህም ነፃነቷንና ክብሯን በማስጠበቅ ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም ቀንዲል ነች። ዓለም በቅኝ ገዢዎች ፉክክር በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ በገባችበት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ነፃነቷን አስከብራ የኖረች ብቸኛ የአፍሪካ ሀገር መሆኗ በጉልህ ይነሳል። የውጭ ወራሪ ኃይል አገሪቷን ለመድፈር በመጣ ቁጥር ሁሉም ዜጋ ከዳር እስከዳር በመነቃነቅ በአንድነትና በአብሮነት በመሰለፍ ጠላትን አሳፍሮ መልሷል።

የታሪክ ምሑራን ዓድዋን "የኢትዮጵያውያን አንድነት መገለጫ፣ የመላው ጥቁር ሕዝቦችና የነፃነት ታጋዮች የድል ታሪክ ነው" ይሉታል። የዓድዋ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ መላው አፍሪካውያን ለነፃነታቸው እንዲተጉና አንድነታቸውን እንዲያጠናከሩ መሠረት የሆነ ታላቅ ድል ስለመሆኑም ይናገራሉ። የጥቁር ሕዝቦች የአሸናፊነት ማሳያም አድርገውም ይወስዱታል።

እኤአ በ1885 ጀርመን አገር በተካሄደው የበርሊን ኮንፈረንስ አውሮፓውያን መላ አፍሪካን በካርታ ላይ የተከፋፈሉትን በተግባር መሬት ላይ ለመቀራመት ጦራቸውን ሰብቀው፣ ስንቃቸውን ጭነውና ትጥቃቸውን አጥብቀው ያካሄዱት ዘመቻና የወረራ ጉዞ የተገታባት ዓድዋ እና እለቷ ዛሬ ድረስ በተገፉ ሕዝቦች ልብ ታትማ በአዕምሮ ውስጥ ተቀርጻ ትኖራለች።

እለቱን አስመልክቶ «ዓድዋን ለዘላቂ ልማትና ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ» በሚል በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ በተዘጋጀ የውይይት መድረክ ላይ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡትን የዩኒቨርስቲው ማኅበራዊ ሳይንስና ሥነ ሰብ ኮሌጅ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር በቃሉ ዋቺሶ ጋር ቆይታን አድርገናል።




**አዲስ ዘመን ፦ ዓድዋ ለእኛ ምንድነው? ዛሬስ ትውልዱ ላይ እንዴት ነው ሲንጸባረቅ የሚገባው?**

**መምህር በቃሉ፦** በዚህ ጉዳይ ሁለት አይነት ብዥታዎች አሉ። አንዱ መዘከር ወይም ደግሞ የትላንትን ብቻ አውስቶ ማለፍ ሲሆን ሁለተኛው ዓድዋ ዛሬ (አሁን) እንደሆነ አድርጎ ማሰብ ነው። በመሆኑም ትላንት በአያት ቅድመ አያቶቻችን የተደረገው ድርጊት፣ የተከፈለው መስዋዕትነት እና የተገኘው ድል ዛሬ ደግሞ ይህ ትውልድ ምናልባት በደም ባይሆንም፤ ተመሳሳይ መስዋዕትነት የሚከፍልበትና የራሱን አሻራ የሚያስቀምጥበት ሊሆን ይገባል።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ትውልዱ አያት ቅድመአያቶቹ በደማቸው አኩሪ ታሪክ በመሥራት አንገቱን ቀና አድርጎ የሚሄድበትን ምቹ ሁኔታ ፈጥረውለት አልፈዋል፤ ዛሬ ይህንን በደም የተገኘ ዋጋ በላብ ማጽናት ከዚህ ትውልድ የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? ከተባለ ዛሬም በዚህ ትውልድ አዕምሮ ውስጥ ዓድዋን መፍጠር እና "እኔ የዓድዋ ትውልድ ነኝ" ብሎ እንዲያምን ማድረግ ያስፈልጋል።

አሁን በዚህ ወቅት የመደመር ትውልድ ይባላል፡፡ አዎ! ዓድዋ ራሱ እኮ ይደምራል፡፡ በመሆኑም ትውልዱ ትላንትና ከፉም ይሁን ደግ የተደረገው ነገር እኔንም ይገልጸኛል፤ በአያቶቼ አጥንትና ደም ውስጥ ነበርኩ ዛሬ እዚህ ደርሼ ሀገሬን እንድረከብ እነሱ መስዋዕትነት ከፍለውልኛል ብሎ ከመዘከር በላይ በሆነ መልኩ ማክበር ያስፈልጋል።

በመሆኑም ዓድዋን ስናስብ ዝም ብለን ተጨባብጠን አልያም ዘምረን ጀግኖችን አንስተንና ሐውልት አቁመንላቸው ብቻ የምናልፈው ሳይሆን ዛሬ ላይ ቆመን ዓድዋን እያሰብን ለነገ ደግሞ ትዝታ የሚሆን ነገርን ለማሳረፍ ወገብ የሚያጎብጥ አይነት አደራ የምንቀበልበትም ነው።

ሀገራችን ከሰጠችን በላይ መስጠት አለብን፤ ግን ደግሞ እንዴት ባለው መልኩ የሚለውንም በማየት በእናት ለምንመስላት ሀገራችን የሚታይ ሥራንም አስቀምጠን ለመሄድ መዘጋጀት ያለብን ዓድዋን ተንተርሰን ሊሆን ይገባል።

ዛሬ ላይ ያለው ትውልድ በቀደሙት አባት እናቶቹ ቦታ ራሱን አስቀምጦ እራሱን እንዲጠይቅ ያስፈልጋል። በመሆኑም ትውልዱ አሁንም ቢሆን ከጦርነት የጸዳን ከስጋት ነፃ የሆንን ባለመሆናችን ከልማቱ ዝግጁነት ጎን ለጎን ለተንኳሾች ተገቢ ምላሽን ለመስጠትም የተዘጋጀ ሊሆን ይገባል። በዓድዋ የፈሰሰ ደም አሁንም ድረስ ትኩስ ነው፤ ይህ ዓይነቱ መስዋዕትነት የሚጸናው ደግሞ አሁን ላይ በምንፈጽመው ገድል ነው።

**አዲስ ዘመን፦ በዚያ ትውልድ ውስጥ ሆኖ ራሱን የሚያይ ትውልድ እንዲፈጠርስ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጀምሮ ቤተሰብና ሌላውም ምን ዓይነት ተግባራትን ማከናወን አለባቸው ይላሉ?**

**መምህር በቃሉ፦** ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ዓድዋን አስመልክቶ ያዘጋጀውን አይነት መድረኮች ዓድዋንና መሰል ድሎች ፋይዳቸው ምንድ ነው? የሚለውን ለትውልዱ ለማሳየት ጥሩ መንገድ ነው። በተለይም ለእኔ ዓድዋ በነፃነት ተጀምሮ በነፃነት የተጠናቀቀ ከመሆኑ አንጻር፤ ድልና ነፃነቱን በማጉላት እንዲሁም ትውልዱ ተገቢና ትክክለኛ መረጃን እንዲያገኝ ማድረግ ይገባል።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ጥሩ ጥሩውን ብቻ ሳይሆን የተቆሳሰልንባቸውንም ቦታዎች በማሳየት ለሀገር ተብሎ የተከፈለን መስዋዕትነት በመናገር ትውልዱ አንገቱን ቀና እድርጎ እንዲሄድ፤ ይህ ታሪክ የተሠራው ለእኔም ነው ብሎ እንዲያስብ ማስቻል ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው።

ይህንን ታሪክ በትውልዱ ልብ ውስጥ ለማስረፅ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ትልቅ ሥራ ይጠበቅባቸዋል። በነገራችን ላይ ተማሪዎቻችን በምን መልኩ አስረድተን ምን ዓይነት ግንዛቤ ነው የምናስጨብጣቸው? የሚለው በጣም ሊታይ ይገባል፤ በዚህም መጀመሪያ ከመናገራችን በፊት ታሪኩን በአግባቡ መረዳት ከዛም የእኔ ታሪክ ነው ብሎ ወደውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል። ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ግን በራሳችን ታሪክ የተዋረደን፣ የምንሸማቀቅና የምንፈራ ትውልዶች እንሆናለን ።

**አዲስ ዘመን፦ የዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች ድል ነው ይባላል ? በተግባር ግን ይህን ድል ከእኛ አልፈን ሌሎች እንዲደምቁበት ለማድረግ ምን ቢሠራ መልካም ነው ይላሉ?**

**መምህር በቃሉ፦** እኔ ዓድዋ የጥቁሮች ድል በመባሉ ራሱ ቅሬታ አለኝ፤ ለምን ብትለኝ በዛ ጦርነት ላይ ኢትዮጵያውያን ግንባር ቀደሙን ትግል ያድርጉ እንጂ ወረራውን የሚቃወሙ የተለያዩ ሀገራት ዜጎች(ነጮች) ተሳትፎ አድርገዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ድሉ የጥቁር ሕዝቦች ካልን እነዛን ለእኛ ሲሉ ዋጋ የከፈሉ የሞቱ የቆሰሉ ነጮችን ክብር ማሳነስ አውቅናም መንፈግ ይሆንብኛል፤ በመሆኑም ዓድዋ የጥቁሮች ድል ነው የሚለው ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ፍትሕና ነፃነት የተደረገ የሰው ልጆች ሁሉ ድል ነው ብንለው የሚሻል ይመስለኛል።

ዓድዋ የማይቻል የሚመስል ነገር ሁሉ ተችሎ የታየበት ያለመደፈር፣ በድልና በነፃነት ራስን አክብሮ ሌሎችንም አክብሮ የመኖር ማሳያ ስለሆነ ከዓለም አቀፍ ድሎች ጋር አብሮ ሊነሳ የሚገባው፣ በሆሊውድና በሌሎች ፊልሞች ሊታይ የሚገባው ነው።

**አዲስ ዘመን ፦ ተዘካሪነቱንስ በዛ ልክ እንዲሆን ለማድረግ እንደ ዜጋ ምን መሥራት አለብን ?**

**መምህር በቃሉ፦** ዓድዋን ለመዘከር ተገናኝቶ አንድና ሁለት ሰዓት ተወያይቶ መሄድ ብቻ በቂ አይደለም። ይህ ትውልድ ወገብ የሚያጎብጥ የቤት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ማወቅ ይገባል። በመሆኑም እንደ አገር ትውልዱ ላይ የተጫኑ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም ዓድዋ ደግሞ ከዛ መካከል ተመዞ መውጣት የሚችል በጣም ግዙፍ ድላችን በመሆኑ ይህንን ማሻገር ይገባል። ዓድዋ የማያልቅ የተከማቸ ሀብታችን እንደመሆኑ በየቀኑ እያወጣንና እየመነዘርን ራሳችንን ለማወቅ ለመገንባት አልፎ ተርፎም ትውልድንና ሀገርን ለመገንባት መጠቀም ያስፈልጋል።

ከዝክር ባለፈ ትውልዱ በምን መልክ ይዞት ለቀጣዩ ትውልድ ያሳልፈው? የሚለውን ፖለቲካ፣ ዘር፣ ቀለም፣ ሃይማኖት ሳይለይ ተጨማሪ ፋይዳው ላይ መስራት ይገባል። ይህም መከባበራችንን፣ ነፃነታችንን እና ወንድማማችነታችንን ለዓለም ለማሳየትና ለማሳወቅ ትልቅ መንገድ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ አሁን ላይ እኔ የዓድዋ ነኝ ከማለት ይልቅ የልዩነት ትርክቶች እየሰፉ ነው፤ ይህን ከማረም አንጻር ምን መሠራት ይኖርበታል ይላሉ?**

**መምህር በቃሉ፦** የዓድዋ ታሪክ የዘመናት ርቀቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ዛሬም ላይ እንዳለው ሁኔታ የፖለቲካዊና ሌሎች ዝንባሌዎቻችንን ተንትነን፣ ይህ ብሔራዊ ማንነታችን ነው ብሎ መቀበል ያስፈልጋል። ዜጎች ምንም ይሁን ምን ሁልጊዜ በሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ አንድ ሆነን ድሉ የእኔ ነው ብለን መቀበል ይጠበቅብናል።

አንድ ሰው ዓድዋ የእኔ ነው ብሎ ባሰበና በተነሳ መጠን በተሠማራበት መስክ ላይ ትውልዱን በመቅረጽና በማነጽ በኩል የበኩሉን መወጣት ይችላል። ትውልዱ ብዙ የሚጫኑት ዘመን አመጣሽ ችግሮች ስላሉበት አሁን ላይ አጎንብሶ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ትንሽ ብቻ ሥራ ከተሠራበት ታሪኩን በማወቅና በመጠበቅ በኩል ትልቅ ሚና ሊወጣ ስለሚችል በዚህ ላይ ሁላችንም ልንሠራ ይገባል።

**አዲስ ዘመን ፦ ስለነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ።**


**መምህር በቃሉ፦**-እኔም አመሰግናለሁ፡፡

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# «አፍሪካ ከአውሮፓ ቅኝ ግዛት ነፃ እንድትወጣ የዓድዋ ድል ትልቁን ሚና ተጫውቷል»

-ፀጋዬ ዘለቀ (ዶ/ር)
በጅማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል
መምህር እና ተመራማሪ

ምሕረት ሞገስ



**በወቅቱ ሰሜን ሸዋ ክፍለ ሀገር ተብሎ በሚጠራው ጎጃም መስመር ጉስሴ በሚባል ቦታ የተወለዱ ሲሆን፤ ለከተማ ቅርብ አካባቢ ይኖሩ ስለነበር እንደአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ትምህርት ቤት ለመድረስ ብዙ ርቀት መጓዝ አይጠበቅባቸውም ነበር፡፡ በግምት ከአንድ ኪሎ ሜትር ብዙም የማይርቅ መንገድ እየተጓዙ የአንደኛ እና መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለዋል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ከተወለዱበት ቦታ በ12 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው ፍቼ በማቅናት፤ በፍቼ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረዋል፡፡ አጎታቸው በቅርብ ርቀት በዛው በፍቼ ከተማ ስለነበሩ፤ ብዙም ሳይቸገሩ የመልቀቂያ ፈተና ለመውሰድ በቅተዋል፡፡**

**በሁለተኛ ደረጃ ሲማሩ ከተፈጥሮ ሳይንስ ቀይረው ማህበራዊ ሳይንስ የተማሩ ሲሆን፤ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ቡኪፒንግ ስለተማሩ ኢኮኖሚክስ የመማር ከፍተኛ ፍላጎት ነበራቸው፡፡ ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት አጠናቀው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ሲቀላቀሉ ምኞታቸው የነበረውን ኢኮኖሚክስ መማራቸውን ትተው፤ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ እና የሶስተኛ ዲግሪያቸውን በታሪክ ላይ አድርገዋል።**

**የዛሬው የዘመን እንግዳችን ፀጋዬ ዘለቀ (ዶ/ር) ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ የሽግግር መንግሥቱ ጊዜ በመሆኑ ኢኮኖሚክስ ብዙም የሥራ ዕድል የለውም የሚል ወሬ ሰሙ፡፡ ሆኖም ለአንድ ዓመት የዩኒቨርሲቲውን የመጀመሪያ የጋራ ኮርሶች ሲማሩ፤ ኦኮኖሚክስን እንደሚማሩ እርግጠኛ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ግርማ አስፋው የሚባሉ መምህር ስለኢኮኖሚክስ ትምህርት ጥሩነት ተናግረው፤ ነገር ግን ሥራ እንደማይገኝበት፤ አካውንቲንግ የተወሰነ ሥራ እንዳለው መግለፃቸውን ተከትሉ የዛሬው እንግዳችን ሌላ ዘርፍ ለመምረጥ አሰቡ፡፡**

**በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያሉ የታሪክ መምህር ሲያስተምራቸው በጣም ደስ ይላቸው ስለነበር ወደ ታሪክ ትምህርት አዘነበሉ፡፡ በእርግጥም ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲወጡ፤ በታሪክ መምህርነት ሥራ ማግኘት አይከብድም ነበር፡፡ እንዲያውም በአንድ ዓመት ውስጥ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አንድ መምህራን ማሠልጠኛ ተፈልገው እየተጠየቁ ለማገልገል በቁ፡፡ ምርጥ ታሪክ መምህር መሆን ቻሉ፡፡ መጀመሪያ ምስራቅ ባሌ በመምህርነት መሥራት ጀመሩ፤ ብዙም ሳይቆዩ አጋርፋ በድጋሚ ተመደቡ፣ እንደገና ሮቤ የመምህራን ማሠልጠኛ እንዲያስተምሩ ተላኩ፡፡ ከዛ እንደገና ጳራ የሚባል ቦታ እንዲያስተምሩ ተጠየቁ፤ በመጨረሻ ግን ጳራ ለሁለት ዓመት ከቆዩ በኋላ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ለመማር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገቡ፡፡**

**የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ካጠናቀቁ በኋላ፤ ሮቤ መምህራን ማሠልጠኛ የነበረው እና ወደ ሮቤ ኮሌጅ ባደገው ተቋም ለሁለት ዓመት ቆይተው ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ተዘዋወሩ፡፡ አሁንም በእዛው በጅማ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት ሙያ እያገለገሉ እና የተለያዩ የምርምር ሥራዎችንም እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል መምህር ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙት እና የምርምር ሥራዎችንም የሚያከናውኑት ፀጋዬ ዘለቀ (ዶ/ር) ጋር አጠቃላይ ታሪክን በተመለከተ እንዲሁም ሰሞኑን እየተዘከረ ያለውን የዓድዋ ድል ላይ አተኩረን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፡፡ መልካም ንባብ፡-**

**አዲስ ዘመን፡- ታሪክ ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ፀጋዬ፡-** ታሪክ በቀላሉ የሚታወቅ እና ተበይኖ የሚቀመጥ አይደለም፤ በጣም ብዙ ማንበብን እና መመራመርን ይጠይቃል፡፡ በትምህርት ላይ በነበርኩበት ወቅት የዓለም፣ የአፍሪካ፣ የኢትዮጵያ ታሪክን ተምሬያለው እጅግ ሰፊ ነው፡፡ የዓለም ታሪክ ሲባል የአውሮፓ ታሪክ ለብቻው እጅግ ሰፊ ንባብን የሚጠይቅ ነው፡፡ እንኳን የዓለም የኢትዮጵያ ታሪክም ባህር ነው፡፡ ታሪክ ላይ ሙሉ ለሙሉ በዘመንም ሆነ በሀገር አውቀናል ማለት አይቻልም፡፡ ለምሳሌ የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ታሪክ ከተባለ ኢኮኖሚው፣ ማህበራዊው እና ሌላ ሌላውም ይጠናል፡፡ እንደዛም ሆኖ ያንን ሙሉ ለሙሉ ማወቅ አይቻልም፡፡ ታሪክ የሰው ልጅ ሰርቶ ያለፈ ጉዳይን በሙሉ ስለሚዳስስ፤ ያንን ማወቅ በጣም ፈታኝ ነው፡፡

በሌላ በኩል በየትኛውም ጊዜ ያለ ታሪክ መረጃ ሙሉ ሆኖ አይገኝም፡፡ ታሪክ ፀሃፊ መረጃዎችን አንብቦ አመሳክሮ፣ የመጀመሪያ መረጃ ሁለተኛ መረጃ እያለ አጣርቶ መፃፍ አለበት፡፡ የእኛ ሀገርን ታሪክ በደንብ ልወቅ ከተባለ የራሳችንን ታሪክ ከአፍሪካ ታሪክ ጋር አመሳክረን፤ በተጨማሪ የፅሁፉን ታሪክ ከአፈ ታሪኩ ጋር አስተሳስረን መፃፍ እና ማንበብ አለብን፡፡ አንድ መጽሐፍ ብቻ ተነቦ አንድን ታሪክ ማወቅ አይቻልም። መመሳከር አለበት፤ ታሪክን ማወቅ ጊዜ የሚወስድ ነው። ይህ በዓለም ደረጃ ፈተና ነው፡፡

እኛ ሀገር ታሪክ ላይ ብዙ ጫናዎች እና የተለያዩ ፈተናዎች አሉ፡፡ እንደሚታወቀው ታሪክን ለታሪክ ባለሙያ የመተው ችግር አለ፡፡ በሌላው ዓለም በእያንዳንዱ ዘርፍ የታሪክ ባለሙያዎች አሉ፡፡ ትንታኔ የሚሰጡትም የታሪክ ባለሙያዎች ናቸው፡፡ ያደጉ ሀገራት ጠንካራ የታሪክ ማህበርም አላቸው፡፡ ታሪክ ሳይንስ ነው፡፡ ባለሙያዎች ታሪክን መፃፍ ያለባቸው በሳይንሳዊ መንገድ ነው፡፡

ታሪክ የራሱ የአፃፃፍ ዘዴ አለው፡፡ ምናልባትም ፈተና የሆነው በሳይንሳዊ መንገድ እየሔድንበት ባለመሆኑ ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ታሪክን የምናይበት መንገድም ሆነ የፖለቲካ ጫናዎች ትልቅ ፈተና ሆነውብናል፡፡ አሁን ግን በሒደት የኢትዮጵያ ታሪክ ባለሙያዎች ማህበርን እስከ ማቋቋም ደርሰናል። ወደ ፊት ብዙ ነገሮች ይስተካከላሉ ብዬ አስባለሁ፡፡

ታሪክን በቅጡ ለማወቅ እያንዳንዱ ቅንጣት መታየት አለበት፡፡ ታሪክ ፖለቲካ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ ሰፊ ጉዳይ ነው፡፡ የሕክምና ታሪክ ብቻውን በሰፊው ሊጠና ይችላል፡፡ የስፖርትን ታሪክ ብቻ መሥራት ይቻላል፡፡ በእርግጥ እኛ እዛ ላይ አልደረስንም፡፡ ነገር ግን ታሪክ ሰፊ እንደባህር ጥልቅ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከታሪክ ጋር ተያይዞ ብዙ ውዝግብ ባለበት በዚህ ጊዜ የታሪክ ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች ማህበር ከመቋቋም ባሻገር ምን ማድረግ አለባቸው ይላሉ?**

**ዶ/ር ፀጋዬ፡-** ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የሚያጨቃጭቁ ታሪኮች አሉ፡፡ እዛ ላይ ባለሙያው ገንዘብ በጣም ቢያስፈልገውም ቢያንስ ማህበሩ በእነዚህ ላይ ምርምር አድርጎ የጠራ ታሪክ እንዲኖር ቢያደርጉ መልካም ነው፡፡ እንደሚታወቀው ታሪክ ለሀገር ግንባታ የሚኖረው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡ ታሪክ ያገናኛል፤ የሰው ልጅ ታሪክ ወደ ኋላም እየተጠና ሲቀጥል አንድ መሆናችንን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በእርግጥ ማህበሩ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ቢሠራ ጥሩ ነው፡፡ አሁንም እየሠራቸው ያሉ ጉዳዮች አሉ፡፡ ኮንፈረስም እያካሄድን ነው፡፡ ስፖንሰር የሚያደርጉም አሉ፡፡ ስለዚህ በታሪክ በኩል ጥሩ መስመር ላይ ነን ብዬ አምናለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከኢትዮጵያ ታሪክ መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው የዓድዋ ድል ነው፡፡ ይህ የዓድዋ ድል ታሪክ በዓለም ደረጃ ያመጣው ለውጥ ምንድን ነው ይላሉ?**

**ዶ/ር ፀጋዬ፡-**የዓድዋ ድል እንደሚታወቀው ጥቁሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙት አንፀባራቂው ድል ነው፡፡ ከዓድዋ ድል በፊትም ሆነ በኋላ ተመሳሳይ እና ተወዳዳሪ በዓድዋ ደረጃ ድል አልተገኘም፡፡ በተወሰነ መልኩ በዓለም ታሪክ ውስጥ ከዘጠኝ ዓመት በኋላ የተመዘገበው ጃፓኖች በራሺያ ላይ የተቀናጁት ድል ነው፡፡ የዓድዋ ድል በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ምክንያቱም በዛ ጊዜ ራሺያ ናፖሊዮን ያሸነፈች፤ በሁለተኛውም ሆነ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ ሁሉንም ለማለት በሚያስችል መልኩ አውሮፓዎችን ያሸነፈች ነበረች፡፡፤ ሆኖም በኋላ በጃፓን ተሸንፋለች፡፡

የኢትዮጵያው የዓድዋ ድል ደግሞ በዛ ጊዜ እንደሚታወቀው ጥቁር ሕዝብ እንደሸቀጥ የሚሸጥበት እና የባሪያ ንግድ የነበረበት፤ ጥቁሮች የበታች ተደርገው አውሮፓዎች አፍሪካን ለመቀራመት የመጡበት እና አብዛኛው አፍሪካ በእነርሱ እጅ ውስጥ በወደቀበት ጊዜ የተገኘ ድል በመሆኑ ጥቁሮች በነጮች ላይ ያገኙት የመጀመሪያው ድል ነው፡፡ ሌላው የዓድዋ ድል ላይ ነጮች ጉልበት ያለው የፈለገውን ማድረግ ይችላል ብለው ያምናል፡፡ ይህ በራሱ ልክ እንዳልሆነ ያረጋገጠ ድል ነው፡፡ ሃይል አለን ቢሉም እንደሚሸነፉ በዓድዋ ድል ታይቷል፡፡ ድሉ ጥቁሮች የበታች ናቸው የሚለው ትርክት እንዲሸረሸር አድርጓል፡፡ ሌላው ቀርቶ ለጣሊያን ወግነው የሚፅፉ የዓለም ዕውቅ ፀሃፊያን እነጆርጅ፤ ‹‹በአፍሪካ አዲስ ሃይል ተነሳ›› ሲሉ ከትበው ነበር፡፡

ይህ በጣሊያን ላይ የተቀናጀነው ድል ምናልባት በኋላም ዘግይተው የመጡትን ፋሺስቶችን ለመምታት እንደዋነኛ ምክንያት ይወሰዳል፡፡ ሌላ መሪ ሲመጣ ለዳግም ወረራ ተዘጋጅተው ከ40 ዓመት በኋላ በሞሶሎኒ በኩል ኢትዮጵያን ሲወሩ፤ ዳግም ተሸንፈዋል፡፡ የዓድዋ ድል ከዓለም አንፃር ሲቃኝ ያመጣው ለውጥ ደግሞ ሄዶ ለሁለተኛው የዓለም ጦርነት መነሳት ዋነኛ ባይሆንም እንደአንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል፡፡

ኢትዮጵያን አስመልክቶ ብዙ የፃፉት በዓለም ደረጃ የታወቁት ፖል የሚባሉት ሰው እንደገለፁት፤ የዓድዋ ድል አውሮፓ በዓለም ፖለቲካ ውስጥ ያላትን የበላይነት ማጣት መጀመሯን ያመላከተ መሆኑን እና የሃይል ፖለቲካ ማዕከሉ ወደ ሌላ መንገድ እያመራ እንደሚገኝ ያመላከተ ድል ነው ብለዋል፡፡

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ እንዳሸነፈች በዛው ዓመት መጀመሪያ ጣሊያን ኢትዮጵያ ውስጥ ቆንፂላ ከፍታለች። ከዛ በኋላ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ የራሳቸውን ቆንፂላ መክፈታቸው እና ኢትዮጵያ በሃያላን ሀገራት ዘንድ ዕውቅና ማግኘቷ የታወቀ ነው። በዛ ጊዜ ብዙ ነጮች ወደ አዲስ አበባ የመጡበት ጊዜ በመሆኑ ዓመቱ የፈረንጆች ዓመት እስከመባል መድረሱ ተፅፏል፡፡

ፓን አፍሪካኒዝም፤ አሜሪካን ውስጥ በባሪያ ንግድ ወደ እዛ የሄዱ ሰዎች የጀመሩት እንቅስቃሴ ነው፡፡ በተጨማሪ የዓድዋ ድል እነርሱንም የበለጠ አነቃቅቷል፡፡ የመጀመሪያው የፓን አፍሪካ ኮንፈረስ ተብሎ የሚጠራው በ1900 ላይ የተካሔደው እና በዊሊያም ሔነሪ ሲልቪስተር ስም ለተሰየመው ኮንፈረንስ ድሉ አንዱ ትልቅ ግብዓት ሆኗል፡፡ ለ1919፣ 1921፣1923 ማንቸስተር ላይ በ1945ም ለተካሔደውም የፓን አፍሪካ ኮንፈረስ ሁሉ ትልቅ ሚና ነበረው። በኋላም ከዳያስፖራው በተጨማሪ አፍሪካ ውስጥ ያሉት እነኩዋሜ ኑኩሩማ ፣ ጆሞ ኬንያታ፣ ጁሊየስ ኔሬሬ እና ሌሎችም ተሳትፈው አፍሪካ ከአውሮፓውያን ነፃ እንድትወጣ ሲጠይቁም የዓድዋ ድል አንዱ ግብዓት ነው፡፡

ስለዚህ በአጠቃላይ ድሉ አፍሪካ ከአውሮፓ ቀኝ ግዛት ነፃ እንድትወጣ ትልቁን ሚና ተጫውቷል። ያንን ሁሉ የጠየቁበት ኮንፈረስ ነው፡፡ በኋላም ፓን አፍሪካኒዝም ወደ አፍሪካ ሕብረት ድርጅት፣ አፍሪካ አንድነት እና አፍሪካ ሕብረት ሲሸጋገሩ በሙሉ ከዓድዋ ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ ስለዚህ ይህ ሁሉ ሲታይ ዓድዋ በአፍሪካ ደረጃ የተገኘ ትልቅ ድል ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ጥቁር ከነጭ ጋር እኩል መሆኑን ከማሳየት ባሻገር የዓለምን የፖለቲካ መስመር ቀይሮታል ይባላል፡፡ በእርግጥ ቀይሮታል ለማለት መገለጫው ምንድን ነው?**

**ዶ/ር ፀጋዬ ፡-** በእርግጥ በታሪክ በረዥም ጊዜ የሚገኝ ለውጥ ተብሎ የሚጠራ ውጤት አለ፡፡ ከዚህ አንፃር እንይ ከተባለ ለምሳሌ በኢትዮጵያ አንድ አቢዮት ተነሳ እንላለን፡፡ አቢዮት ረዥም ጊዜ የሚወስድ ነው። የዓድዋም በተመሳሳይ መልኩ ተፅዕኖው በአንድ ጊዜ የታየ ነው ለማለት ያዳግታል፤ ረዥም ጊዜ ይወስዳል። በዛን ጊዜ ለምሳሌ ሃያል ሀገር የሆኑት አውሮፓዎች ራሳቸው ፈረንሳይ እና ራሺያ የኢትዮጵያ ተፃራሪዎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ፈረንሳይ ጅቡቲ ላይ ቤዝ ነበራት። ጦርነቱ በዛ በኩል እንዲመጣ ፈረንሳይ ፈቅዳ ነበር። ራሺያም በተመሳሳይ መልኩ ከኢትዮጵያ ጋር በተቃራኒው የቆሙ ነበሩ፡፡ ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራቸዋል፡፡

በተጨማሪ በአሜሪካን ውስጥም የነማርቲን ሉተር ኪንግ መነሳት በራሱ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ግን አሁንም ገና በአፍሪካ ብዙ ችግሮች እንዳሉ መካድ አይቻልም፡፡ ስለዚህ በቀጣይ ለሚኖረው የዓለም የፖለቲካ አሰላለፍ ለውጥም ጭምር የዓድዋ ድል ሚና ይኖረዋል ብዬ መናገር እችላለሁ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የትኛውም ሀገር ሕዝብ**

ወደ ገጽ 20 ዞሯል

# ዓድዋ! በኢትዮጵያ ድል የደመቀ የአፍሪካ ኩራት

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

‹‹ያገሬ ሰው ከአሁን በፊት የበደልኩህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም:: ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ፣ለሚስትህ፣ ለሃይማኖትህ ስትል በኀዘንህ እርዳኝ:: ወስልተህ የቀረህ እንደሁ ግን ኋላ ትጣላኛለህ:: ለዚህ አማላጅ የለኝም:: ማርያምን! አልተውህም:: ዘመቻዬ በጥቅምት ነውና የሸዋ ሰው እስከጥቅምት እኩሌታ ወረኢሉ ከተህ ላግኝህ››

ይህ ታላቅ የክተት አዋጅ ከኢትዮጵያው ንጉሰ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ አንደበት በተሰማ ጊዜ መላው ኢትዮጵያዊ ከያለበት ተመመ:: በወቅቱ ማቄን ጨርቄን፣ ቤቴን ፣ ትዳሬን፣ ያለ አልነበረም:: ጥሪው የንጉሥ፣ ነገሩ የህልውና ጉዳይ ነውና ሁሉም ስለሀገሩ መኖር፣ ስለ ወገኑ መቆም ራሱን ሊሰጥ ዓላማው በአንድ ሆነ::

የኢትዮጵያ ድንቅ ተፈጥሮ እንደ ልዩ መዓዛ ከሩቅ የሚስባቸው ባዕዳን ዝናዋን ሰምተው ብቻ አልተቀመጡም:: ጣዕሟን ሊመጡ፣ ክብሯን ሊያዋርዱ ድንበር ጥሰው፣ ባህር አቋርጠው ተመላልሰዋል:: እንዲያም ሆኖ ሊያጣጥሟት የሻቷትን ሀገር ደርሰው እጇን አልጨበጡም:: እንደ እሳት የሚፋጀው የጀግኖች ልጆቿ ሀያልነት የውርደት ሸማን አከናንቦ መልሷቸዋል::

ይህ እውነት የኢትዮጵያ ሀገራችን ተደጋጋሚ ታሪክ ነው:: ለዘመናት ማንነቷን ሊፈትኑ ከደጇ የደርሱ ጠላቶቿ መጨረሻቸው በሽንፈት መንበርከክ ሆኗል:: ሀገራችን በዘመኗ ባህር አቋርጣ ድንበር ጥሳ የሌሎችን ሀብት የተመኘችበት ጊዜ የለም:: በእሷ ታሪክ ግን ይህ አይነቱ ሀቅ ተገላቢጦሽ ሆኖ ታላቅነቷን ሲያስመሰክር ፣ስሟን በዝና ሲያስጠራ ኖሯል::

የዓመታት ታሪክ ወደ ኋላ ሲቃኝ አውሮፓውያን መላ አፍሪካን በቅኝ ለመግዛት ፣ መሬቷን ለመቀራመት የተንቀሳቀሱበት ዘመን ላይ ያደርሰናል:: የዚህ ጊዜ ሌላው መልክ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መንግሥት መካከል የውጫሌ ውል ስምምነት የተካሄደበት ጊዜ ነበር::

ኢጣሊያኖች ምጽዋን በእንግሊዞች ርዳታ ከግብጽ ከወሰዱ በኋላ ዓላማው ለነጋዴዎች ማረፊያ በሚል ምክንያት አስመራንና ዙሪያውን በቁጥጥር ስር አደረጉት:: ቀስ በቀስም ሰራዬ የተባለውን ስፍራ ጨምሮ እስከ ሀማሴን ምድር ዘለቁ:: ውሎ አድሮ አጼ ምኒልክ ጣሊያኖቹ በያዟቸው ድንበሮች ላይ ወሰን ለመለየት የሚስላቸውን የውጫሌ ውል ለመፈራረም ከስምምነት ደረሱ::

እነሆ ! ሁለቱ ወገኖች በአንድ ሊቀመጡ ቀኑ ደረሰ :: የተጻፈው ሃሳብ ጥንቃቄ የሚያሻው ነው:: ስምምነቱ ከመፈረሙ አስቀድሞ ጉዳዩን በወጉ ማጤን ይገባል :: ውሎቹ ገፅ በገፅ እየተገለጡ፣ ቃል በቃል እየተነበቡ አንድ በአንድ ተፈተሹ::

ምርመራው ሲቀጥል በኢትዮጵያ በኩል በውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው አንቀጽ ከሌሎች ሁሉ የሚለይ መሆኑ ታወቀ :: በኢጣሊያ ቋንቋ የሰፈረው ይህ ውል ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን በሀገረ ኢጣሊያ በኩል ብቻ እንድታካሂድ የሚያስገደደድ ስለመሆኑ በግልጽ ሰፍሯል:::

ንጉሥ አጼ ምኒልክ ይህን ውል አይተው ለመፈረም ልባቸው አልፈቀደም:: ሙሉ ለሙሉ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ ስለሚሰጠው አስገዳጅ ውል ከባለሚሎቻቸውና ከሌሎች ሀገራት መሪዎች ጋር መከሩበት:: ባገኙት ምላሽ መሠረትም ውሉን ላለመፈረም በአቋማቸው ጸኑ:: ይህ ውሳኔያቸውንም ለኢጣሊያ መንግሥት በግልጽ አሳወቁ::

ከዚህ በኋላ ኢጣሊያ የልቡ ሃሳብ አለመሙላቱን ተረዳ:: ውሎ ሳያድርም ግዛቱን ከመረብ አሻግሮ ኢትዮጵያን ለመውረር ጦሩን አደራጀ :: አሁን ወራሪው የኢጣሊያ ጦር ያነሰ ግምት ለሰጣት ኢትዮጵያ የበዛ ጦሩን አስታጥቆ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር ገብቷል::

ዕቅዱ ግን እንደታሰበው አልሆነም:: በአምባላጌና መቀሌ የተላኩት የኢጣሊያ ወታደሮች በአፍታ ቆይታ በኢትዮጵያውያን ብርቱ ክንድ ድል ሆኑ:: ይህ ሽንፈት ባህር አቋርጦ ለመጣው የጠላት ጦር ከውርደት በላይ ነበር:: ከዚህ በኋላ ሰፊውን ጦር በዘመናዊ የመሣሪያ ሃይል ያደራጀው የኢጣሊያ ሠራዊት መላ ኢትዮጵያን አንበርክኮ የቋመጠባትን ድንቅ ሀገር በእጁ ሊያደርግ ተጣደፈ::

የጦርነቱ አይቀሬነት የገባቸው ንጉሥ ምኒልክ ‹‹አለኝ›› የሚሉትን ዘመናዊ መሣሪያ ከልበ ሙሉው ጦራቸው ጋር አዘጋጁ:: አምስት ጎራሹ የወጨፎ ጠመንጃ ተወልውሎ ከጀግኖቹ እጅ ዋለ:: ከውጭ ሀገራት በግዢ የተገኙት በሚሊዮን የሚገመቱ ጥይቶች ተቆጠሩ:: ከፈረንሳይ መድፎች ተገዙ:: ብልሁ ንጉሥ ይህ ብቻ አልበቃቸውም::

በወቅቱ ሊፈጠሩ የሚችሉ የሀገር ውስጥ አለመግባባቶችን በውይይት ለመፍታት ሞከሩ:: ያኮረፉ፣ የከዱና የሸፈቱ አገረ ገዢዎችን በምህረትና ይቅርታ እየመለሱ ከጎናቸው አደረጉ:: እንዲህ መሆኑ የሀገር አንድነትን አበረታ:: ሁሉም ለአንድ ዓላማና ግብ ተጣምሮ ወራሪውን ጠላት ሊመክት በሙሉ ልብ ተዘጋጀ::

ምኒልክ የሆነባቸውን ሁሉ ለመላው ዓለም ለማሳወቅ አጠገባቸው ባሉ የፈረንሳይና የሩሲያ ዜጎች አንደበት ተጠቀሙ:: እውነታው በታወቀ ጊዜም የዓለም ዓይንና ጆሮ ወደ ኢትዮጵያ ምድር አዘነበለ::

ዓድዋ ላይ የምኒልክ ጦር በጀግንነት ተሰልፏል:: በእጁ ያለው መሳሪያ ከጠላቱ ጋር ሲተያይ እዚህ ግባ ይሉት አይደለም::በባዶ እግር፣ በአጭር ሱሪ በኋለ ቀር ጠመንጃ ጠላቱን ሊዋጋ በሙሉ ወኔ ዘብ ቆሟል:: ፉከራና ቀረርቶው ልብ እያሞቀ ወንድ ሴቱን እያነሳሳ ነው::

የኢጣሊያው ጦር አዛዥ ጄኔራል ባላቶሊ ይህን ባወቀ ጊዜ ሃያ ሺህ የሚሆነውን በዘመናዊ መሣሪያ እስከ አፍንጫው የታጠቀ ጦሩን በሶስት ግንባር አሰልፎ ወደፊት ተጠጋ:: ጦርነቱ አይቀሬ ሊሆን ደቂቃዎች ተቆጠሩ:: የአጼ ምኒልክ ጦር በሶስት ግንባር ተሰልፎ የተጋፈጣቸውን የጠላት ጦር ለመመከት የጀግንነት ሥልቱን ተጠቀመ::

ሃያልነቱን ተመክቶ ንቀቱን ሊያሳይ ጉዞ የጀመረው ጠላት በትንታጎቹ ኢትዮጵያውያን እጅ ሲገባ በድንጋጤ ግራ ተጋባ :: ከፊት የሚያጠቃው ሃይል ከኋላው በሚገኝ የደጀን ጦር እየታገዘ ጠላትን ያስጨንቅ ያራውጠው ያዘ::

ጦርነቱ ተፋፋመ:: በጥይት አረር መፋጀቱ፣ በሳንጃ ስለት መሞሻለቁ ቀጠለ:: ከየአቅጣጫው የሚወድቅ፣ የሚቆስለው በረከተ:: በዓድዋ ምድር ደም እንደውሃ ጎረፈ:: ሁለት የኢጣልያ ጄኔራሎች በሽንፈት እጅ ሲሰጡ አንደኛው ከፊታቸው ወድቆ የሞት ጽዋን ተጎነጨ ::

ከአንድ ሺህ ሁለት መቶ በላይ ጦር ምርኮ የሆነበት ጠላት እንደአገባቡ ሁሉ ሜዳው አልቀለለውም። መውጫው ጠፍቶት ከወዲያ ወዲህ ተራወጠ:: በዓድዋው ጦርነት ከአስር ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን መስዋዕት ሆነዋል::

ይህ መሰዋዕትነት ያቀለመው ታላቅነት ነጮች በአሸናፊነት የመዝለቃቸውን እውነት የሚያከሽፍ ሆኗል:: በዘመኑ በቅኝ ግዛት ስር ለሚማቅቁ ሀገራትም የማንቂያ ደወል ነበር :: ውሎ ያላደረው ብርቱ ትግል በአንድ ቀን ተጋድሎ ፣ ድሉን ለኢትዮጵያውያኑ አደረገው::

እነሆ! የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም :: ኢትዮጵያውያን ‹‹እምቢኝ ለሀገሬ ሲሉ በደማቸው ታሪክ የጻፉበት፣ ነጻነታቸውን ያዋጁበት ድንቅ ቀን:: አንድነታቸውን በሕይወት መስዋዕትነት ያሳዩበት አስደናቂ ውሎ:: ይህ ዕለት ታሪካዊነቱ ለምድረ አበሻ ብቻ አልሆነም:: በማንም ዘንድ ያልተሞከረው ሃያል ተጋድሎ አሸናፊነቱ ለመላው ጥቁር ሕዝብ ሆኖ ድሉን በመላው ዓለም አስተጋባ::

በቅኝ ቀንበር የታገቱት ሕዝቦች ትግልን ይጀምሩት ዘንድ ሃይልና ጉልበት የሆነው የዓድዋው ድል የወንዶች ተሳትፎ ብቻ አልነበረም:: እቴጌ ጣይቱን የመሰሉ ብልህ የጦር መሪና አማካሪ ድንቅ ጀግንነት ታክሎበታል::

በጣይቱ መሪነት በተካሄደው ጦርነት በመላው ሀገሪቱ የነበሩ ሴቶች ተጋድሎ የበዛ ነበር:: ከስንቅ ዝግጅት ደጀን እስከመሆን፣ ቁስለኞችን አክሞ ጦር መርቶ እስከመዋጋት የደረሰው የሴት አርበኞቹ ትግል ለዓድዋው ድል መሠረት ለአፍሪካውያን ህብረት ክንድ ነበር::

# «አፍሪካ ከአውሮፓ ቅኝ ግዛት ነፃ...

ከ19 ኛው ገጽ የዞረ

**ዝም ብሎ ቅኝ አልተገዛም፡፡ የተለያዩ ትግሎችን ያደርጉ ነበር፡፡ ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ድል አልተጎናፀፉም፡፡ ኢትዮጵያውያን እንዴት ቅኝ ገዢን ማሸነፍ እና ድል መጎናፀፍ ቻሉ?**


**ዶ/ር ፀጋዬ፡-** እዚህ ላይ ኢትዮጵያውያኖች ድሉን ለማግኘት የነበራቸውን ምቹ ሁኔታ ጣሊያኖች የነበራቸውን ምቹ ሁኔታ ምንድን ነው የሚለው ሲነፃፀር አውሮፓውያን ያለምንም ጥርጥር በዛ ጊዜ የተሻለ የጦር መሣሪያ ነበራቸው።በተጨማሪ ከኢንዱስስሪ አብዮት በኋላ የመጡ በመሆኑ ከእኛ በጣም የተሻለ የጦር መሣሪያ ነበራቸው:: ለምሳሌ ማክሲም ገን የሚባል ለአፍሪካውያን የማይሸጥ የጦር መሣሪያ ነበር። ጣሊያኖች ያንን መሣሪያ ይጠቀሙ ነበር::

በሌላ በኩል ኢትዮጵያውያኖች መልከዓ ምድሩን ያውቃሉ:: ምናልባትም ግን የመሪዎች ብቃት እና አቅም እንዲሁም አፄ ምኒልክን ጨምሮ የሌሎችም የጦር መሪዎች ሚና ትልቅ ነበር:: በዛ ጊዜ የነበሩት የጦር መሪዎች በጦርነት ውስጥ ተወልደው ያደጉ እንዲሁም ጦርነት ምን እንደሆነ የሚያውቁ ነበሩ:: ነገር ግን ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ ዓድዋ ላይ ድል እንድታገኝ ያደረጋት አንድነቷ ነው:: መላው ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ ተንቀሳቅሰው በአንድነት እዛ ሔደው መዋጋታቸው ኢትዮጵያውያን ድል እንዲያገኙ አድርጓቸዋል:: ሁሉንም ሕዝብ በአንድ ላይ መጠራቱ እና ሁሉም መንቀሳቀሱ ድሉ እንዲገኝ አድርጓል የሚል እምነት አለኝ::

**አዲስ ዘመን፡- ከዓድዋ ድል ኢትዮጵያ ምን አተረፈች?**

**ዶ/ር ፀጋዬ ፡-** የዓድዋ ትሩፋት ብዙ ነው። ሀገርን ወይም ሀገረ መንግሥትን በመገንባት ላይ ሚናው ከፍተኛ ነው:: ማለትም ሉዓላዊነትን ማስከበር ከመቻል እና መንግሥትን ከመገንባት አንፃር የተገኘውን ትሩፋት መጥቀስ ይቻላል:: በሌላ በኩል ዓድዋ ኢትዮጵያውያን የጋራ ትርክት እንዲኖራቸው አድርጓል::

**አዲስ ዘመን፡- ከላይ እርሶ እንደገለፁት ዓድዋ በዓለም ደረጃ ሲጠቀስ የሚችል በጣም ትልቅ ድል ነው፡፡ ነገር ግን በልኩ ለዓለም አስተዋውቀነዋል ብለው ያምናሉ ?**



**ዶ/ር ፀጋዬ፡-**ይሔ ምንም ጥያቄ የለውም ድሉን በማስተዋወቅ በኩል ተገቢውን ሥራ አልሠራንም:: ምናልባት በተለይ የአሁኑ ትውልድ አፍሪካ ውስጥም ሆነ ከአፍሪካ ውጪ ያሉት ድሉን የማያውቁበት ሁኔታ ይኖራል:: ነገር ግን በዛ ጊዜ የተማረው ሕዝብ እና የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የፖለቲካ መሪዎች ከእኛ የበለጠ ዓድዋን ያውቁታል:: አሁንም ብዙዎች ከእኛ በላይ ለዓድዋ ቅርብ ናቸው:: አሁንም ከእኛ ይልቅ አሜሪካን ውስጥ ያሉት ጥቁሮች፣ ካረቢያን አካባቢ ጃማይካ ላይ እና ሌሎችም አካባቢዎች ለምሳሌ ብራዚል ውስጥ ይታወቃል:: በመጀመሪያ ብራዚል ውስጥ የነበረው የጥቁሮች ጋዜጣ ‹‹ኦ ሚኒሊክ›› የሚል ነበር:: ዓድዋን በማስተዋወቅ እንደውም እኛ ብዙ ሠርተናል ማለት አይቻልም:: አሁን የተወሰነ እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: ነገር ግን አሁንም ብዙ ይቀረናል::

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ ምን መሠራት አለበት?**

**ዶ/ር ፀጋዬ ፡-** የዓድዋን ታሪክ ለማሳወቅ አሁን ላይ የተጀማመሩ ነገሮች አሉ:: ነገር ግን ብዙ ጥናት መደረግ አለበት:: ዓድዋ ላይ ብቻ ሳይሆን ብዙ የተጀማመሩ ታሪኮች ላይ ብዙ ይቀረናል:: የዓድዋ ታሪክ ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ታሪክ ብዙ ምርምሮችን ማድረግ አለብን:: ብዙ ነገሮች ላይ የማንስማማባቸው ነገሮች አሉ:: ለምሳሌ በዓድዋ ጀግኖች ራሱ አንስማማም፤ ለምሳሌ ገበየሁ ጎራ ይባል ነበር፤ በኋላ ገበየሁ ጉርሙ ተባለ አሁን ደግሞ ገበየሁ ገብሩ ተባለ ስለዚህ በጀግኖቻችን ስም እንኳ እየተስማማን አይደለም::

የጦር መሪዎች ታሪክ ከስማቸው ጀምሮ አሻሚ ናቸው:: ይሔን ማጣራት ከባድ አይደለም:: ምክንያቱም የ 128 ዓመት ታሪክ የልጅ ልጆቻቸውን አግኝቶ ማጣራት ይቻላል:: የተወለዱበት ቦታ ሔዶ ማረጋገጥ ይቻላል:: እዚህ ላይ የታሪክ ተማሪዎች ባለሙያዎች እና ተመራማሪዎች እንዲሁም የመገናኛ ብዙሃን ሰዎች መሥራት አለባቸው:: መፅሐፎች አልፎ አልፎ አሉ:: ነገር ግን ብዙ ግልፅ ያልሆኑ ነገሮች አሉ። ሙሉ ታሪኩን የያዘ ሳይሆን ለአንድ ወገን ያደላ ለራስ ብቻ ዕውቅናን የሚሰጥ የራስን ሚና ብቻ ከፍ በሚያደርግ መልኩ የሚደረጉ ትርክቶች ሙሉውን ታሪክ አይነግሩንም:: ሚዛናዊ የሆነ የሁሉንም መሪዎች ቢያንስ የዓድዋን ድል በሚመጥን መልኩ ምርምር ከማካሔድ ባሻገር የጥናት ማዕከላት መቋቋም ይኖርባቸዋል:: አሁን የተጀመረው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም እንደትልቅ ሊታይ ይችላል:: ነገር ግን ከዚህ በኋላ ሰፊ ምርምሮች መካሔድ አለባቸው::

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶ/ር ፀጋዬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

# ዓድዋ - የነፃነትና የፍትሕ ትግሎች መሰረት

**አንተነህ ቸሬ**

ታላቁ የዓድዋ ድል መላውን ዓለም ያስገረመ፣ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገና ኢትዮጵያና ድሏ የጭቁኖች የነፃነት ምልክትና መሰረት ሆነው እንዲታዩ ያስቻለ ደማቅ ታሪክ ነው:: በዳግማዊ አፄ ምኒልክ የተመራው የኢትዮጵያ ጦር በወራሪው የኢጣሊያ መንግሥት ጦር ላይ ያስመዘገበው ድል በዓይነቱ የተለየ ስለነበር መላውን ዓለም ያስገረመ፣ ያስደነቀና ያስደነገጠ ክስተት ሆኖ በታሪክ ተመዝግቧል።ይህ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ ለመላው ዓለም ጭቁኖች የነፃነት ተስፋን የፈነጠቀና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገ፤ በአንፃሩ ለወራሪው ጦር ደግሞ ሁለገብ ውድመትንና ውርደትን ያስከተለ ድል ነው::

የዓድዋ ድል የአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት ንቅናቄዎች ምልክት መሆን የቻለ ወሳኝ ታሪካዊ ክዋኔ ነው። ጦርነቱና ድሉ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ በጋራ ተሰልፈው ዓለምን ያስደነቀ ገድል መፈፀማቸውን ለመላው ዓለም ያሳዩበት በመሆኑ ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው በጋራ ሆነው መታገል እንደሚገባቸው ትምህርት የሰጠ ታላቅ ክስተት ነው:: የድሉ ትሩፋቶች ለጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ የሞራል ስንቅ ሆነዋል፤ የነፃነት ትግሎቹም ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ የስኬት መንገድን ጠርገዋል::

ድሉ በአፍሪካ፣ በካሪቢያንና በእስያ ለተካሄዱ የነፃነት ትግሎች መጀመርና ስኬታማ መሆን የጎላ ሚና ነበረው:: የዓድዋ ድል በመላው ዓለም የሚገኙ ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው እንዲታገሉ ያነሳሳ፣ ትግላቸውን ያጠነከረና ለስኬት እንዲበቁ ያደረገ የአሸናፊነት ምንጭ ስለመሆኑ የበርካታ አገራት መሪዎች፣ ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል፤ በጥናቶቻቸውም አረጋግጠዋል:: ከአሕመድ ሴኮ ቱሬ እስከ ኔልሰን ማንዴላ፣ ከክዋሜ ንክሩማህ እስከ ታቦ ምቤኪ፣ ከዊልያም ኤድዋርድ ዱ ቦይስ እስከ ማርከስ ጋርቬይ፣ ከስቬን ሩቤንሰን እስከ ማሞ ሙጬ፣ ከሬይሞንድ ጆናስ እስከ አየለ በከሪ፣ ከቨርጂኒያ ሊ ጃኮብስ እስከ ሮበርት ኔስታ ማርሌይ (ቦብ) ... በርካታ የአገራት መሪዎች፣ ምሁራንና ታዋቂ ሰዎች ስለዓድዋ ድል አንፀባራቂነትና በዓድዋ ስለደመቁት ኢትዮጵያውያን ጀግንነት ተናግረዋል፤ ጽፈዋል፤ አዚመዋል!

ኢትዮጵያን እንደ ሁለተኛ አገራቸውና ቤታቸው ቆጥረዋል:: የአፍሪካ የነፃነት መሪዎች (ኔልሰን ማንዴላ፣ ሮበርት ሙጋቤ እና ሌሎችም) የነፃነት ትግላቸውን ባደረጉባቸው ጊዜያትም ኢትዮጵያ ውስጥ መጥተው የተለያዩ ድጋፎችን አግኝተዋል:: ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ እንደነፃነት ምልክት መቆጠሯ በወሬና በንድፈ ሃሳብ የተገለፀ ብቻ ሳይሆን በተግባር የታዩና የተረጋገጠ መሆኑን ነው:: የዚህ ሁሉ ምንጭ ደግሞ የዓድዋ ድል ነው:: የአብዛኞቹ የዓለም የጭቁኖች የነፃነት ትግሎች መነሻና የስኬት ምንጭ የዓድዋ ድል እንደሆነ አይካድም::

የዓድዋ ድል በተለያዩ የዓለም አካባቢዎች ለተደረጉ የነፃነት ትግሎች መነቃቂያ ከመሆን ባሻገር አገራት ነፃነታቸውን ካገኙ በኋላ በጭቁኖች ለተቋቋሙ ተቋማት መመስረትም ሚናው የጎላ ነው:: ከእነዚህ ተቋማት መካከል አንዱ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (Organization of African Unity - OAU) የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት (African Union - AU) ነው:: የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (Organization of African Unity) መመስረት የዓድዋ ድል ውጤት ነው:: የድርጅቱን ምስረታ፣ ዋና መስሪያ ቤቱ አዲስ አበባ ላይ የመሆኑንና የአፍሪካ አገራትም በዚህ የመስማማታቸውን ነገር ከዓድዋ ድል ውጭ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፤ አይቻልምም::

ለድርጅቱ መመስረት ምክንያት የሆነው የፓን አፍሪካ ንቅናቄ (Pan-Africanism) የተጠናከረውም በዓድዋ ድል ነው:: ምንም እንኳ የፓን-አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ከዓድዋ ጦርነት ቀድሞ የተጀመረ ቢሆንም በዓድዋ የተገኘው ድል ግን የፓን-አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴን ይበልጥ እንዲጠናከር አድርጎታል:: የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዓድዋ ድል ውጤት መሆኑ የዓድዋ ድል የአፍሪካውያን የነፃነት ትግሎችና ከትግሎቹ መጠናቀቅ በኋላ የተመሰረቱ ተቋማት የዓድዋ ድል ደማቅ አሻራ እንዳረፈባቸው ጠቋሚ ምስክር ነው::

የዓድዋ ድል የትብብርንና የአንድነትን ውጤታማነት እንዲሁም ለነፃነት መስዋዕትነት መክፈል ታላቅ ክብር እንደሆነ ያሳየ፤ የነጮች የበላይነት ማክተም እንደሚችልም የጠቆመና መንገድ የከፈተ አንፀባራቂ ክስተትም ነው:: ይህን ክብርና መንገድ በጀግንነትና በመስዋዕትነት በታጀበ ተግባር ያሳዩትና የመሩት ኢትዮጵያውያን ደግሞ የጭቁኖች መመኪያ መሆናቸውን አስመስክረዋል::

> **የዓድዋ ድል በቅኝ ግዛት ስር ወድቀው ለነበሩ የአፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ ፋይዳ እንደነበረው የነፃነት ትግሎቹ መሪዎች የነበሩና በኋላም አገሮቻቸውን በመሪነት ያገለገሉ አፍሪካውያን የትግል መሪዎች መስክረዋል**

በደቡብ አፍሪካ አፓርታይድን ለመታገል በተደረገው ጥረት ኢትዮጵያ እንደነፃነትና ክብር ምልክት ተደርጋ ትወከል ነበር:: ከ1896 እስከ 1897 ዓ.ም ድረስ ሩስያና ጃፓን ያደረጉትና በጃፓን አሸናፊነት የተጠናቀቀው ጦርነት (Russo-Japanese War) ከዓድዋ ድል ጋር ተያያዥነት እንዳለውም በታሪክ ተጠቅሷል:: በአጠቃላይ ዓድዋ ለመላው ዓለም ጭቁኖች የነፃነት ምልክትና የሞራል ምንጭ ሆኗቸዋል:: በተለይ የአፍሪካ አገራት ነፃነታቸውን እንዲጎናጸፉ ትልቅ መሰረት የሆነ ድል ነው:: የአፍሪካ አገራት ነፃ ከወጡ በኋላም የሰንደቅ ዓላማዎቻቸውን ቀለማት የወሰዱት ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት (አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ) ነው::

የዓድዋ ድል በቅኝ ግዛት ስር ወድቀው ለነበሩ የአፍሪካ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ ፋይዳ እንደነበረው የነፃነት ትግሎቹ መሪዎች የነበሩና በኋላም አገሮቻቸውን በመሪነት ያገለገሉ አፍሪካውያን የትግል መሪዎች መስክረዋል:: የመጀመሪያው የጋና ፕሬዚደንት ክዋሜ ንኩርማህ ‹‹ኢትዮጵያ ነፃ ከሆነች ሁላችንም አፍሪካውያን አንድ ቀን ነፃ እንደምንሆን አምናለሁ›› በማለት ነበር የዓድዋ ድል ለአፍሪካውያን የነፃነት ትግል መጠናከር ትልቅ ሚና እንደሚኖረውና በአትዮጵያም ያላቸውን ሙሉ ተስፋ የተናገሩት::

የመጀመሪያው የጊኒ ፕሬዚደንት አሕመድ ሴኮ ቱሬ ደግሞ ‹‹ ... ኢትዮጵያውያን ታላቅ ሕዝቦች ናቸው:: ጀግና አፍሪካውያን ናቸው:: በጀግንነት ተዋግተው ነፃነታቸውን አስከብረዋል፤ ለመላው አፍሪካውያንም የነፃነትን መንገድ አሳይተዋል›› በማለት ለኢትዮጵያውያን ጀግንነትና ለዓድዋ ድል አበርክቶዎች እውቅና ሰጥተዋል::

የፀረ-አፓርታይድ መሪውና የደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዚደንት ኔልሰን ማንዴላ የፀረ-አፓርታይድ ትግል መሪ በነበሩበት ወቅት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና እንደወሰዱ በታሪክ ተመዝግቧል:: ‹‹ኢትዮጵያ ምንጊዜም በውስጤ ልዩ ቦታ አላት:: ወደ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ከመሄድ ይልቅ ወደ ኢትዮጵያ መጓዝ የበለጠ ልዩ ስሜት ይሰጠኛል፤ አፍሪካዊ ወዳደረገኝ የማንነቴ ምንጭ እንደሄድኩ ይሰማኛል›› በማለት የተናገሩላት የዓድዋ ድል ባለቤቷ ኢትዮጵያ ለትግላቸው ያደረገችላቸው ድጋፍ ትርጉሙ ብዙ ነው። ምስክርነታቸውም ከዓድዋ ድል ታሪክ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ጥርጥር የለውም::

የማንዴላ ተተኪ ታቦ ምቤኪም የዓድዋ ድል ለጥቁሮች፣ በተለይም ለአፍሪካውያን፣ የነፃነት ትግል ስለነበረው ፋይዳ ተናግረው አይጠግቡም:: ‹‹የዓድዋ ድል ለትናንት ድሎቻችን ብቻም ሳይሆን ልናሳካቸው ላሰብናቸው አፍሪካዊ እቅዶቻችን ስኬት ታላቅ ስንቅ የሚሆነን አኩሪ ድል ነው›› በማለት በተደጋጋሚ ተናግረዋል::

በዓድዋ ጦርነት ላይ ብዙ ጥናቶችን ያደረጉትና የምርምር ጽሑፎችን ያሳተሙት የታሪክ ተመራማሪው ፕሮፌሰር አየለ በከሪ፣ የዓድዋ ድል፣ ነፃነትን አጥብቆ የሚሻ አዲስ የአፍሪካዊነት ስሜት እንዲጎለብት ማድረግ የቻለ ታሪካዊ ድል እንደሆነ ይገልፃሉ:: እሳቸው እንደሚያስረዱት፤ ኢትዮጵያ ያስመዘገበችው አንፀባራቂ ድል የአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት ንቅናቄዎች ምልክት መሆን የቻለ ወሳኝ ታሪካዊ ክስተት ነው። ጦርነቱና ድሉ ኢትዮጵያውያን ለጋራ ዓላማ በጋራ ተሰልፈው ዓለምን ያስደነቀ ገድል መፈፀማቸውን ለመላው ዓለም ያሳዩበት በመሆኑ ጭቁን ሕዝቦች ለነፃነታቸው በጋራ ሆነው መታገል እንደሚገባቸው ትምህርት ሰጥቷል::

ፕሮፌሰር አየለ ‹‹The Victory of Adwa : An Exemplary Triumph For The Rest of Africa›› በሚለው ጽሑፋቸው የደጃዝማች ዘውዴ ገብረሥላሴን (ዶ/ር) ሃሳብ ይጠቅሳሉ:: አምባሳደሩ ስለጦርነቱና ድሉ በገለፁበት ማብራሪያቸው፣ ‹‹የዓድዋ ድል የአውሮፓን ሰማዮች የሀዘንና የድንጋጤ ደመና ያለበሰ፤ በአንፃሩ በቅኝ ገዢዎች እየተበዘበዙ ለነበሩ ጭቁን የአፍሪካና የእስያ ሕዝቦች ደግሞ የነፃነት ተስፋን የፈነጠቀና የጀግንነት ወኔን ያላበሰ ደማቅ ድል ነው›› በማለት ይገልፁታል::

ከዚህ የደጃዝማች ዘውዴ ገለፃ መረዳት የሚቻለው የዓድዋ ድል ንዝረቱ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም እንደተሰማ እንዲሁም የድሉ ትሩፋቶች ለጭቁን ሕዝቦች የነፃነት ትግል ትልቅ የሞራል ስንቅ እንደሆኑና ትግሎቹም ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ የስኬት መንገድን የጠረጉ ታሪካዊ አጋጣሚዎች እንደነበሩ ነው::

የታሪክ መምህርና ተመራማሪው ፕሮፌሰር ገላውዴዎስ አርዓያ፣ በ1988 ዓ.ም፣ በዓድዋ ድል 100ኛ ዓመት መታሰቢያ ላይ፣ ‹‹The Ethiopian Victory at Adwa : Meanings For Africans and People of African Descent in The Diaspora›› በሚል ርዕስ በሐዋርድ ዩኒቨርሲቲ ባቀረቡት ገለፃ፣ ታላላቅ ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የድሉን ዜና ለመላው ዓለም ማስተጋባታቸውን ጠቁመው፣ የድሉ ብስራት በአፍሪካ፣ በእስያ፣ በአሜሪካና በካሪቢያን አካባቢዎች ከፍተኛ መነቃቃትን እንደፈጠረ አስረድተዋል:: ቅኝ ገዢ ኃይሎችም የዓድዋ ድል ታላቅ ድንጋጤና ፍርሃት እንዳሳደረባቸውም ፕሮፌሰር ገላውዴዎስ ተናግረዋል::

የዓድዋ ድል የኢትዮጵያውያን ብቻ እንዳልሆነ የጠቀሱት ፕሮፌሰር ገላውዴዎስ፣ ድሉ በመላው ዓለም በሚገኙ የአፍሪካ ዝርያ ባላቸው ጥቁር ሕዝቦች መካከል የወንድማማችነትና የትብብር መንፈስ እንዲፈጠረም አብራርተዋል:: ‹‹የዓድዋ ድል የአፍሪካ የነፃነት ብቻ ሳይሆን፣ የአፍሪካዊ ስልጣኔ ኅዳሴ ምልክት ጭምር ነው›› ብለዋል::

ስመጥሩ የታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና የፓን አፍሪካዊነት አቀንቃኝ ዊሊያም ኤድዋርድ ዱ ቦይስ ‹‹በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር የወደቁ ሕዝቦች ከዓድዋ ድል በመማር የነፃነት ትግሎቻቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል። በርትተው ለመታገል ቁርጠኛ በመሆን በነፃነት መኖርን ለድርድር እንደማያቀርቡት ለመላው ዓለም ማሳወቅ አለባቸው፤ ከኢትዮጵያ መማር ያለባቸውም ይህን እውነት ነው›› በማለት የዓድዋ ድል ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ትግል መነሻና ስንቅ እንደሆነ ለጭቁኖች መልዕክት አስተላልፈው ነበር::

የ‹‹Roots of Rastafari›› መጽሐፍ ጸሐፊዋ ቨርጂኒያ ሊ ጃኮብስ፣ የዓድዋን ድል ‹‹ኢትዮጵያ ዘረኛና ከፋፋይ የሆነውን የአውሮፓውያን የቅኝ ግዛት ተግባርን በመቃወምና ድል በማድረግ የማይነቃነቅ ግዙፍ የክብር ማማ እንድትገነባና በድል የታጀበ ተጋድሎዋ ለሌሎች አፍሪካውያን የነፃነት ትግል አርዓያ እንድትሆን ያስቻላት ተምሳሌታዊ ድል›› በማለት ገልጸውታል::

ሮበርት ኔስታ ማርሌይ (ቦብ ማርሌይ)ን ጨምሮ ስመጥር የኪነ-ጥበብ ሰዎች በልብሶቻቸውና በሙዚቃ መሳሪያዎቻቸው ላይ አረንጓዴ-ቢጫ-ቀይ ቀለማትን መጠቀማቸውና ከ30 በላይ የአፍሪካ፣ የላቲን አሜሪካና የካሪቢያን አገራት ለሰንደቅ ዓላማዎቻቸው እነዚህኑ ቀለማት መምረጣቸው የአጋጣሚ ጉዳይ ሳይሆን ኢትዮጵያና በዓድዋ ያስመዘገበችው ደማቅ ድሏ የጭቁኖች መመኪያ በመሆናቸው ነው::

ጥቁሮች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ የዓድዋ ድል ትዝታና ስሜት ነበር:: ጭቁኖች ኢትዮጵያን የነፃነት ምልክትና የጥቁሮች ሁለተኛ ቤት አድርገው ነው የሚመለከቷት:: ‹‹ኢትዮጵያ ሀገራችን ናት›› ብለው ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት እንቅስቃሴ ሲያደርጉም ነበር:: በተለይ ጃማይካዊው የፖለቲካ አክቲቪስትና የመብት ተሟጋች ማርከስ ጋርቬይ በንግግሮቹና በጽሑፎቹ ላይ ‹‹በባርነት ተይዛችሁ በዘር አድልኦ በሽታ በተጠናወተው ኅብረተሰብ ውስጥ የምትኖሩ ጥቁር አፍሪካውያን በሙሉ ወደ አገራችሁ ወደ አፍሪካ፣ የነፃነት አገር ወደ ሆነችው ሀገራችሁ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። ፊታችሁን ወደ ኢትዮጵያ መልሱ፤ ወደ ጥንት ርስታችሁ ወደ አፍሪካ ተመለሱ፤ ዘውዱን የደፋውን ጥቁር ንጉሥ ተመልከቱ፤ እርሱ አዳኛችን ነው›› እያለ ደጋግሞ መጥቀሱ ኢትዮጵያ የጭቁኖች ተስፋና መመኪያ ተደርጋ መቆጠሯን የሚጠቁም ነው።

በአጠቃላይ የዓድዋ ድል ለጭቁን ሕዝቦች፣ በተለይም ለአፍሪካውያን፣ የነፃነት እንቅስቃሴዎች ሂደትና ስኬት ደማቅ አበርክቶ እንደነበረው ከአገራት መሪዎች፣ ከምሁራንና ከታዋቂ ሰዎች የተሰጡ ምስክርነቶች ያስረዳሉ:: እነዚህ ስለዓድዋ ድል አስደማሚነትና ዘመን አይሽሬ አበርክቶዎች የተሰጡ ምስክርነቶች ኢትዮጵያ በዓለም የነፃነት ትግልና የጀግንነት ታሪክ የማይነቀነቅ ታላቅ የከፍታ ስፍራ እንዳላት የሚያረጋግጡ ዘመን ተሻጋሪ ማስረጃዎች ናቸው::

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# የዓድዋ ድል ሥጋ ለብሶ የታየበት የዘመኑ ትውልድ ስኬት

**ፍሬሕይወት አወቀ**



ፎቶ- በረሁ ታደሰ

ከኢትዮጵያውያን አልፎ የአፍሪካውያን ኩራት በመሆን ዘመናትን የተሻገረው የዓድዋ ድል ዛሬም ሕያው ነው፡፡ በትውልድ ቅብብሎሽ ለበርካታ ዓመታት ሲዘከር መኖሩም ከታሪኩ ግዝፈትና ጥልቀት የተነሳ መሆኑ ዕሙን ነው፡፡ በደም የተጻፈው ይህ የ128 ዓመት ታሪክ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ቢኖረውም ሁነቱን የሚዘክር መታሰቢያ ሳይኖረው ክፍለ ዘመን ተሻግሯል፡፡ ዛሬ ግን ጥበቃው አብቅቶ ግዙፉን የዓድዋ ድል የሚያህል መታሰቢያ ሙዚየም በመሐል ፒያሳ ተገንብቷል፡፡

ሙዚየም የተገነባበት ቦታ ኢትዮጵያውያን ለነፃነታቸው ሲሉ ለሕይወታቸው ሳይሳሱ ወደ ጦርነት ለመትመም በአንድነት በተሰባሰቡበት መሐል አዲስ አበባ ፒያሳ ላይ መሆኑም ታሪካዊ ያደርገዋል፡፡ የ128 ዓመት ታሪክ ሥጋ ለብሶ መታየት የቻለበት ይህ ሙዚየም የታሪኩን ግዝፈት በልኩ ማሳየት የቻለ የዘመኑ ትውልድ ሌላኛው ዓድዋ ነው ቢባል ከዕውነት የራቀ አይሆንም። ዓድዋ ሁሌም አዲስና ረቂቅ እንደመሆኑ አሁን ያለው ትውልድ ‹‹የእኔ ዘመን ስኬት ነው›› በሚል ሊጠብቀው፣ ሊንከባከበውና ለመጪው ትውልድ ሊያሻግረው እንደሚገባ ይታመናል፡፡

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በየትኛውም ዘመን ያልታየ የዘመኑ ስኬት ስለመሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የዓድዋ ድል የመላው ኢትዮጵያውያን ድል እንደመሆኑ መታሰቢያ ሙዚየሙም እንዲሁ የመላው ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያውያን ከራሳቸው አልፎ ለጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነው የድል ታሪካቸውን የሚዘክሩበትና ለትውልድ የሚያስተላልፉበት ብሎም ለዓለም የሚያስተዋውቁበት የጋራ ቤታቸው ነው፡ ፡

የዓድዋ ድል እጅግ ግዙፍና ረቂቅ እንደመሆኑ የታሪኩን ግዝፈት ከፍ ማድረግ የሚችል መታሰቢያ ሙዚየም መገንባቱ የዘመኑ ድል ነው የሚሉ ብዙዎች ናቸው፡፡ የዓድዋ ድል ግዙፍነት እንዲሁም ረቂቅ ሚስጥር በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ደምቆ የተጻፈ ቢሆንም እስከዛሬ ድሉን ማጣጣምና ዕውነታውን ፍንትው አድርጎ ማሳየት የሚችል ሥፍራ አልነበረውም። ይሁንና አሁን ላይ ይህ ታላቅ ድል ገዝፎ መታየት የሚችልበት መታሰቢያ ሙዚየም መገንባት መቻሉ ትልቅ ስኬት ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

ሙዚየሙ ከዓድዋ ድል ታሪክ ባለፈም የኢትዮጵያን የታሪክ ከፍታ ማሳየት የሚችልና በወቅቱ የተከፈለውን መስዋዕትነት ፍንትው አድርገው የሚገልጡ የተለያዩ ቅርሶች በውስጡ የያዘ በመሆኑ ትውልዱ ሥጋ የለበሰውን ይህን ታሪክ የማወቅ፣ የመረዳትና ለሌሎች የማስተላለፍ ወርቃማ ዕድል ገጥሞታል፡፡

በመሆኑም ወጣቱ ትውልድ እንደ ጀግኖች አባቶቹ ሁሉ የጋራ አንድነቱን በማጠናከር ሠላሙን ማጽናት ይጠበቅበታል የሚሉት የታሪክ ምሁራን በተለይም አሁን ያለው ትውልድ ከ128 ዓመታት በኋላ የተገነባው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም የነፃነት፣ የሉዓላዊነትና የአርበኝነትን ልክ ማሳያ መሆኑን በመረዳት ለመጪው ትውልድ የማሻገርና የማስተማር ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

የሁሉም የጥቁር ሕዝቦች የትግል መነሻ ተደርጎ የሚወሰደው የዓድዋ ድል ታላቅ ድል መሆኑን የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ናቸው። እሳቸው እንዳሉት የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የዓለም ሕዝብ ኩራቴ፣ ተምሳሌቴ፣ ፋናዬ ነው የሚለው ትልቅ ድል ነው፡፡ ‹‹እኛ ኢትዮጵያውያን ግን እስካሁን ድረስ ይህን ታላቅ ድል የሚመጥን መታሰቢያ ማቆም አልቻልንም ነበር፡፡ ዛሬ ላይ ግን ይህን ቁጭት የሚቀይር ፕሮጀክት መገንባቱ እጅግ የሚያኮራ ነው›› ይላሉ፡፡

እሳቸው እንዳሉት የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በወቅቱ የነበረውን ሁነት ቁልጭ አድርጎ ማሳየት የሚችል ነው፡፡ በዓድዋ ዘመቻው በጦርነቱ ወቅት ተሳታፊ የነበሩ ጀግኖቻችን፣ ሴቶቻችን፣ ገበሬዎቻችን ይዘው የነበሩትን ቅርሶች በሙሉ አሰባስቦ የያዘ ታላቅ ሙዚየም ነው። ከጦር መሣሪያ ጀምሮ እስከ የዕለት ተዕለት ምግብ መመገቢያ ያሉትን የዓድዋ ዘማች አርበኞች መገልገያ ቁሳቁሶች አሟልቶ ይዟል፡፡ እነዚህን ቁሳቁሶችን በአንድ ቦታ አሰባስቦ ማሳየት ማለት ደግሞ አሁን ላለው ትውልድ ትልቅ ዕውቀት ማስገንዘብ ማለት ነው፡፡

ሌላው ዓድዋን በልኩ ለማስረዳትና ለመግለጽ ሥነ-ጥበብን በመጠቀም ማስረዳት አለብን የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ሥነ-ጥበብ ላይ የተለያዩ ቅርጾች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፤ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ውስጥ እንዲሁ የተካተቱት በርካታ ቅርጾች መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡ እሳቸው እንዳሉት ጦርነቱ ምን ይመስል እንደነበር የሚያሳዩ በርካታ ቁሳቁሶች በሙዚየሙ ይገኛል፡፡ ጦርነቱም በምናብ ብቻ የሚታይ ሳይሆን በወቅቱ ከነበሩ ስዕሎች፣ ስኬቾችና ከየተለያዩ ቁሳቁሶች የተነሳና ያካተተ እንደሆነም አስረድተዋል። ዓድዋ ከቅርሶቹ ባሻገር ለትውልድና ለቀሪው ዓለም ማሳየት ይቻላል የሚሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ ለዚህ ሥነ ጥበብ አንዱ መንገድ ነው ይላሉ። በዓድዋ መታሰቢያ ውስጥ የተገነቡ ቅርፆች (የጀግኖች መሪዎችና የጦር ጀነራሎች ሐውልቶች) መኖራቸውንም ገልጸዋል።

የሠላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታና በታሪክና ባሕል ላይ ጥናትና ምርምር ደረጉት ዶክተር ኬይረዲን ተዘራ በበኩላቸው፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም የታሪክ ባዶነት እንዳይሰማን ያደረገ፤ ሁሉ ነገራችን ገዝፎና የልኬታችን ልክ ሆኖ መገንባቱን አንስተዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ከዓድዋ አስቀድሞም በተለያዩ ግንባሮች ላይ ሀገራቸውን ነፃ ለማውጣት የታገሉና ድል ያደረጉ ቢሆንም ትግላቸው በአንድ አካባቢ ወይም ነጠላ በሚባለው መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን መላው ኢትዮጵያውያንን በአንድ አሰባስቦ ድል ማድረግ የተቻለው በዓድዋ በመሆኑ የዓድዋ ድል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድል ነው ይላሉ፡፡

‹‹የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ያሰባሰበና መነበብ የሚችል መታሰቢያ ሙዚየም መሆኑን ሲያስረዱ፤ ኢትዮጵያን በአግባቡ ለተረዳና በቀና ልብ ለሚመለከተው ማንም ሰው የለውም የሚልበትን ዕድል በሙሉ የዘጋና የሚነበብ ነው›› ይላሉ። እሳቸው እንደሚሉት በሀገሪቱ በርካታ ፕሮጀክቶች የተገነቡ ቢሆንም የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ግን ቀደም ሲል መገንባት የነበረበት ትልቅ ፕሮጀክት ነው። ሙዚየሙ ኢትዮጵያውያንን የሚያሳስብና ሊያሰባስብ የሚችል መሆኑን ግዙፍ ፕሮጀክት ነው ይላሉ፡፡

በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ውስጥ ያልተካተተ ኢትዮጵያዊ የለም የሚሉት ዶክተር ኬይረዲን ከብሔር፣ ከፆታና ከጀግኖች የቀረ አለመኖሩን አንስተው ሙዚየሙ ኢትዮጵያን ለማቆም የተከፈለ መስዋዕትነትን ለማሰብ የቆመ እንደመሆኑ ከመታሰቢያነቱ ባሻገር ኢትዮጵያውያንን አንድ ሊያደርግ፣ ሊያሰባስበንና አናሳ የሆኑ ትርክቶች ቦታ እንዳይኖራቸው በማድረግ ኢትዮጵያውያን ገዝፈን እንድንታይ ያደረገ ግዙፍ ፕሮጀክት እንደሆነ ያላቸውን እምነት ገልጿል፡፡

ዶክተር አየነው ማሞ በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት፤ የዓድዋ ድል መላው ኢትዮጵያዊ ከጫፍ እስከ ጫፍ መስዋዕትነት የከፈለበትና ለነፃነቱ የታገለበት ታላቅ ድል ነው፡፡ በመሆኑም ለጥቁር ሕዝቦች ጭምር መመኪያና ኩራት ሆኗል ይላሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ድሉ አቻ የማይገኝለት የአፍሪካውያን ድል ነው፡፡ ከዛም አልፎ የመላው ጥቁር ሕዝቦች ድል በመሆኑ ከፍ ያለና ትልቅ ምስጢር ያለው ነው።

‹‹ነፃነቱን አጥቶና ለጠላት ተገዝ ሆኖ መኖር ለኢትዮጵያውያን ጀግኖች የማይዋጥ የጉሮሮ አጥንት ነበር›› የሚሉት ዶክተር አየነው፤ የድሉ ባለቤት መሆን የቻሉት ኢትዮጵያውያን በወቅቱ አንድነታቸውን ማጠናከር በመቻላቸው መሆኑን ያስረዳሉ፤ በዓድዋ ጦርነት ኢትዮጵያውያን በሠለጠነ ወታደርና በዘመናዊ መሣሪያ የተቃጣባቸውን ወረራ በአልበገር ባይነት በሀገር ፍቅር ስሜት፣ በጋራ በመቆም የድል ባለቤት መሆን ችለዋል። አሁንም ያለው ትውልድ ልዩነቱን ወደ ጎን በመተው በአንድነት ቆሞ የጋራ ታሪኩን ማጣጣምና ለመጪው ትውልድ ብሎም ለዓለም ማስተዋወቅ አለበት፡፡

ለዓድዋ ድል ስኬት ዋናው ምክንያት ኢትዮጵያውያን ያለምንም ልዩነት በአንድነት ሆነው የሰጡት ፈጣን ምላሽ አንዱ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር አየነው፤ ይህም እጅግ የሚያስገርም ድንቅ ዕውነታ እንደነበር ነው ያስታወሱት፡ ፡ ‹‹ሕዝቡ በተለይም የንጉሠ ነገሥቱን የክተት አዋጅ ተቀብሎ በፍጹም ቆራጥነት፣ በልበሙሉነትና በድፍረት ጦርነቱን መቀላቀሉ ለድል አብቅቶታል፡፡ አንድነት ትልቅ ጉልበት በመሆኑ የጋራ ጠላትን በጋራ ለመመከት አስችሎታል›› በማለት አሁን ያለው ትውልድም ልዩነቱን ወደ ጎን በመተው ሀገራዊ በሆኑ አጀንዳዎች አንድ መሆን እንዳለበትና ዳግማዊ ዓድዋን መፍጠር እንደሚገባው ነው የተናገሩት፡፡

የዓድዋ ድል አከባበርን አስመልክቶም እሳቸው እንደሚሉት፤ ዓድዋ ግዙፍ እንደመሆኑ የገዘፈ አከባበር፣ የገዘፈ መታሰቢያና ማስታወሻ ያስፈልገዋል፡፡ ምክንያቱም ይላሉ፤ ምክንያቱም የዓድዋ ድል ሩቅ መንገድ የመጓዝና ብዙ ትውልድን የማስተማር አቅም ያለው ነው፡፡ ስለዚህ በታላቅ ክብርና ድምቀት መከበር ያለበት በዓል ነው፡፡ ለዚህም ሙዚየሙ አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ሲሆን፤ የዓድዋ ድል በኢትዮጵያ ብቻ መከበር የለበትም ባይ ናቸው፡፡ እሳቸው እንደሚሉት ድሉ ለአፍሪካውያን ነፃ መውጣት አርዓያ እንደመሆኑ የዓድዋ ድል በዓል በመላው አፍሪካ መከበር ያለበት የድል በዓል ነው በማለት ሲያስረዱ፤

የዓድዋ ድል ሲከበር ለሀገር ፍቅር ተዋድቀው ለዚህ ታልቅ ድል ያበቁንን አባቶቻችንን ከመዘከር ጎን ለጎን የድሉ ተጠቃሚ ለሆነው ለዘመኑ ትውልድ ታሪኩን የጋራ በማድረግ ማስተላለፍ ተገቢ እንደሆነ በመጥቀስ ጭምር ነው፡፡ በተለይም የዓድዋ ድል ለወጣቱ ትውልድ ያለውን አንድምታ በማሳየት ትውልዱ የመላው ኢትዮጵያዊ ድል መሆኑን አምኖ በመቀበል ሊኮራበትና ሊሠራበት እንደሚገባ አንስተው፤ የዓድዋ ጦርነት የኢትዮጵያውያን አንድነት ጎልቶ የታየበት ታሪካዊ መድረክ መሆኑ በተለይም ወጣቱ ትውልድ የነፃነትና የአንድነትን ትርጉም ማወቅ፣ መረዳትና በተግባር ማዋል ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ጦርነቱ የኢትዮጵያን ነፃነት ከማስከበር ባሻገር ብሔራዊ ስሜት በከፍተኛ ደረጃ እንዲጎለብትና ስር እንዲሰድ አድርጓል ይላሉ፡፡

‹‹ከዚህ እውነታ የምንማረው የትኛውንም አይነት የሀሳብ ልዩነት ቢኖር በሀገራዊ ጉዳይ ላይ የጋራ አመለካከትና ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊና አዋጭ ነው›› የሚሉት ዶክተር አየነው፤ በዚህ ረገድ የዓድዋ ድል አሁን ላለው ትውልድ ነፃነቱን በዘላቂነት ለማስጠበቅ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው። ለዚህም ትውልዱ በራስ የመተማመን ባሕል ማዳበርና ታሪክን ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ታሪክን ለማወቅ ደግሞ የታሪክ ትምህርት መማር አንዱ መንገድ ነው። ታሪክን ከመማርና ከመዘከር ባለፈም ትውልዱ እንደ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ሁሉ የገዘፈ ታሪክ በዘመኑ መሥራት ይጠበቅበታል፡፡

ሙዚየሙን ኢትዮጵያውያን በሙሉ እንዲሁም አፍሪካውያን ማየት አለባቸው ያሉት ዶክተር አየነው፤ ሙዚየሙ ግዙፉን የዓድዋ ድል ታሪክ የሚያሳይ በመሆኑ ኢትዮጵያውያኑም ሆኑ የአፍሪካ መሪዎች ዳግማዊ ዓድዋ፤ የክፍለ ዘመኑ ትልቅ ድል አድርገው መውሰድ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡ በተለይም ሙዚየሙ የያዘውን ዕውነታ ለትውልድ የማስተማር፣ የመጠበቅ፣ የማስተላለፍና የማስተዋወቅ ኃላፊነት ጭምር ከዚህ ትውልድ ይጠበቃል። ምክንያቱም ‹‹ነጮች በጥቁሮች አይሸነፉም›› የሚለውን ለዘመናት የቆየ ትርክት መቀየር የቻለና የጥቁር ሕዝቦችን ታሪክ የያዘ ትልቅ ሙዚየም በመሆኑ ነው፡፡

የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም የሚኮሩበት፣ ብዙ ቁም ነገር የሚማሩበትና ሁልጊዜም ቢሆን ትኩስ የድል ስሜትን የሚፈጥር ታሪክ እንደመሆኑ ወጣቱ ትውልድ ከዚህ ታሪክ ብዙ መማርና ታሪኩን ማወቅ መረዳት እንደሚገባው ያነሱት ዶክተር አየነው፤ ድሉ በታሪኩ ግዝፈት ልክ መከበርና መዘከር እንዳለበትም ያነሳሉ፡፡ በቀጣይም በደመቀ መልኩ መከበር እንዲችል ትውልዱ በሁሉም ዘርፍ ዘመኑ የሚጠይቀውን ሥራ ጠንክሮ መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

በመጨረሻም የቀደሙ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን የፈጸሙትን አኩሪ ታሪክ ትውልዱ በልኩና በክበሩ በመዘከር፤ በማስታወስ፤ ከሚከፋፍል ጉዳይ ወጥቶ በጋራ ልማትና የአገር ዕድገት ላይ ትኩረት በማድረግ፤ መተባበርን እና አንድነትን ከዓድዋ ድል መማር ከሁሉም ይጠበቃል በማለት አበቃን!

# ለዓድዋ ድል የሚመጥን ሰብዕና ይኑረን!

ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ

መላውን ዓለም ያስገረመው፣ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገውና ኢትዮጵያ የጭቁኖች የነፃነት ምልክትና መሰረት ሆና እንድትታይ ያስቻለው ታላቁና አንጸባራቂው የዓድዋ ድል፣ ኢትዮጵያን የአኩሪ ታሪክ ባለቤት ያደረገ ብቻ ሳይሆን፤ በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስኮች ብዙ እድገቶችንና መሻሻሎችን እንድታስመዘግብ የሚያስችሉ በርካታ ትሩፋቶች ያሉት ታሪካዊ ክስተት ነው።

የዓድዋ ድል ከኢትዮጵያ አልፎ ለመላው ዓለም ጭቁኖች የነፃነት ተስፋን የፈነጠቀና ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ ያደረገ አስደናቂ ገድል ነው። የአፍሪካ የፀረ-ቅኝ ግዛት ንቅናቄዎች ምልክት መሆን የቻለ ወሳኝ ታሪካዊ ክዋኔም ነው። በአፍሪካ፣ በካሪቢያንና በእስያ ለተካሄዱ የነፃነት ትግሎች መጀመርና ስኬታማ መሆን የዓድዋ ድል የጎላ ሚና ነበረው።

የፓን አፍሪካዊነት ንቅናቄ (Pan-African-ism) የተጠናከረውም በዓድዋ ድል ነው። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (OAU) መመስረት የዓድዋ ድል ውጤት ነው። የድርጅቱን ምስረታ፣ ዋና መስሪያ ቤቱ አዲስ አበባ ላይ የመሆኑንና የአፍሪካ አገራትም በዚህ የመስማማታቸውን እውነት ከዓድዋ ድል ውጭ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፤ አይቻልምም።

በድሉ ማግሥት ታላላቅ የአውሮፓ መንግሥታት ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት መስርተዋል። ከድሉ በፊት ‹‹ኢትዮጵያውያን ኋላ ቀሮች ናቸው›› ብለው ያስቡ የነበሩ አካላት ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅነት መስርተው የምጣኔ ሀብትና ወታደራዊ ግንኙነት ለመፍጠር ፍላጎት አሳይተዋል። የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ዋና ከተማ (አዲስ አበባ) የብዙ አውሮፓውያን መንግሥታት ኤምባሲዎች መቀመጫ እንድትሆን እድል ፈጥሯል። ድሉ ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት (ለከተማ እድገት መነቃቃት፣ ለመሰረተ ልማቶች መገንባትና ለሥራ እድል መፈጠር) ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። ኢትዮጵያ ‹‹የዓለም መንግሥታት ማኅበር›› (League of Nations)ን ጨምሮ የሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት መስራች አባል እንድትሆን ድሉ ከፍተኛ ሚና ነበረው። በአጠቃላይ የዓድዋ ድል ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ እውቅና እንድታገኝ አስችሏታል።

ከላይ የተጠቀሱትን የዓድዋ ድል ያስገኛቸውን በጎ ውጤቶችን (መልካም አጋጣሚዎች) ይዘን ‹‹ድሉ ያስገኛቸውን ትሩፋቶች በሚገባ መንዝረን ተጠቅመንባቸዋል? በድሉ የተገኙትን ውጤቶች በማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ዘርፎች የበለፀገችና ጠንካራ የሆነች ሀገርን ለመገንባትስ ተጠቅመንባቸዋል?›› ለሚለው ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ አናገኝም!

የዓድዋ ድል ትሩፋቶችን እያሰብን የኢትዮጵያን ያለፉት።ን ዓመታት (በተለይ ያለፉትን 50 ዓመታት) ጉዞ ስንቃኝ ‹‹ለመሆኑ ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያንና የዓድዋ ድል ይተዋወቃሉ?›› ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። ሀገሪቱ በድህነት፣ በግጭት፣ በዘረኝነትና በጦርነት ጎዳናዎች ላይ ደጋግማ መመላለሷ የዓድዋ ድል ያስገኘላትን በረከቶች መዘንጋቷንና አለመጠቀሟን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ነፃነት፣ ክብርና አንድነት ሲሉ በዓድዋና በሌሎች ስፍራዎች ለማመን የሚከብዱ ከባድ ተጋድሎዎችን አድርገው ነፃ አገር ለ‹‹ተተኪው ትውልድ›› ቢያስረክቡም ‹‹ተተኪው ትውልድ›› (በተለይ ልኂቃኑ) ግን ያን ታሪክ በሚገባ በማወቅና በመመንዘር ለሀገር ግንባታ ሊጠቀምበት አልቻለም። ይህ መራራ እውነት እጅግ ያሳዝናል፤ ያሳፍራልም።

ኢትዮጵያ በዘር፣ በሃይማኖትና በአመለካከት ሳይከፋፈሉ ዓድዋ ላይ ጠላትን ድል ያደረጉ ልጆች እናት መሆኗን ማሰብና፣ ከዓድዋ ድል በኋላ ባፈራቻቸው ‹‹ልጆቿ›› ምክንያት በአስከፊ የዘር ፖለቲካ ስትታመስ መመልከት እጅግ አሳዛኝና አስገራሚ ተቃርኖ ነው። ይህ ውድቀት ደግሞ ‹‹በእውነቱ ይህ የታላቁን የዓድዋ በረከቶች የዘነጋ ትውልድ ድሉን የማክበር/የመዘከር ሞራል አለው?›› የሚል ጥያቄን ይጋብዛል።

የዓድዋ ድል ያስገኘልንን በረከቶች መንዝረን ተጠቅመንባቸው ቢሆን ኖሮ ... ዛሬ በዓባይ ወንዛችን ላይ በምንገነባው ግድባችን ምክንያት ‹‹ጥቅሜ ተነካ›› የሚሉ አካላትና የእነርሱ ወዳጆች ጫና ሊያደርጉብን እንዲሁም ታሪካዊና ሕጋዊ መብታችንን በአደባባይ ሊነጥቁን አይሞክሩም ነበር። [በነገራችን ላይ የዓድዋ ድል በዓባይ ወንዛችን ላይ እየገነባነው እንዳለው ዓይነት ግዙፍ የልማት ስራዎችን እንድንሰራ ስንቅ የሚሆን ድል ነበር] ... የዓድዋን በረከቶች ብናውቃቸውና ብንጠቀምባቸው ኖሮ በብሄርና በፖለቲካ የሚታመስ፣ ሚሊዮኖች በችጋር የሚሰቃዩባትና የሚፈናቀሉባት .... ሀገር አትኖረንም ነበር!

የዓድዋ ድል ሀገርን ከጠላት ወረራ ከመጠበቅ ያለፈ ዓላማና ትርጉም ነበረው። በእርግጥ ድሉ ኢትዮጵያን ከወራሪ ኃይል ጠብቆ የማቆየት አኩሪ ታሪክ እንደሆነ ባይካድም ቀደምት ኢትዮጵያውያን ከወራሪው የኢጣሊያ ጦር ጋር የተፋለሙት ኢትዮጵያን ከወቅቱ ወራሪ ኃይል ለመጠበቅ (ዳር ድንበሯን ለማስከበር) ብቻ ሳይሆን ወራሪው ኃይል ውሎ አድሮ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ የሚያደርሰውን ጥፋት በመገንዘብ ያን ጥፋት በእንጭጩ ለመቅጨት ጭምር እንደሆነ መዘንጋት አይገባም።

ድሉ ያስገኘውን መልካም ፍሬ መንዝሮ ማኅበረሰባዊ ንቃት ያዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀች በአጠቃላይ ኃያል የሆነች ኢትዮጵያን እውን ማድረግ የድሉ ዘላቂ ዓላማና ትርፍ ሊሆን ይገባ ነበር። የዓድዋ ድል የትብብርና የአንድነት ውጤት መሆኑን ተገንዝበን ኢትዮጵያን በትብብርና በአንድነት ካለችበት ዘርፈ ብዙ መከራና ችግር ማላቀቅ ያልቻልነው ለምን ይሆን?

ቀደምት ኢትዮጵያውያን ባስገኙት ድል መኩራትና ድሉን መዘከር ጥሩ ቢሆንም የድሉን ትሩፋቶች ሳይጠቀሙ፣ ድሀ የሆነች ሀገር ይዞ በድሉ ‹‹መኩራት›› ብቻ ግን ግራ የሚያጋባ ይመስለኛል። በዓድዋ ለመኩራት ዓድዋን ማወቅና መጠቀም ይገባል! ለመሆኑ ዓድዋን ማባከናችን የሚቆጨን መቼ ይሆን?

የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንትና የዓድዋ ድል ለጥቁሮች፣ በተለይም ለአፍሪካውያን፣ የነፃነት ትግል ስለነበረው ፋይዳ ተናግረው የማይጠግቡት ታቦ ምቤኪ፣ ‹‹የዓድዋ ድል ለትናንት ድሎቻችን ብቻም ሳይሆን ልናሳካቸው ላሰብናቸው አፍሪካዊ እቅዶቻችን ስኬት ታላቅ ስንቅ የሚሆነን አኩሪ ድል ነው›› በማለት በተደጋጋሚ የሚናገሩት የድሉ መታሰቢያ መከበር ከድሉ መንፈስና ዓላማ ለመነጩት አፍሪካዊ እቅዶች ስኬት ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖረው በማመን ነው።

የዓድዋ ድል በማኅበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ መስኮች ጠንካራና ኃያል የሆነች ሀገር ለመገንባት የሚያስችል እምቅ አቅም ያለው ድል መሆኑን መረዳትና መቀበል ያስፈልጋል። የዓድዋን ድል ያስገኘልንን በረከቶች አውቆ እየመነዘሩ መጠቀምና ማኅበረሰባዊ ንቃት ያዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገች፣ ልዩነቶችን አስማምታ አንድነቷን የጠበቀችና ኃያል የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር (መገንባት) የድሉን ትርጉም የማወቅ ንቃት ነው። ይህን በመተግበር ኢትዮጵያን ለታላቁ የዓድዋ ድል የምትመጥን ታላቅ ሀገር ማድረግ ይገባል!

## ዓድዋ

ነጭ ፋሺስት የተመኛት፣
ክብሯን ገፎ ሊያሳንሳት።
ባሕር ተሻግሮ፣ቅጥሯን አልፎ፣
እልፍ አእላፍ አሰልፎ።
የጦቢያን ገነት ምድር፣
የአበውን ስጋና ደም፣ሕያው አፈር።
ለቀኝ ግዛት፣
እርስት ጉልት፣
ቅርጫ አድርጎ ሊመትራት።
በነጭ ሴራ፣በሞት እብሪት ተሸፋፍኖ፣
አልሰማ ቢል ልቡን ደፍኖ።
ካሰበበት ደግሞ ሊደርስ፣
በእሳት የታጠረ ቅጥሯን ሊያፈርስ።
ለፋሺስት፣
ከንቱ ቅዠት፣
ግሳንግሱ፣
ዓድዋ ነው፣መራራ ጽዋ፣ለጠላት ምሱ።
« ዓድዋ፣(2 ጊዜ )
የሀበሻ ፣አጽመ ርስቱ፣
የወረሰው፣ከአያት ቅድም ሃያቱ፣
ምንጅላቱ፣
ለእም አበው ሕይወት ሞቱ።
« ዓድዋ፣የሰማይ አድማስ ጥቁር አለት፣
የቀለመው በደም ፍሰት።
በነጭ ሴራ ተጠንስሶ፣
በአበው ትግል ደም ተከሶ።
የቆየልን ርስታችን፣
« ጦቢያ ነች፣ ሃገራችን።
ከአማራ አይደል ከጉራጌ፣
ከሲዳማ ወይም ከሐረርጌ።
ከጋምቤላም በለው ከሺናሻ፣
ባለ ብዙ ሕብር ነው።አንዱ አበሻ።
በዓድዋ የከተመ
« (ሃገር/ምኒሊክ)ሲታመም፣ሁሉ የታመመ።
« ዓድዋ፣(2ጊዜ )
የእም አበው አጥንት ስብርባሪ፣
ሕያው ልሳን ተናጋሪ፣
ከዘመን ዘመን ተሻጋሪ፣
የነጻነት ድል አብሳሪ።
የአልደፈር ባይነት አኩሪ ገድል፣
ጠላትን በጦር በጎራዴ ቆራርጦ የሚጥል።
ጥልቅ ነው።የሙት ባህር፣
ፋሺስት ኢጣሊያን አስጥሞ የሚያስቀር።
« ዓድዋ፣
ለጠላቱ ሲኦል መቃብሩ፣
ለእም አበው ሃገር ምድሩ፣
ስጋና ደሙ ነው፣ምስክሩ።
ከትውልድ ትውልድ፣የአበው ውርስ፣
ዘመን የማይሽረው ሕያው መንፈስ።
በደም የቀለመ፣ሕያው የማይጠፋ፣
የአበው ገድል፣ከዘመን ዘመን በልባችን የሚሰፋ።
አዲስ ዜና አዲስ ብስራት፣
የጥቁር ሕዝብ ነፃነት፣
የወጣበት ከባርነት፣
« ዓድዋ፣ ነው።ሕያው እውነት።
« ዓድዋ፣ታሪካችን የጦቢያ ክብር ሞገስ፣
የድላችን አርማ፣በልባችን ጽላት የሚቀረጽ።



ኢዩኤል ገላሼ(ገዛኸኝ)

ሕያው ታሪክ ድርሳናችን፣
ያበው ስራ ነው፣ክብራችን።
ለጦቢያ አጥንት፣ስጋና፣ደም፣ሃገር ምድሩ፣
«ዓድዋ፣ነው ምስክሩ።

የደም ጅረት፣
የደም እንባ፣
ዓድዋ ዓድዋ ዓድዋ።
ክብርና ሞገስ ለቀደሙት አባቶቻችን ይሁን።

# የዓድዋ ሙዚየም -
# ጀግኖቻችንን እና አንጸባራቂ ድላቸውን የሚመጥን

ምሕረት ሞገስ



ጥቁር እና ነጭ እኩል መሆኑን ማረጋገጫ የሰጠ፤ የዓለምን የፖለቲካ አሰላለፍ የቀየረ፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ የኩራት ምንጭ የሆነው የዓድዋ ድል ሊታወስ እንደሚገባ አያከራክርም፡፡ በእርግጥ ለ127 ዓመታት ሲወሳ ኖሯል፡፡ በዚህ ዓመት ደግሞ 128ኛውን የዓድዋ ድል በዓልን እያከበርን እንገኛለን። ነገር ግን ድሉን ያስመዘገቡ ጀግኖች በልካቸው በእርግጥ በአግባቡ አውስተናቸዋል? የሚል ጥያቄ ከተነሳ መልሱ ያጠያይቃል፡፡

የውጪውን ዓለም ያዩ የታሪክ ምሑራንም ሆኑ ሌሎች የተለያዩ ዜጎች የዓድዋ ድል በግዝፈቱ ልክ ማስታወሻ እንዳልተቀመጠለት እና እየታወሰ አለመሆኑን ደጋግመው ሲያነሱ ቆይተዋል፡፡ መነሻቸው በዓለም የሀገራቸውን ጀግኖች ለመዘከር የተለያየ ታሪካዊ ሙዚየሞችን የገነቡ ሀገሮችን በመጎብኘታቸው ነው፡፡ በትልቅነታቸው፣ የታመቀ ታሪክን ቀርፆ በመያዝ፣ በጎብኚዎች ብዛት እና በሌሎችም መመዘኛዎች ታዋቂነትን ያተረፉ ሙዚየሞችን ከገነቡ ሀገራት መካከል አውስትራሊያ፣ ቤልጂየም፣ ካናዳ፣ ፈረንሳይ፣ አየር ላንድ፣ ግሪክ፣ ጃፓን እና አሜሪካን ተጠቃሾች ናቸው።

እነዚህ ሀገራት ጀግኖቻቸውን የሚያወሱ እና ስለጀግኖቻቸው ታሪክ በሰፊው ሊያስረዱ የሚችሉ ሙዚየሞችን ሲገነቡ፤ እነርሱ የፈፀሙት ጀብድ ከኢትዮጵያ ጀግኖች ጋር የሚነፃፀር አይደለም።ሕድላቸውም በዓለም ደረጃ የዘር ልዩነትን ጥቁር እና ነጭ የሚል ክፍፍልን ወይም ነጭ ብቻ አቅም እንዳለው የሚገልፀውን ድሉ ከአገራቸው አልፎ በኢትዮጵያ የዓድዋ ድል ልክ ለሌሎች መሻገር የሚችል ሆኖ አይደለም፡፡ በዓለም ላይ የሰውን ልጅ እኩልነት ማረጋገጥ እስከ ቻሉ ድረስ ሳይሆን ለሀገራቸው ነፃነት ታግለዋል በሚል ብቻ ነው፡፡

ነገር ግን ከሙዚየም በተጨማሪ የተለያዩ የአውሮፓ ሀገሮችም ሆኑ አሜሪካን እና ሌሎችም ሀገሮች ከተሞቻቸውን ያደመቁት በክብር ለሀገራቸው የተሰዉ ጀግኖቻቸውን በሚያውሱ ሐውልቶች ነው፡፡ መናፈሻ በመሥራትም መታሰቢያነቱን ለጀግኖቻቸው ይሰጣሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ግን እዚህ ላይ ሰፊ ክፍተት እናስተውላለን፡፡ በእርግጥ ዓድዋ ሰፈር አይደለም-ዓድዋ መንደር አይደለም፤ ሀገር ነው፤ ከነታሪኩ-አህጉር ነው፣ ሰ......ፊ ዓለም ነው እያልን ግጥም ገጥመናል፡፡ ዓድዋ ዛሬ ናት ዓድዋ ትናንት መቼ ተረሱ እና የወዳደቁት ብለን ከመዝፈን ውጪ ጀግኖቻችንን በቅጡ በትውልድ አዕምሮ ውስጥ ተቀርፀው ሊቀሩ በሚችሉበት መልኩ አውስተናቸዋል ምስላቸውን ቀርፀን አስቀምጠናል ለማለት ያዳግታል፡፡



የጀግኖችን ምስል ለይቶ በማስቀመጥ በኩል በተለይ ከአሁኑ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በፊት እኛ ኢትዮጵያውያን ሰፊ ክፍተት ነበረብን፡፡ ከሰፊው የዓድዋ ድል ታሪክ ውስጥ ጥቂቱን በማሳየት ለዓድዋው ድል ጀግኖች ተገቢው ማስታወሻ ሳናስቀምጥ መቆየታችን ደግሞ ያስቆጫል።ዓመት ጠብቆ በማክበር ቀኑን ለመዘከር ከሚደረግ ጥረት ባለፈ የዓድዋ ድልን ታላቅነት የሚመጥን የታሪክ ማስታወሻ በማኖር በኩል ብዙ አለመሠራቱ ብዙዎችን በእጅጉ ሲያነጋግር ቆይቷል።

ጦርነቱን ከመሩት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒሊክን ከሚያሳይ ቅርፅ በጊዮርጊስ አደባባይ ከማስፈር ውጪ የነበሩት ማስታወሻዎች እጅግ ውስን ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መካከል በዓድዋ ጀግኖች ስም የተሰየሙ ትምህርት ቤቶች እና የዓድዋ ድልድይ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በእርግጥ ከ100 ሺህ በላይ ገበሬዎች ማረሳቸውን፣ መዝራት እና ማጨዳቸውን ትተው ወደ ቀረበላቸው ሀገርን በነፃነት የማቆየት ጥሪ ምላሽ የሰጡትን በሙሉ አካቶ ምስላቸውን በመላው ኢትዮጵያውያን አዕምሮ ውስጥ እንዲከተብ ማስቻል እና ለማስታወሻነት ማስቀመጥ ያዳግታል፡፡ ነገር ግን ራስን ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑትን በተለያየ መልኩ በስዕል በማስቀመጥ፤ ጦርነቱ በተካሔደበት ወቅት ጦር በመምራት በጀግንነታቸው የታወቁ ስለውለታቸው ምስላቸው ተቀርፆ እንዲጎበኝ አለመደረጉ እስከ አሁን ለምን ይህ ሆነ ያስብላል። በሌላ መልኩ ዛሬ ይህንን ማድረግ መቻሉ ብዙዎችን አስደስቷል፡፡

ከሰሞኑ በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ድሉን ላጎናፀፉን ጀግኖች ምስላቸው ተቀርፆ እና በስዕል መልክ ተሰቅሎ ማየታችን ብዙዎቻችንን አስደስቷናል፡፡ ስንል መነሻችን በኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ጥቁር ሕዝቦች መጎብኘት እንዲችል እና ታሪካችን ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ስለሚያግዝ ነው፡፡ ምንም እንኳ አሁንም ከጦር መሪነት ባሻገር በተለያየ መልኩ ለድሉ መገኘት ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ ጀግኖች ሊኖሩ ቢችሉም፤ በዋናነት መታወቅ ያለባቸው ለትውልድ ታሪካቸው ሊነገርላቸው የሚገቡትን በዚህ መልኩ ቀርፆ ማስቀመጡ በብዙዎች ድጋፍ ያስገኘ ጉዳይ ሆኗል፡፡

ከየአቅጣጫው የመጣውን ሕዝብ እየተዋጉ እያዋጉ ከፊት ሆነው የመሩ፤ ለሀገራቸው ራሳቸውን የሰጡ ብቻ ሳይሆኑ እህል ይዘው የተጓዙ፣ ፈጭተው አብኩተው እና ጋግረው ሠራዊቱን ሲመግቡ የነበሩትም ለዓይን በሚማርክ መልኩ በስዕሎች በሙዚየሙ ተጠቃልለው ተገልፀው መታየታቸው የበለጠ የተሟላ አድርጎታል፡፡

የዓድዋ ጀግና የነበሩት ከንጉሥ አፄ ምኒሊክ እና ከጀግናዋ እና ከብልኋ እቴጌ ጣይቱ ብጡል በተጨማሪ ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ጉዲሳ፣ ንጉሥ ተክለኃይማኖት ተሰማ ጎሹ፣ ንጉሥ ሚካኤል አሊ ልበን፣ ደጃዝማች ባልቻ ሳፎ ሮባ፣ ራስ ወሌ ብጡል ኃይለማርያም፣ ፊት አውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ሁንዱል፣ ራስ አሉላ እንግዳ ቁቢ፣ ራስ መንገሻ ዮሐንስ፣ ራስ አባተ ቧያለው፣ ራስ ቢትወደድ መንገሻ አቲከም፣ ፊት አውራሪ ገበያው ገቦን የመሳሰሉ በግምባር ቀደምትነት የሚነሱ 12 የጦር መሪዎች ከለኮሱት የድል ችቦ ጋር በመሐል የኢትዮጵያ እምብርት አዲስ አበባ በፒያሳ አካባቢ ስማቸው እና ምስላቸው ተቀርፆ መቀመጡ የሀገር ባለውለታ አባቶች ገድል ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረግ በኩል የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡

የጀግንነት ስማቸውን ጨምሮ አባ ጎራው፣ አባ ቃኘው፣ አባ ጠና ፤ አባ ሻንቆ፣ አባ መላ ፣ አባ ነጋ፣ አባ ግጠም እያሉ ክብር በተሞላው መልኩ ሙሉ ማስታወሻቸውን በማቆሙ ትውልዱ ታሪኩን የበለጠ ለማወቅ እንዲነሳሳ የሚግዝ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ በዓድዋ ከዘመቱት ኢትዮጵያውያን መካከል 45ሺህ አካባቢዎቹ ፈረሰኞች ሲሆኑ፤ እነርሱንም የሚወክል ቅርፅ በሙዚየሙ መቀመጡ በምን መልኩ ጦርነቱ ሲካሔድ እንደነበር የሚመላከቱ ናቸው፡፡ ይህ እና ሌሎችም የጦርነቱን ዓይነት የሚያመላክቱ ሌሎችም የአሸዋ ገበታን የመሳሰሉ ቅርፆች በሙዚየሙ መገኘታቸው ይህንን ታላቅ ዐሻራ ላስቀመጡ ምስጋና ይገባል እንድንል ያስገድደናል።

# ‹‹ ዓድዋ በዲፕሎማሲው መስክ እኩል የመደራደር ብቃት እንዲኖረን ያደረገ ግዙፍ ድል ነው ››

- አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን
የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ

ማሕሌት አብዱል

የአፍሪካ የነፃነት ምልክት ነው፤ አፍሪካውያንና ጥቁር ሕዝቦች በአንድ ድምፅ ከፍ አድርገው የሚናገሩት ደግሞም የሚኮሩበት ድል ነው፤ ዓድዋ! ። 1888 ዓ.ም ሰውን በቆዳ ቀለም ለይቶ፤ ደካማና ኃያል፤ ገዢና ተገዢ፤ ባሪያና ጌታን ታሳቢ አድርጎ የመጣን ወራሪ ኃይል ያነገበውን የነጭ የበላይነት እሳቤን ከመሠረቱ የቀየረ ድል ነው። የድሉ ባለቤት የሆኑ የአባቶቻችን ልጆች እንደሃገር በዓለም አቀፍ መድረክ ባሉን ዲፕሎማሲ ግንኙነቶች ውስጥ የተሰጠን የአቻነት መንፈስ ባለፈ ለኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ጉዞ ሥምረትና ቅቡልነት የዓድዋ ድል ዋነኛ ማዕከልና ማጠንጠኛ ስለመሆኑ ይነሳል።

ምንግዜም ኢትዮጵያውያንና መላው ጭቁን ሕዝብ የሚኮሩበት ፤ አሁንም ድረስ ኢትዮጵያ በዓለም ደረጃ ለተጎናፀፈችውና ለሚሰጣት ክብር ሁነኛ መሣሪያ ሆኖ እያገለገለ እንደሆነም ይነገራል። የዲፕሎማሲ ኩራታችን ምንጭ ሆኖ ሁላችንም በየደረስንበት ከአንገታችን ቀና ብለን እንድንሄድ ቀንዲል ሆኖ እያበራ ያለ ድል እንደሆነም አጠያያቂ አይደለም።

በዛሬው ልዩ እትማችንም የዓድዋ ድል ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከፍታ የነበረውን አበርክቶ እንዲሁም ድሉን መነሻ በማድረግ በዲፕሎማሲው መስክ መሠራት በሚገባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አምባሳደር እሸቴ ጥላሁን ጋር ውይይት አድርገናል። እንደሚከተለው ይቀርባል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በዓድዋ ጦርነት ጣሊያን ድል ከመንሳቷ በፊት በዓለም ላይ የነበራት ገፅታ ምን ይመስል ነበር ?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** እንደሚታወቀው ከዓድዋ በፊት የነበረው ጊዜ የዘመነ መሳፍንት ማብቂያና ከዓለም ጋር በተወሰነ መልኩ ግንኙነት የጀመርንበት ወቅት ነበር። ከአፄ ቴዎድሮስ በፊት ደግሞ በአካባቢና በጦር መሪዎች ማዕከላዊ መንግሥቱ ተዳክሞ የነበረበት፤ መልክ ያለው የውጭ ግንኙነት ያልነበረበት ጊዜ ነበር። ታላላቆቹ የአውሮፓ መንግሥታት አፍሪካ ላይ ተፅዕኖ ለማሳደር ወይም ደግሞ ባላቸው ቅኝ የመግዛትና የማንበርከክ ፍላጎት የየአካባቢ መሳፍንቶችን እየደገፉ የሚሠሩበት፤ የተበታተነ አይነት ሁኔታ ነበር። ወደኋላ ዘመን ገፋ አድርገን ስንሄድም ከውጭ ዓለም ጋር በተወሰነ መልኩ ራስን የማግለል ሁኔታ ነበር የሚታየው። በእርግጥ በአክሱም ዘመን መንግሥት ኢትዮጵያ በአፍሪካ ብቻ ሳይሆን በአዋሳኝ የዓለም ሀገራት ጭምር ተፅዕኖ የምትፈጥርና ገናና ሥም ያላት ሀገር ነበረች።

ከዓድዋ ወዲህ ያለውን ዲፕሎማሲ ስናነሳ ደግሞ በአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች አፍሪካ ላይ ተዘርግቶ የነበረውን ፅኑ ፍላጎት መረዳት ተገቢ ነው። በቅኝ ግዛት ቦታ ለመያዝ በነበረው የቅርምቱ ፉክክርና ውድድር እርስበርሳቸው እስከመጋጨት የደረሰቡት ጊዜ ነበር። ያንን ፍላጎታቸውን ለማሳካት ከተጠቀሙባቸው ስልቶች አንዱ መሬት ላይ ሆኖ ግዛቱን መቆጣጠር ነው። ሌላው በተፈፀሙ ውሎች ወይም በተፈረሙ ውሎች መሠረት የመቆጣጠር መብት እንዲኖራቸው (ሌጂትመሲ) በአንድ ሀገር ላይ የማድረግ አካሄድ ነበር። ጣሊያኖቹም የተከተሉት ይሄኛውን መንገድ ነው። ከዓድዋ በፊት መሬት ለመውረርና ለመስፋፋት ሲሞክሩ በገጠማቸው ተግዳሮት ምክንያት የውጫሌን ስምምነት መፈረም ነበረባቸው።

እንግዲህ በዚያ ገና ለጋ በነበረበት ወቅት የኢትዮጵያ ዘመናዊ ማዕከላዊ መንግሥት እና የውጭ ጉዳይ የውጭ ግንኙነት አያቶቻችን ስምምነቱን ዓላማ ተረድተው መግባባት ላይ ሳይደርስ ቀርቷል። ይህም ሲባል ኢትዮጵያ በጣሊያን ቁጥጥር ስር አለመሆንዋንና ራሷን የቻለች ነፃ ሀገርና መንግሥት መሆንዋን በገሃድ ማሳወቅ ችላለች። ያንን ደግሞ ጣሊያኖቹ ባለመቀበላቸውና ትልቁ ዓላማቸው ባለመሳካቱ ሁለተኛ አማራጭ መከተል መረጡ። በመሣሪያ ኃይል ኢትዮጵያውያንን አምበርክከው ሰብረው የኢትዮጵያ ግዛትን ለመቆጣጠር የሞከሩት ሙከራ ሳይሳካ ቀረና ዓድዋ ላይ በተከፈለ መስዋዕትነት እኛም የዛሬው ነፃነታችንን ይዘን ቆየን።


> “ዓድዋ ነፃ ያወጣው እኛን ጥቁር ሕዝቦችን ብቻ ሳይሆን መላውን ጭቁን የዓለም ሕዝብን ጭምር ነው

**አዲስ ዘመን፡- ጀግኖቻችን በዓድዋ ላይ ጣሊያንን ድል መንሳታቸው ለዲፕሎማሲው የነበረው አበርክቶ እንዴት ይታያል?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** ኢትዮጵያውያን ጣሊያንን ድል መንሳታቸው በዓለም ላይ መነቃቃት ፈጥሯል። ቀድሞ የነበረው እኩልነትን ወይም ሚዛኑን ያልጠበቀ፤ የራስን ፍላጎት ሌላ ላይ የመጫን የምዕራባውያኑ እሳቤ እንዲመክን በማድረግ ረገድ የላቀ አበርክቶ ነበረው። ምክንያቱም ደግሞ አፍሪካውያን ከአውሮፓ ጋር እኩል አይደሉም የሚለውን አስተሳሰብ ሰብሯል። ዓድዋ ነፃ ያወጣው እኛን ጥቁር ሕዝቦችን ብቻ ሳይሆን መላውን ጭቁን የዓለም ሕዝብን ጭምር ነው።

በቅኝ ገዢዎች ስር የነበሩ ሌሎች ሀገራት እኩል ነፃ ሕዝቦች ነን፤ ነፃ መንግሥት ነን የሚል እሳቤ እንዲኖራቸውና በዲፕሎማሲው ዘርፍ እኩል የመደራደር ብቃት እንዲኖራቸው ያደረገ ግዙፍ ድል ነው። እናም በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ለውጦታል። በዓለም ላይ ኢትዮጵያ ምንአይነት ሀገር እንደሆነች፤ ምን አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል የተዘጋጀ ሕዝብ እንዳላት፤ የነፃነት ፣ የእኩልነት ፣ የሀገርነት መርሆችን ለዓለም ማሳየት የቻለ ድል ነው።

እንዳውም በቁንፅል ደረጃ ብቻ የሚታይ አይደለም።



ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

ይህ ድል በሌሎች ትርክቱን በደንብ በሚሠሩት ተመሳሳይ የተገፉ ሕዝቦች ለምሳሌ በዓረቦች ወይም በእስያውያን የተገኘ ድል ቢሆን እኛ ባልኮሰኮስነው መልክ አይሆንም ነበር። የፈጣሪ ፈቃድ ሆኖ አሁን ላይ ግልፅና ጎልቶ በሚታይ ሁኔታ ስለዓድዋ የምንናገርበት ዘመኑ ደርሷል። የዓድዋ ድል መታሰቢያ ማዕከል መገንባቱ በራሱ ለዚህ አመላካች ነው። በአጠቃላይ ድሉ ለዲፕሎማሲያችን ከፍታ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ነበረው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ መድረኮች ተደማጭነት እንዲኖራት በማድረግ ረገድስ የድሉ ሚና እንዴት ይገለፃል?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** ዓድዋ ሌላው ይቅርና በሥነ-ልቦናችን ውስጥም እንዲገነባ ያበረከተው አስተዋፅዖ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ኢትዮጵያውያን ከማንኛው ሃገር ጋር እኩል ነን የሚለውን ሥነ-ልቦና የገነባነው በዓድዋ ምክንያት ነው። ያም በመሆኑ ነው እኮ ልክ ከዓድዋ ጦርነት በኋላ ተከትሎ የመጣው የአውሮፓ መንግሥታት ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥታት ጋር ቁጭ ብለው እየተደራደሩ እኮ ነው እንደአቻ መንግሥታት አብረን እንሥራ፤ በንግድና በመሳሰሉ የኢኮኖሚ ጥቅሞች እንተባበር የሚለው ነገር ቅቡልነት እያገኘ የመጣው። የዲፕሎማቲክ ልዑኩንና ተልዕኮ ይዞ የመጣው ዓድዋ ነው።

ዓድዋ እኩልነትን ፈጥሯል ከሚባለውም በላይ የሚታይ ነው። ምክንያቱም ደግሞ ኢትዮጵያውያን እኩልነታቸውን አረጋግጠው ብቻ አይደለም የቀረው፤ ሌሎች እንዲማሩበትም ነው ያደረገው። በወቅቱ ቅኝ ግዛት ገና እየተንሰራፋ ነበረ። የነፃነት ትግልና እና ፓንአፍሪካኒዝምን ማቀንቀን ተጀመረ። ስለዚህ እኛ የእኩልነት መንፈስን፤ ኢትዮጵያ በወቅቱ እንደበለፀጉ ሀገራት ነፃነትና መብቷን የምታስጠብቅ፤ ተደራድራ የምታገኝ መሆንዋን ከማሳወቅ አልፎ ለሌሎች ትምህርት ሆኗል።

ከጥቂት ዓመታት በኋላ ሊግ ኦፍ ኔሽን ምሥረታ የራሷን በጎ አሻራ እንድታሳርፍና አባል ሆና ከሌሎቹ ታላላቅ ሃገራት እኩል ቁጭ ብላ ስለሠላም ለመደራደር አስችሏታል። ግልፅ በሆነ መንገድ የእኩልነት ሥነ-ልቦናችን ከፍ እንዲል ያደረገ ነው።

አሁን ላይ ማንኛውም የሰው ዘር በቀለሙ፤ ወይም በኢኮኖሚ ደረጃው የማይለያይ መሆኑን መረዳት የሚቸግራቸው አልያም መቀበል ያልቻሉ፤ ቅኝ መገዛታቸው በፈጠረባቸው ተፅዕኖ ምክንያት የበታችንነት መንፈስ የሚሰማቸው አሉ። ወደ እኛ ሲመጣ ግን ይህ ስሜት የለም። አሁን ላይ ቀርቶ በወቅቱ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የነበራቸው የእኩልነት ሥነልቦና አስገራሚ ነበር።

እኔ ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በ1985 ዓ.ም ላይ የናሚቢያ ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያውያን ከነበራቸው በራስ የመተማመንና የእኩልነት ጠንካራ ሥነልቦና ይደነቁ ስለነበር ከኢትዮጵያ የተለያዩ ባለሙያዎችን በመውሰድ ከቅኝ ግዛት ስሜት መውጣት ያልቻለውን ሕዝባቸውን ይህንን የእኩልነት መንፈስ እንዲረዱ ለማስቻል የሄዱበት መንገድ እንደነበር አስታውሳለሁ።

በወቅቱ ሕዝባቸው ከቀድሞ ቅኝ ገዢዎቹ ጋር እኩል የመሆን ስሜትን በራሱ መማር ተቸግሮ እንደነበር ነው የነገሩኝ። ይህ ምንያህል የሥነልቦና ጫና አሳድረውባቸው የሚያስረዳ ነው። ይህ የበታችነት መንፈስ አሁንም በአንዳንድ ሀገራት ሕዝቡ አዕምሮ ተሰንቅሮ ይስተዋላል፤ ወደ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ ሲመጣ ግን ነገሩ የተገላቢጦሽ ነው፤ በየጊዜው በሚገጥሙን ነገሮች ተፅዕኖ ሲደረግብን፤ ሁኔታው ከመንገድ የወጣ ብሔራዊ ክብርን የሚነካ ሲሆን ቅድመ ሁኔታዎችን አንቀበልም።

በተለይም ነፃነትንና እኩልነትን የሚጋፋ ከሆነ ሁሉም የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች ቀድሞ ከነበሩት ዲፕሎማቶች ጀምሮ ዛሬ የሚገቡ አታሼዎች ድረስ የሀገርን ክብር የሚነካ ነገር ላይ እንደነብር የሚያስቆጣ ስሜት ነው በውስጣችን ያለው። ይሄ ዓድዋ የሰጠን በረከት ነው ብዬ አምናለሁ። ከዚያ በፊት ደግሞ ለውጭ ተፅዕኖ የተጋለጥንበት

ወደ ገጽ 26 ዞሯል

# ‹‹ ዓድዋ በዲፕሎማሲው መስክ ...

ከ25 ኛው ገጽ የዞረ



**ኢትዮጵያውያን ዓድዋ ላይ ይህንን ድል በሚያገኙበት ጊዜ በጣም ከፍተኛ ጉልበት ነው የሰጡት። ለፓን አፍሪካኒዝምና ለጥቁሮች የነፃነት ንቅናቄ ስሜት ዝም ብሎ ከመብላላት ወደ አደባባይ እንዲወጣና የነፃነት ማረጋገጫ መሠረት ሆኖ ጎልቶ እንዲወጣ፤ መደፋፈር እንዲፈጠር አድርጓል፤ የይቻላል ስሜት ፈጥሯል**

ሁኔታ ስለሌለ ይህንን የተገዢነት ስሜት አናውቀውም። ደግሞም መሠረት ባይኖረው ኖሮ ዓድዋም ሊመጣ አይችልም ባይ ነኝ።

ዓድዋ ዋናው ነገር ኢትዮጵያ መንግሥት ያላት ሉዓላዊ ሀገር መሆንዋን እንዲቀበሉ ማድረጉ ነው። በወቅቱ ሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት ቅኝ ገዢዎቹ ከፋፍለው በያዙት ሀገሮች ስያሜ ያላቸው ነበሩ። የሉዓላዊነት መገለጫ ሀገሩም መንግሥቱም ነው። ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በቴክኖሎጂ የተስፋ ጫማ ባናደርግም፤ በባዶ እግራችንም ብንሆን፤ ነፃነታችንን ለማስከበር ወደኋላ አንልም።

በሊግ ሆፍ ኔሽን ተደራድረን እንደማናቸውም ነፃ ሀገራት ድምፃችንን አሰምተን ነው አባል የሆነው። ያንን በራስ የመተማመን ብቃት የጎለበትነው አባቶቻችን ዓድዋ ላይ ባጎናፀፉን ድል ነው። ያንን እኩልነት ስሜት ብቻ ሳይሆን በሚጨበጥ፤ በሚዳሰስና መለካት በሚቻል መልኩ የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ አካል መሆን ችላለች። በአጠቃላይ ዓድዋ እንደሕዝብ ወይም እንደሰብዓዊ ሙብት ብቻ ሳይሆን እንደሀገር ያንን እንድናገኝ አድርጓል።

**አዲስ ዘመን፡- ለፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ መጎልበትስ የዓድዋ ሚና ምን ነበር?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** የቅኝ አገዛዝ ተፅዕኖ እየበረታ ሲመጣ የዓድዋ ድል ደግሞ ጭቁኖች ያንን የቅኝ ግዛት ቀንበር ከላያቸው ላይ የማራገፍ ፍላጎቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል። በአውሮፓም፤ በሰሜን አሜሪካም ንቅናቄዎች ነበሩ። የባሪያ ንግድ ከተወገደ በኋላ የሉዓላዊነት ጥያቄና የቀለም እኩልነት ጥያቄዎችና ቅኝ ግዛትን አሻፈረኝ የማለት ስያሜዎች የተጠነሰሱበት ዘመን ነበር። ኢትዮጵያውያን ዓድዋ ላይ ይህንን ድል በሚያገኙበት ጊዜ በጣም ከፍተኛ ጉልበት ነው የሰጡት። ለፓን አፍሪካኒዝምና ለጥቁሮች የነፃነት ንቅናቄ ስሜት ዝም ብሎ ከመብላላት ወደ አደባባይ እንዲወጣና የነፃነት ማረጋገጫ መሠረት ሆኖ ጎልቶ እንዲወጣ፤ መደፋፈር እንዲፈጠር አድርጓል፤ የይቻላል ስሜት ፈጥሯል።

ራስን ነፃ ማውጣትና ጥቁር ሕዝቦች እንደማንኛውም ሌላ ሕዝብ እኩል ናቸው የሚለውን ስሜት በጣም አጠናክሮታል፤ የማይቆራረጥ እንዲሆን አድርጎታል። ተቋማዊ እንዲሆን አድርጎታል። የተለያዩ የነፃነት ንቅናቄዎች በተደራጀ መልኩ እንዲጀመሩ አድርጓል። በዚያው መንፈስ እየቀጠለ ሄዶ የአፍሪካ ሀገሮች ከቅኝ ግዛት ነፃ የሚወጡባቸውን ተቋማት ፤ አቋሞች፤ አደረጃጀቶች እየፈጠሩ ወደ ነፃነት እንዲጓዙ መበረታታት ፈጥሯል።

ግን ደግሞ ያንን ብቻ አድርጎ አይደለም የቀረው፤ ኢትዮጵያን እንደምሳሌ እያዩ የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ከመቼው ጊዜ በላይ እንዲጎለብት አድርጓል። ሰውን ለነፃነት የሚቀሰቅስ፤ የሚያነቃቃ መንፈስ ፈጥሯል። ያ መንፈስ ደግሞ መሠረት እንዲኖረው ያደረግነው እኛ ነን። በእ.ኤ.አ 1963 ነፃ የወጡትን የአፍሪካ ሀገራት የተለያየ የመከፋፋል ዝንባሌ ነበር ፤ያንን አልፈው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲመሠረት የፓንአፍሪካኒዝም አስተሳሰብና መንፈስ ማዕከል እንዲኖረው አድርጓል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አፍሪካ አሁንም ቢሆን በእጅ አዙር የሚደረጉ የቅኝ አገዛዝ ዝንባሌዎችና ጫናዎች እንዳሉባት እሙን ነው፤ ይህንን ጫና በመከላከል ረገድ ምን ሲሠራ ይገባል ይላሉ?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** እንግዲህ የፖለቲካ ቅኝ አገዛዝ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እየከሰመ መጥቷል። ትልቁ መከራና ፈተና ሆኖ የቀጠለው የባሕልና የኢኮኖሚ ቅኝ አገዛዙ ነው። ታዳጊ ሀገራት በተለይ የአፍሪካ አህጉር ያለምዕራባውያኑና ቀድመው ከበለፀጉት ሀገሮች ድጋፍና ትብብር ውጪ የማደግ ተስፋ የለውም ፤ ጨለማውና ተስፋቢሱ አህጉር እያሉ የቀጠሉት ተፅዕኖ ነው ትልቁ ፈተና። በማዕድናት፤ በንግድ የሚያደርጉት ብዝበዛ አለ።

የየሀገራቱ ሕዝቦች ተጠቃሚ ሳይሆኑ ለራሳቸው እየወሰዱ የሚበለፅጉበት ሁኔታ ነው ያለው። ሌላው እንደካንሰር የሚታየውና አንዴ ከተተከለ ለማውጣት አስቸጋሪ የሚሆነው የውጭ እርዳታ የሚባለው ነገር ነው። በውስጡ የሰብዓዊ ድጋፍ፤ የልማት ድጋፍ አለው፤ የወታደራዊ ድጋፍና የመሳሰሉትን ልንጠቅስ እንችላለን። እነዚህ በሙሉ የእጅአዙር ቅኝ አስተሳሰብ ወይም የጥገኝነት አስተሳሰብና ሥነልቦና እንዲጠናውት አድርገዋል። ነፃ የወጡ ሀገራት ውስጥ ያሉት ተቋማት ራሳቸው ጠንክረው እንዳይቆሙ የሚያደርግ ነው። ይህም ለኒዮ ኮሎናሊዝም በር ይከፍታል ማለት ነው።

ስለዚህ ይህንን ለመቋቋም ልንሠራቸው የሚገባቸው ሥራዎች አሉ። በዓድዋ ጦርነት ላይ ሕዝቡ እንዲሳተፍ ጥሪ ሲቀርብለት ወታደራዊ ሥልጠና አልወሰደም፤ ጠመንጃ ሁሉም የለውም፤ ስንቅ የለውም፤ ቤተሰብ አለው፤ ሀገርን፣ ምድርን ፣ ምሽትህን ሊነጥቅህ ጠላት መጥቷል፤ ተነስ ሲባል ምንም ሳያቅማማ ነው የተመመው። አሁን ደግሞ እንዲህ አይነት የረቀቀ ተፅዕኖ መውጣት የምንችለው በሥራ ነው። መሥራት፤ መመራመር ፤ ማወቅና በተለይ ከውጭ እርዳታ ጥገኝነት ለመላቀቅ ክብርን የሚነካና የሚያዋርድ፤ የበታች የሚያደርግ ነገር መሆኑን በደንብ መረዳት ያስፈልጋል።

እርግጥ እርዳታ ሕይወት ያቆያል፤ ትክክል ነው፤ ሆኖም የተወሰነ ጊዜ ተቸግረን ከዚያ ውስጥ መውጣትና ራስን መቻል ያስፈልጋል። ለአሁኑ ትውልድ ይሄ እንደከባድ መስዋዕትነት ሊቆጠር ይችላል ግን ወላጆች ተቋማት እና መገናኛ ብዙኃን ይህንን ለመለወጥ ሰፊ ሥራ ሊሠሩ ይገባል። የሰውን ልጅ ነፃነት ሊረጋገጥ የሚችለው በመሥራት እንዲሁም በኢኮኖሚ ተወዳዳሪ መሆን ሲቻል ነው። በዚህ መልክ ክብርና ነፃነት ማስጠበቅ ያስፈልጋል።

የዓድዋ አባቶቻችን ገድል እና በጦርነቱ ያገኙት ውጤትም ከሕሊና ወቀሳ ድነን እነሱን እንድንዘክር የሚረዳን ከጥገኝነት ስንላቀቅ ነው። እናም የኒዮ ኮሎናሊዝም ሆነ ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) ብዙ መንገዶችን የማስከፈትና አስቀድሞ ያደገውን የዓለም ክፍል የበለጠ ለማበልፀግ የሚደረገውን ሩጫ መቋቋም የሚቻለው በመንቃት፤ በመሥራት፤ በመማርና በመመራመር ነው የሚለው መልዕክት ተገቢ ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ዓድዋ ጥሎት ካለፈው አበርክቶ አኳያ በዓለም ላይ ድሉን ማስተዋወቅ አለመቻሉ ይነሳል፤ እርሶ በዚህ ላይ ያሉት ምልከታ ምንድን ነው? ምንስ ሲሠራ ይገባል ብለው ያምናሉ?**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** ልክ ነው፤ በዓድዋ ከተከፈለልን ዋጋ አኳያ የሚገባውን ያህል አሳውቀነዋል ብዬ አላምንም። እንደሚታወሰውም፤ ቀደም ባሉት ዓመታት እንዲሁ በተለሳለሰ መንገድ እያከበርነው እንሄድ ነበር። ከ1990ዎቹ መጀመሪያ ወዲህ ደግሞ ጨርሶ የመፋዘዝ እና የመደብዘዝ ነገር ነበር። በየመሐሉ ደግሞ በጣም አውርደነው ድሉ የእኛ እስከማይመስል ድረስ የተገኘንበት ሁኔታም የማይካድ ነው።

ይህንን የሚያክል የዓለም ሕዝቦችን እኩልነትና ነፃነት ያረጋገጠ መስዋዕትነትና ድል አራክሰነው፤ የአካባቢ ጉዳይ አድርገነው በጣም በሚያሳንስ ሁኔታ ውስጥ ገብተን ነበር። በነገራችን ላይ እኛ የድሉ ባለቤት የሆንን ሕዝቦች ይህንን ሁሉ ስናደርግ ሌሎቹ ጋር ግን ይከበር ነበር።

ደቡብ አፍሪካ ያከብሩታል፤ ጎረቤታችን ኬኒያም ይዘክሩታል፤ በጽሑፎቻቸው ያወጡታል፤ አረሱትም ነበር። ካሪቢያንና ጥቁር አሜሪካውያን በደንብ በደመቀ ሁኔታ ነው የሚያከብሩት። በተቃራኒው ደግሞ እኛ የድሉ ባለቤት የሆንን ሕዝቦች በራሳችን ላይ ይሄ አይነት ጥፋት ነው አድርሰን የነበረው።

በእርግጥ ይህም አይነቱ የተሳሳተ ምልከታ የሚመጣው የተወሰነ ፍላጎት ባላቸው ኃይሎች እንደነበር ይታወቃል። ይህ ቡድን ታዲያ በሕዝቡ ዘንድ በድሉ ዙሪያ የጋራ መግባባት እንዳይኖር፤ የአመለካከት ችግር እንዲፈጠር በማድረግ ትልቁን ድላችንን አሳንሰን እንድናይ በመደረጉ ነው። ያ የብዙዎች ቅሬታ የነበረው ጉዳይ አሁን ላይ ምላሽ እያገኘ ነው፤ የዓድዋ ድል የአርበኞቹ የአያቶቻችን ገድል ቋሚ ማስታወሻ ቆሞለታል፤ ማዕከል፤ ጥናት ምርምር ለማድረግ የተሻለ እድል አለ። ይሄ ማለት ዲፕሎማቶቻችን ውጪ ወስደው የሚሠሩበት፤ በእውቀት ላይ የተመሠረተ ግብዓት ይወጣል ማለት ነው።

አንዱ ቱሪስት የመሳቢያ መሣሪያም ነው። ሌሎቹ ሃገራት እኮ አደባባይ የተደረጉ ሰልፎች እንደቱሪስት መሳቢያ አድርገው ያስተዋውቋቸዋል። ለምሳሌ ሙባረክን የጣለው የታሃሪር ስኩዌር ሰልፍ የተካሄደበትን አደባባይ ግብፆች አሁን ላይ እንደአንድ የቱሪዝም መዳረሻ ተጠቅመው ገቢ እያገኙበት ነው። ይህ ትንሽ ለዓለም ጆሮ የሚቀርብ ነገር ሲገኝ ኢንቨስት ተደርጎበት የሚሠራ መሆኑን ያሳያል። ይህንን ያህን የተደበቀ ድል አውጥተን መሥራት ነው ያለብን።

በዚህ ረገድ ዘንድሮ ከሌላ ጊዜ በተለየ በሚሲዮኖቻችን ደመቅ ባለ ሁኔታ ይከበራል። ከዚህ በኋላ ባላ ጊዜ ግን በአግባቡ እየታቀደ ማዕከሉንም ሰዎች እየመጡ እየጎበኙት፤ ቦታው ድረስ እየሄዱ በማየት፤ እዛ የሚካሄደው ዩኒቨርስቲና ምርምር እያደገ ዓድዋ የነፃነት መሠረት የተጣለበት ቦታ መሆንዋን ዓድዋና የጦርነቱ አካባቢዎች የምናሳውቅበት ሊሆን ይገባል። በነገራችን ላይ ይህንን ማድረጋችን የኢኮኖሚ ጥቅምም ያመጣል። የክብር፤ የታሪክ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ቱሪዝምን በማስፋፋት የኢኮኖሚ ጥቅምም ጭምር የሚያመጣ ስለሆነ ብዙ ሥራ ይጠበቃል።

በሌላ በኩል ግን ዲፕሎማቶች ለሚሠሩት ሥራ ዋና መሠረት የሚሆነው ሀገር ውስጥ የሚሠራው ሥራ ነው። አስቀድሜ እንደገለፅኩልሽ በጥናት በምርምርም በሌሎችም ጉዳዮች የምንሠራው ሥራ ለአባቶቻችን ድል ያለንን ክብርና የሃገራችን አንድነትና ነፃነት አስጠብቀን በመቆየት ነው ዲፕሎማሲያችንንም ማሳደግ የምንችለው። ደግሞም ይህ ሥራ የዲፕሎማቶች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ለሀገሩ አምሳደር ሆኖ የየበኩሉን አስተዋፅዖ ሲያበረክት ነው። ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ አባቶቻችን ስለሠሩት ድል ማንሳትና ሃገራችንን ማስተዋወቅ የሁላችን የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አምባሳደር እሸቴ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# ‹‹ አሁን መጠየቅ ያለበት ድህነትን ለማሸነፍ ምን እንሥራ የሚለውን ነው››

- ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት

**ስምስም መንግሥቱ**

ላለፉት ስምንት ዓመታት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት ሆነው ያገለገሉት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፤ ስማቸውም ታሪክ አለው። በውጭው አጠራር ሚድል ወይንም በመካከል ላይ ያለው ጆቴ የሚለው ነው ታሪክ ያለው።

እርሳቸው እንደነገሩን፤ አባታቸው ጀግና ይወዱ ስለነበር ለልጃቸው የጀግና ስም አወጡላቸው። በአጋጣሚ ጀግናው ሰው ቤተሰብም ናቸው። እኚህ ጀግና ሰው ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ ወይም ሙቲ ጆቴ ነው የሚባሉት። ሙቲ ቃሉ ኦሮምኛ ሲሆን፣ ትርጉሙም ንጉሥስ ማለት ነው። እኚህ ንጉሥ ከነኩምሳ ሞረዳ ጋር በመሆን ወለጋን ያስተዳድሩ ነበር። በወቅቱ ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የሀገር አንድነትን ለማጽናት ደፋ ቀና በሚሉበት ወቅት አሻፈረኝ ካሉት መካከል ይጠቀሳሉ።

የኋላ ኋላ ግን ሀገራቸውን ከተለያየ ነገር የጠበቁ ባለውለታ መሆን ችለዋል። ለአብነትም በሱዳን ድንበር በኩል ኢትዮጵያ አጋጥሟት የነበረውን ችግር ገትረው የያዙ ጀግና ናቸው። እርሳቸው ይህን ባያደርጉ ግማሹ የወለጋ ሕዝብ ወደሱዳን የሚገባበት አጋጣሚ ይፈጠር ነበር። በሌላኛው ደግሞ ጣሊያኖች የዓባይን ምንጭ መነሻ ለማወቅ በመጡ ጊዜ ‹‹ንጉሤ ዓድዋ ላይ እየተዋጋ እናንተ የዓባይን ምንጭ መነሻ ለማወቅ መጣችሁ›› ይሏቸውና ርምጃ ይወስዱባቸዋል።

በነዚህና በሌሎች ታሪኮች የሚታወቁት ደጃዝማች ጆቴ ቱሉ፤ የልጅ ዳንኤል ጆቴ እናታቸው እናት የደጃዝማች ጆቴ ቱሉ ልጅ ልጅ ናቸው። ወላጅ አባታቸው ደግሞ ጀግና ስለሚወዱ ጆቴ ተብለው እንዲጠሩ ያደርጋሉ። ከጊዜ በኋላ ግን በተለያየ ምክንያት ዳንኤል የሚለውን ስም ለራሳቸው በማውጣት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን በሚለው ስማቸው ፀንቶ መጠሪያቸው ሊሆን ችሏል።

ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን በ1936 ዓመተ ምህረት ነው የተወለዱት። የተወለዱበት አካባቢ ደግሞ ኢሉባቦር ነው። አባታቸው የአካባቢው ገዥ ነበሩ። በወቅቱ ጣሊያኖች ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ለቀው ባለመውጣታቸው ሀገር አልተረጋጋችም። ሆኖም ግን አባታቸው ለሥራ ከሀገር ሀገር ይዘዋወሩ ነበር። በኋላም የከፋ ጠቅላይ ግዛት ተብሎ የሚጠራው ሀገረ ገዥ ሆነው በሹመት ተዛወሩ።

በከፋ ጠቅላይ ግዛት የቆዩት ስምንት ዓመት በመሆኑ፤ ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውንም ሚያዚያ ሃያሰባት በሚባል ትምህርትቤት ገብተው ለመከታተል ችለዋል። በወቅቱ ኢትዮጵያን ለ17 ዓመታት በደርግ ሥርዓት ያስተዳደሩት ኮሎኔል ምንግሥቱ ኃይለማርያምን ጨምሮ በርካታ የወታደር ልጆችም በትምህርት ቤቱ ተምረዋል። ኮሎኔል መንግሥቱ በሁለትና እና በሶስት ዓመት እድሜ ቢበልጧቸው ነው። ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን አባታቸው የዘመድና በኑሮ አቅም ያነሳቸውንም ልጆች በቤታቸው ሰብስበው ያሳድጉ ስለነበር በብዙ ቤተሰብ ውስጥ ነው ያደጉት።

አባታቸው አሁንም አዲስ አበባ ከተማ የሀገር ግዛት ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍንም፣ ለጊዜው በወቅቱ የባላባት ልጆች ብቻ የሚማሩበት መድኃኒያለም ትምህርት ለሶስት ወር እንዲቆዩ ተደረጉ። ከአጭር ጊዜ ቆይታ በኋላ ደግሞ ተፈሪ መኮንን ትምህርትቤት ገብተው ለአንድ ዓመት ከተማሩ በኋላ ዊንጌት ትምህርት ቤት ገቡ። በትምህርታቸው 10ኛ ክፍል ከደረሱ በኋላ የጤና እክል ገጥሟቸው ለህክምና ወደ እንግሊዝ ሀገር ሄዱ። በዚያም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ እድሉን አገኙ።

በዩኒቨርሲቲ የመማር እድል ያገኙት ደግሞ በአሜሪካን ሳንፍራሲስኮ ነው። ትምህርታቸውን እንደጨረሱ ሀገራቸውን ለማገልገል ተመለሱ። ሀገር ቤት ከገቡ በኋላ ነገሮች እንዳሰቡት ሆነው አላገኙም። ሥራ ለመቀጠርም በወቅቱ ከነበረው የፖለቲካ ሁኔታ ጋር ፈተናዎች ገጥመዋቸዋል። በጊዜ ሂደት ግን በልማት ባንክ በፈተና አልፈው ተቀጥረው ለማገልገል ችለዋል። ከዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ በኋላ ነው አሁን በሚመሩት የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ፕሬዚደንት ሆነው እያገለገሉ የሚገኙት።

ከልጅ ዳንኤል ጆቴ ጋር 128ኛውን የዓድዋ ድል በዓልን ምክንያት በማድረግ በዓድዋ ዙሪያ፣ ስለሚመሩት ተቋም፣ የዓድዋ ተምሳሌት ስለሆነው ዓድዋ ዜሮ ዜሮ ፕሮጀክት አንስተን ተጨዋውተናል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ እንኳን ለ128ኛ የድል በዓል አደረስዎ፤ ከዓድዋ ጀግኖች ዋና ዋናዎቹን በማንሳት ቀኑን እናስታውስ።**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** እንኳን አብሮ አደረሰን፤ ስለዓድዋና የዓድዋ ጀግኖች ስናወሳ ታሪኩ በአጭሩ የሚገለጽ አይደለም። ታሪኩ ግዙፍ ነው። ጣሊያን ኢትዮጵያን በኃል ስትወር ኢትዮጵያ በሥልጣኔ ከሚጠሩ ሀገሮች መካከል አልነበረችም። በወቅቱ የነበሩት መኖሪያ ቤቶች እንኳን ከጭቃ የተሠሩ ናቸው። ግን በኃይል ደሀ ሀገር ሊወር የመጣን ፋሽሽት ጣሊያንን በተባበረ የሕዝብ ክንድ ወደመጣበት ለመመለስ ችላለች።

በወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበሩት አፄ ዳግማዊ ምኒልክ ይህችን ደሀ ሀገር ወራሪ ያጋጥማታል፣ ጦርነት ውስጥም እገባለሁ ብለው አላሰቡም። ስለዓለማዊ ሁኔታ መረጃ ይከታተሉ ስለነበር ጀርመን በርሊን ላይ በኢትዮጵያ ላይ የተዶለተውን ለማወቅ ቻሉ። በርሊን ላይ በተካሄደው ኮንፈረንስ ላይ የተካፈሉ ነጮች አስተሳሰባቸው ግልጽ ነው። አፍሪካን እንደቅርጫ ለመከፋፈል ነበር ምኞታቸውና ፍላጎታቸው።


ጀርመኖች፣ እንግሊዞች፣ ቤልጂጎች፣ ስፓኒሾች፣ ደቾች ቦርቹጊዞች ተከፋፍለው ስር ሰደው እየተነቃነቁ ነበር። በዚህ መካከል ጣሊያን ኤርትራንና የተወሰነውን የሶማሌ ክፍል ይዛለች። ለጣሊያን የለቀቀላት ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ስለሆነች ዋናዋን ኢትዮጵያ እንድትይዝ ነው የተለቀቀላት።

ጣሊያን ደግሞ በዚያን ጊዜ ዘ ግሬት ሮማንያ ኢምፓየር ትባል ነበር፣ እኛ ልክ የአፄ ቴውድሮስንና አፄ ዳግማዊ ምኒልክን ታሪክ እንደምናነሳው ሁሉ ነበር ታሪኩን የሚያወሱት። ጣሊያን ኢትዮጵያን በጦር አሸንፉ በቅኝ ለመያዝ አቅዳ ስትመጣ የኢትዮጵያን የውስጥ ችግር መሠረት በማድረግ ነበር። በወቅቱ ኢትዮጵያ በውስጧ የተለያዩ ችግሮች ነበሩባት።

ከነበረው ችግርም የከፋው ሕዝቦችዋ በረሀብ መጎዳታቸው ነበር። ወረርሽኝ ገብቶ ከብቶችም በጣም አልቀውባታል። በበሽታ የጎዱ ከህንድ ሀገር የመጡ ከብቶች ፤ የኢትዮጵያ ከብቶች እንዲያልቁ ምክንያት የሆነዋል ። ክስተቱ ሆን ተብሎ ሊሆን እንደሚችል ይጠረጠራል። ምክንያቱም ከብቶች ተጎዱ ማለት በበሬ የሚያርሰው የኢትዮጵያ ገበሬ ማምረት ያቆማል። የሚበላ ከሌለ ሰው በረሀብ ይሞታል። ይዳከማል። የተራበ ሕዝብም ለመዋጋት አይነሳም።

በጊዜው የነበሩ መሳፍንቶችም በመካከላቸው ነፋስ ገብቶ ስለነበር ስምምነት አልነበራቸውም። የነርሱ አለመስማማት ገበሬውን አሰልችቶታል። ስለዚህ ሌላ ጦርነት ቢመጣ ለመዋጋት የነበረው ፍላጎት እጅግ አናሳ ነበር። ይህ ሁሉ ችግር እጇን ለጠላት ያለምንም ጥርጥር ለመስጠት የሚያስችላት ጊዜ ነው ። በኃይል ኢትዮጵያን ሊወር የመጣው ፋሽስት ጣሊያን ደግሞ ይህንን የኢትዮጵያን የውስጥ ችግሮች ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበር ያለምንም ድካም ሰተት ብሎ ኢትዮጵያ መግባት እንደሚችልና በቅኝም እንደሚይዝ እርግጠኛ ነበር ።

ብልሁ የኢትዮጵያ ንጉስ አፄ ዳግማዊ ምኒልክ ግን ጦርነቱን ከሕዝባቸው ጋር ለመወጣት በወቅቱ ምኒልክ ዓደባባይ ላይ ሆነው በአዋጃቸው የጥሪ ክተት እንዲህ ነበር ያሉት። “እኔ ምንም ያጠፋሁት ነገር የለም፣ ያደረኩትም ነገር የለም። ሀገራችንን፣ ኃይማኖታችንን በአጠቃላይ ሁሉ ነገራችንን ሊያጠፋ የውጭ ወራሪ ኃይል መጥቶብናል። አቅም ያለህ በጉልበትህ፣ አቅም የሌለህ በንብረትህና በፀሎትህ ብለው ነበር ለክተት ዘመቻ ሕዝባቸውን የቀሰቀሱት። መሃላውም አልቀረም። የክተት ጥሪውን ተቀብሎ ለማይመጣው ደግሞ ትቀርና ማርያምን ምሬ አልምርህም” ነበር ያሉት። ጉዳዩ የሀገር ስለሆነ ነው ይህን ማለታቸው።



ኢትዮጵያን በኃይል ሊወርር የመጣን ፋሽስት ጣሊያንን ወደ መጣበት ለመመለስ የቀረ ኢትዮጵያዊ አልነበረም ማለት ይቻላል። በወቅቱ ለዳግማዊ አፄ ምኒልክ ታዛዥ ከነበሩት ራስ መኮንን፣ ልጅ ወይንም ራስ አባተ ቧ ያለው፣ አባመላው፣ ንጉሥ ሚካኤል፣ ደጃች ባልቻ፣ አሉላ አባነጋ፣ ራስ ሚካኤል ይጠቀሳሉ። ከታዛዥነታቸውም በላይ ሀገራቸውን አስበልጠው የሚወዱ ነበሩ። ለምቾታቸው ሳይሆን ለሀገራቸው ቅድሚያ የሰጡ ናቸው።

ራስ መኮንን ከሀረር ነው ጦር አሰባስበው ወደ ግንባር የሄዱት። ንጉሥ ሚካኤልም እንዲሁ ከወሎ ወደ 40ሺ የሚሆን ጦር ይዘው ነበር የዘመቱት። የአፄ ዮሀንስ ልጅ ራስ መንገሻ ዮሀንስ፣ እነራስ አሉላ አባነጋም ጦርነቱን በማካሄድ ስማቸው ከሚነሱት መካከል ናቸው።

በዓድዋው ጦርነት የሴቶች ሚና ከወንዶች ያልተናነሰ ነው የነበረው። ያደርጉ የነበረው ድጋፍ በዚህ በአጭር ጊዜ ቆይታ ተነግሮ የሚያልቅ አይደለም። በታሪክ በሰፊው ቢሰነድ ብዙ ሊባልላቸው የሚችሉ ሴቶች አሉ። ከሴቶች ደግሞ ስማቸው ከፍ ብሎ የሚነሳው እቴጌጣይቱ ድርሻቸው እጅግ ከፍተኛ ነው የነበረው።

ጠላትን ለመዋጋት የዘመተውን ጦር ምሳና እራት በማብላት፣ የቆሰለውን በማከም፣ የደከመውን ደግሞ ለአዝማሪ ግጥም እየሰጡ በማበረታታት፣ ወንዱም፣ ሴቱም በጋራ ለሀገራቸው አንድ ሆነው በመነሳታቸውና ትግሉንም በጋራ በመቋቋማቸው ነው ጦርነቱን በአንድ ቀን ድል ማድረግ የተቻለው።

**አዲስ ዘመን፡- ወራሪው ፋሽት ጣሊያን ያሰበው ሳይሳካ ነገሮች የተገላቢጦሽ ሆኖ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች በአንድ ቀን ድል ተቀናጅተዋል ። ከድሉ በሃላ ያለው እውነታ ምን ይመስል ነበር?**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** ከድሉ በኋላ በሀገር ውስጥ ብዙ ክንውኖች ነበሩ። ኢትዮጵያ በውስጥ ጉዳዩዋ ተጠምዳለች። ወራሪው ፋሽት ግን የገጠመውን ሽንፈት አምኖ ባለመቀበሉና ቂምም በመያዙ ዳግመኛ ኢትዮጵያን ለመውረር 40 ዓመት ሙሉ ሲዘጋጅ ነው የነበረው። ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጣም የጣሊያንን ታላቅነት አመጣለሁ ብሎ ነው። በአውሮፕላን የታገዘ ዘመናዊ የሆነ የጦር መሣሪያ ታጥቆ፣ ብዛት ያለው ሠራዊት ነበር ያሰለፈው። የጦር መሪው ደግሞ ሙሶሎኒ ነበር።

በኢትዮጵያ በኩል ደግሞ በመጀመሪያው ጦርነት አምስትና ከዚያ በላይ ቤተሰባቸውን ያጡ ናቸው። የኔንም ብጠቅስልሽ አያቴ ደጃዝማች ስለሺ ከወንድሞቻቸው ጋር በዓድዋ ተዋግተዋል። የመጀመሪያውን ጦርነት ያየና የተሳተፈ ነው ጣሊያን ከ40 አመት በኋላ ዳግም ኢትዮጵያን ለመውረር ሲመጣ የተነሳው። በዳግመኛውም ቢሆን ጣሊያን የቱንም ያህል በዘመናዊ መሣሪያ ቢታጠቅና ብዙ ጦር ቢያሰልፍም በጀግኖች ኢትዮጵያውያን ሽንፈትን ተከናንቦ ነው ድል የተመታው።

በርግጥ በኢትዮጵያ በኩል በጦርነቱ የተጎዳው ሕዝብ ከፍተኛ የሚባል ነበር። አምስት ዓመት ሙሉ በየጫካውና በየዱሩ ተንገላተዋል። ከታሪክ እንደምንሰማው ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያን ለጠላት አሳልፎ ላለመስጠት ተጋድሎ ሲያደርጉ የፈረስ ሽንት እስከመጠጣት ደርሰዋል። ወራሪው ጣሊያን ኢትዮጵያውያኑ የሚጠጣ ውሃ እንዳያገኙ ወንዞችን ሳይቀር እስከመመረዝ ግፍ መፈጸሙ ጭምር ነው የሚነገረው። በአጠቃላይ የሁለተኛው ጦርነት ለኢትዮጵያውያን ፈታኝ ነበር ።

ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያን ፈታኝ የሆነውን ጦርነት

ወደ ገጽ 28 ዞሯል

# ‹‹ አሁን መጠየቅ ያለበት...

ከ27 ኛው ገጽ የዞረ

ተቋቁመው የሀገራቸውን ዳር ድንበር ባያስከብሩ ኖሮ ዛሬ ስለዓድዋ የድል ታሪክ አናወራም ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረውን ታሪክ ብቻ ሳይሆን፤ ከዚያ በኋላ ስላለውም ታሪክ ማውራት ቻልን። ጣሊያኖች ሲወጡ እረዳለሁ በሚል ሰበብ ደግሞ እንግሊዞችም መጥተው ነበር። እነርሱን ደግሞ በዲፕሎማሲ ነው ማስወጣት የተቻለው። አፄ ኃይለሥላሴ ቀድመው ካቢኔያቸውን በማቋቋምና ሚኒስትሮችንም በመሾም ተንቀሳቀሱ።

**አዲስ ዘመን፡- ትልቅ መስዋእትነት ተከፍሎበት የተገኘው ድል ዘመን ተሻጋሪ ሆኖ ትውልድ ተምሳሌት አድርጎት ለሀገሩ በተለያየ መንገድ እንዲያገለግል ምን መሠራት አለበት ይላሉ?**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** አሁን ያለው ትውልድ ቀላል ነው ብዬ አልወስድም። ጥሩ አእምሮ አለው። መሥራትም የሚችል ነው። ሀገር ወዳድም ነው። እንደሀገርም ጠንካራ የሠለጠነ የተገነባ ሠራዊት አለን። ትውልዱ ግን በድህነት ብዙ ፈተናዎችን አሳልፏል። አሁን ላይ ደግሞ ለትውልዱ ተስፋ የሚሰጡ ነገሮችም እየታዩ ነው። እጅ ላይ ባለው ስልክ የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ለማወቅ እድል አግኝቷል። የሀገሩንም ታሪክ ለማወቅ የሚያስችሉት ነገሮች ምቹ ናቸው። አሁን መጠየቅ ያለበት ድህነትን ለማሸነፍ ምን እንሥራ የሚለው ነው። ኢትዮጵያ በማዕድንም ሆነ በተለያየ ነገር የተፈጥሮ ሀብት አላት። ይህንን ወደ ኢኮኖሚ መለወጥ ያስፈልጋል ።

**አዲስ ዘመን፡- የዓድዋ ድል በዓል በየዓመቱ በተለያየ ዝግጅት ከመታወስ አልፎ ቋሚ የሆነ መታወሻ የሚሆን የዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም በመሀል አዲስ አበባ ከተማ ተገንብቷል። ይህ የመታሰቢያ ፕሮጀክት ያለውን ትርጉምና በጥውልዱ ውስጥ የሚፈጥረውን መነቃቃት እንዴት ይገልጹታል ለእርስዎስ የሰጠዎትን ስሜት ምን ይመስላል ?**


**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** የዓድዋ መታሰቢያ ፕሮጀክት በቅርጹና በይዘቱ ብቻ ሳይሆን፤ በውስጡ በያዛቸውም ታሪካዊ ቁሶች ከዓድዋ ድል ጋር እንዲገናኝ ጥረት የተደረገበት ነው። በተጓዳኝም መዝናኛዎች ተካትተዋል። ይሄ እየተዝናኑ ታሪክንም ለማወቅ እድል ይሰጣል። ይህን ትምህርት ሰጪ የሆነ ፕሮጀክት ወጣቱ ሊጠቀምበት ይገባል ። የያኔውን ኩነት አሁን እርሱ ከሚገኝበት ጋር በማነፃፀር ምን መስራት እንዳለበትም እራሱን እንዲጠይቅ ያስችለዋል። የእኔን ስሜት በተመለከተ፤ እውነት ለመናገር በደስታ አልቅሼያለሁ። ለፕሮጀክቱ እውን መሆን የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ብዬ አምናለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የታሪክ ቤት ነው ፤ የማህበሩ አባላት በተለያየ ምክንያት በሕይወት የማይኖሩበት ሁኔታ ሲከሰት ከመቻሉ አኳያ ማህበሩን ለማስቀጠል የታሰበ ነገር አለ?**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** በእኔ እምነት አንድ ማህበር ወይንም ድርጅት ሊፈርስ የሚችለው እራስ ወዳድ የሆነ አባል ወይንም መሪ ሲኖር ነው። ያለውን ሀብት ለመቀራመት እጅ ሲበዛበት ወይንም ለማጥፋት ዓላማ ተደርጎ ሲሠራ ነው ። በእውነት ለመሥራት ዝግጁ አለመሆንም ሌላው ጥፋት ነው። አሁን ላይ በማህበሩ እየተሠራ ያለው ሥራ ቤቱን በተለያየ መንገድ ማጥራት ነው።

የማጥራት ሥራው በውስጡ የሚሠሩት ሠራተኞች ያላቸው የትምህርት ዝግጅት ጭምር ያካትታል። አመራሮቹ የተማሩ ሰዎች መሆን አለባቸው የሚል እምነት አለኝ። የትምህርት ዝግጅት ባለው ሰው የሚመራ ከሆነ ክፍተቶችን መቀነስ ይቻላል። እስካሁን ጥሩ እንቅስቃሴዎች እየተደረገ ነው።

ከዓድዋ ድል ጋር በተያያዘ በአርቲስቶችና በተለያዩ ግለሰቦች ተነሳሽነት የኢትዮጵያውያንን የጀግንነት ታሪክ ለማውሳት ጥረት ተደርጓል። ለአብነትም አርቲስት ቻቺ ታደሰ በደቡብ አፍሪካ፣ መድረክ አዘጋጅታ ማህበሩ የተገኘውን መድረክ በመጠቀም ጥሩ ሥራ ተሠርቷል። በኬንያም በተመሳሳይ ድሉን፣ ታሪኩን፣ ጀግኖቹን የሚያስታውስ እና የኢትዮጵያንም ኩራት ከፍ የሚያደርግ ሥራ ለመሥራት ዝግት ተደርጓል። በዚህ መልኩ አፍሪካ ውስጥ መሥራት ተችሏል።



በአሜሪካን ሀገርም እንዲሁ አቶ ጥላሁን የተባሉ የታሪክ አዋቂ የማህበሩም የምክር ቤት አባል የሆኑ ሎሳንጀለስ ላይ ባዘጋጁት መርሃግብር ላይ ማህበሩን ወክዬ ተገኝቼ እንዲሁ ገለጻ አድርጌያለሁ። ይህም በዓለም ላይ በታሪካችን ለመታወቅ ያለውን እድል ጨምሮልናል።

የተጀመረው ሥራ የበለጠ እንዲጠናከርና የተሻለም እንዲሆን በውስጥ በተለይም ማህበሩን የምንመራው ሰዎች በእውቀት ላይ የተመሠረተ አመራር መስጠት ይጠበቅብናል ። ከራስ ወዳድነትም የራቅን መሆን ይጠበቅብናል። ማህበሩን በማቆየት ለተተኪ ትውልድ ማስተላለፍ እንድንችል ሥራችን ጥራት ሊኖረው ይገባል። ማህበሩ ዘላቂነት እንዲኖረው ደንባችንንም በየጊዜው ማሻሻል ይኖርብናል። የማህበሩን ሀብት የሚያሳድግ ሥራም መሠራት አለበት። ፍትሀዊ የሀብት ተጠቃሚነትም አብሮ የሚታይ ነው።

የማህበሩን አባላት በተመለከተም መንግሥት የሚሰጠንን ድጎማ በመጠቀም ማህበሩ የሚችለውን ሁሉ እያደረገ ነው። አዋቂዎች በሕይወት ባይኖሩም ማህበሩ ልጆቹን ይዞ ነው እየሠራ የሚገኘው።

**አዲስ ዘመን፡- ማህበሩ የሚተዳደርበት የገቢ ምንጭ በተመለከተና አባላት የሚገኙበትን ሁኔታና ያሉትን አባላት እንዲሁም ማህበሩ በክልሎች ስላለው እንቅስቃሴ ቢገልጹልኝ?**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** የማህበሩ አባላት ከ10ሺ በላይ ይሆናሉ። ግን መረጃ ማጣራት ይጠይቃል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማህበሩ የገንዘብ ድጎማ የሚያደርግላቸው አባላት ሁለት ሺ ይሆናሉ። በሥራቸው የሚያስተዳድሯቸው ቤተሰብ ሲጨመር ከፍ ይላል። ሁሉም አባላት በገንዘብ ቢታገዙ ጥሩ ነው ግን ገቢ ውስን በመሆኑ ማሟላት አልተቻለም። ይህም መንግሥት ስለሚያግዝ እንጂ በማህበር አቅም ተችሎ አይደለም። ስለዚህ ድጋፉን በእድሜ እና ባላቸው የኑሮ ሁኔታ በመለየት መታገዝ ያለባቸው እንዲታገዙ እየተደረገ ነው ።መንግሥት በፈቀደው ነፃ የሕዝብ የትራንስፖርትና የህክምና አገልግሎቶችም እየተጠቀሙ በመሆኑ በዚህ በኩልም ችግራቸውን ለማቃለል ጥረት ተደርጓል።

በአሁኑ ጊዜ ማህበሩ 14 ያህል ዞን አለው። ይሁን እንጂ በነዚህ ዞን ውስጥ የሚገኙት የአርበኛ ልጆችና ቤተሰቦች ተመዝግበው መረጃ ገና አልተያዘም። እዚህ ላይ አንዱ ችግር ምዝገባ ከተካሄደ ክፍያም አብሮ መፈፀም ይጠበቃል። የአቅም ጉዳይ ክፍተት እንዲፈጠር አድርጓል።

በአሁኑ ጊዜ አርበኞችም ሆኑ የአርበኞች ቤተሰቦች

**ወንዱም፣ ሴቱም በጋራ ለሀገራቸው አንድ ሆነው በመነሳታቸውና ትግሉንም በጋራ በመቋቋማቸው ነው ጦርነቱን በአንድ ቀን ድል ማድረግ የተቻለው**

በተበታተነ ሁኔታ ነው የሚኖሩት። ሰው ሊረዳቸው ቢፈልግ እንኳን አድራሻቸው ምቹ አይደለም። ረዳት የሌላቸውም አሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ከውጭ ገንዘብ ይልኩላቸዋል። ነገር ግን ገንዘቡን ተቆጣጥሮ በአግባቡ እንዲጠቀሙ በኃላፊነት የሚያግዛቸው ባለመኖሩ እየተቸገሩ ነው። እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት የአርበኞች መንደር ማቋቋም ያስፈልጋል የሚል እምነት አለኝ።

የአርበኞች መንደር ቢመሠረት መንግሥትም ሆነ ግለሰቦች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የማህበሩ አባላትን በቀላሉ ማገዝ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ። በዚህ ረገድም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባን እየጠየኩ ነው። ከንቲባዋ ሃሳቡንም የሚደግፉት ይመስለኛል። እስካሁንም ማህበሩን በተለያየ መንገድ እያገዙት ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበርን በመምራትዎ ምን ይሰማዎታል ? ማህበሩን ላለፉት ስምንት ዓመታት ሲመሩ ምን አስተዋጽኦ አደረጉ? ምንስ ይቀረኛል ይላሉ?**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን :-** ከውጭ ሀገር እንደመጣሁ ለ17 ዓመታት በልማት ኮሚቴ ውስጥ አገልግያለሁ። በዚህ እና በተለያዩ ሥራዎች ውስጥም እሳተፍ ነበር። በወቅቱ ማህበሩ ውስጥ አለመግባባቶችና የተለያዩ ችግሮች ነበሩ። ይህን የተገነዘቡና ለማህበሩ ተቆርቋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ማህበሩን እንድመራ ጥያቄ ቀረበልኝ። እኔም ይህን ታሪካዊ አጋጣሚ አላሳለፍኩም፤ ኃላፊነቱን ተቀብዬ ላለፉት ስምንት ዓመታት መርቻለሁ። ከዚህ በኋላ የሁለት መዓት እድሜ ነው የቀረኝ። ከዚያ በኋላ አገልግሎቴ ያበቃል። እስካሁን ምን አሳክተሃል ለተባልኩት ይህን ያህል ሰርቻለሁ ብዬ አፌን ሞልቼ የምናገረው ነገር የለም።

ግን ደግሞ አስተዋጽኦ አድርጌያለሁ። እኔ ወደመሪነት ከመምጣቴ በፊት አንድ አርበኛ አስር ብር ነበር ድጎማ የሚያገኘው። ድጎማው ወደ 2000 ብር ከፍ እንዲል አድርጌያለሁ። ዞን ላይ የሚገኙት እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ ወይንም እንዲችሉ የሚጠናከሩበትን መንገድ እያመቻቸን ነው።

በተጨማሪ የጀግኖች አርበኞች ማህበር አባላት ጥቅማጥቅም አንዱ የመቀበሪያ ሥፍራ ነው። በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ቀደም ሲል ሥላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከአርበኞች በስተቀር የሌላ ሰው ቀብር አይፈጸምም ነበር። አሁን ላይ ግን ይህ እየተከበረ አይደለም። በዚህ፣ም ቢያንስ የነርሱ ተጠቃሚነት ግምት ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ተችሏል።

ከመንግሥት ጋር በመሆንም የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራን ነው። መንግሥትም ለማህበሩ ትልቅ እክብሮት እንዳለው በተለያየ መልኩ በሚያደርገው እገዛ ይገለጻል። ከመንግሥት ጋር ከምንሠራቸው ሥራዎች አንዱ የትውልድ ግንባታ ላይ ነው። ወጣቱ ትውልድ የሀገር ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከዓድዋ ጀግኖች አባቶች እንዲማር በተለያየ ጊዜ በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ በመገኘት ከማህበሩ የሚጠበቁ ተግባራት አከናውነናል። በተለያዩ ዝግጅቶች ላይም ግብዣ ሲደርግልን አጋጣሚውን ተጠቅመን ጀግኖች አባቶች እንዲታወሱ አድርገናል ።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚገኙ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያንም ስለሀገራቸው ታሪክ እንዲያውቁ ፣ በተለይም በወላጆች ይህንን ሃላፊነት እንዲወጡ የምንችለውን ሁሉ እያደረግን ነው። የማህበሩ ህልውናም እንዲረጋገጥ በሚቻለው ሁሉ ጥረት እየተደረገ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ብዙ ሥራዎች ይቀራሉ። የማህበሩ ህልውና እንዲረጋገጥ ኃላፊነቱ የማህበሩ ብቻ አይደለም ፤ የሁሉም ዜጋ ነው ። የሚኮራበትን ታሪክ ያስመዘገቡት በዚህ ተቋም ውስጥ በማህበር የተሰባሰቡ ጥንታዊ አርበኞች ናቸው። ማህበሩ የገቢ ምንጭ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። በዚህ አጋጣሚ ዜጎች ማህበሩን በሃሳብ፣ በእውቀት፣ በገንዘብ እንዲያግዙ ጥሪ አቀርባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በጣም እናመሰግናለን**

**ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# የአፍሪካ ኩራት የሆነው ዓድዋ በዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም

**በኃይሉ አበራ**





ፎቶ- በሪሁ ታደሰ

የጥቁሮች የነጻነት ተምሳሌት ተብሎ ዓለም የመሰከረለት የዓድዋ ድል ኢትዮጵያውያን ምንጊዜም የሚኮሩበት፣ ብዙ ቁም ነገር የሚማሩበትና ሁልጊዜም ቢሆን ትኩስ የድል ስሜት ሆኖ የሚቀጥል እያደር አዲስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አባቶችና እናቶች ምስጋና ይግባቸውና አሜሪካንን ጨምሮ በርካታ የዓለም ሀገራት ከቅኝ አገዛዝ ነፃ የወጡበትን የነፃነት በዓል ሲያከብሩ፤ ኢትዮጵያ ግን የድል በዓሏን ስታከብር ዓለም ያውቃታል።

ከኢትዮጵያ አልፎ በቀኝ ግዛት እና በባርነት ውስጥ ለነበሩ አፍሪካ ሀገራት ነጻ መውጣትና ለፓን አፍሪካኒዝም መወለድ ምክንያት የሆነው የዓድዋ ድል እነሆ 128ኛ ዓመት ላይ ደርሷል፡፡ ዘንድሮ የሚከበረው ዝክረ ዓድዋም ካለፉት 127 ዓመታት ጋር ሲነጻጸር ልዩ የሚያደርገው አንድ ሁነት ከሰሞኑ በመዲናችን አዲስ አበባ መሀል ፒያሳ ላይ ተከውኗል፡፡ ይህ ክዋኔም ዓድዋን በልኩ ሊዘክርና ግዝፈቱን ሊያሳይ የተወከል የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ነው፡፡

በግዙፉ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም የሚከበረው 128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ለከተማው ነዋሪ ምን ስሜት ፈጥሯል፤ ሲል አዲስ ዘመን ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ስሜታቸውን እንደሚከተለው አጋርተዋል፡፡

ተማሪ ሃና ወንድምአገኝ የኢትዮጵያ እና የአዲስ አበባ ስካውት አባል ነች፡፡ ኢትዮጵያ በቅኝ ሳትገዛ ነጻነቷን አስጠብቃ የቆየች በመሆኑ በየዓመቱ የዓድዋ ድል በዓል ሲከበር የተለየ የደስታ ስሜት የሚፈጥርባት እንደሆነ ጠቅሳ፤ በባህላዊ መሣሪያ በመታገዝ ከሁሉም በላይ በሀገር ወኔ በአንድነት በቆሙ አባቶቻችን የተገኘው ድል ዛሬ ላይ ቀና ብለን ለመሄዳችን ምክንያት ነው ትላለች።

ለዚህ ታላቅ ድልም በቅርቡ ግንባታው ተጠናቅቆ ለጉብኝት ክፍት የሆነው የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም መገንባቱ እጅግ የሚያስደስት መሆኑን ገልጻ፤ እስካሁን ተግባራዊ አለመሆኑ የሚያሳዝን ቢሆንም አሁን ላለውና ከዚህ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ ጠቃሚ የሆነ ሙዚየም ነው ትላለች። ምክንያቱም ታሪካችንን በሚገባ በመሰነድ እና ለጎብኚዎችም በማሳየት ኢትዮጵያን የበለጠ ለማስተዋወቅ እና ከታሪካዊ የቱሪዝም ዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚገኝበት በመሆኑ ጠቀሜታው ከመታሰቢያም በላይ ዘርፈ ብዙ መሆኑን ተናግራለች።

አቶ ፍቅረሰላም መኮንን የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው፡፡ የዓድዋ ድል ከየትኛውም ጊዜ በላይ በአሁኑ ወቅት እውቅና ያገኘው መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አርበኞች፣ አባቶችና እናቶች በአንድነት ሆነው ያስመዘገቡትን የነጻነት ድል የዛሬው ትውልድም በጋራ ልማትና የሀገር ዕድገት ላይ ሊደግመው ይገባል ይላሉ፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ ትውልዱ የሀገሩን ታሪክ በጠራ መልኩ ማወቅ እና መረዳት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ ባለፈም ትኩረቱን ወደ ሥራ እና ልማት በማድረግ ጊዜው የሰጠውን ዕድል ሁሉ አሟጦ በመጠቀም የዓድዋ ድልን በኢኮኖሚው መስክ መድገም የሚጠበቅበት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

እሳቸው እንደሚሉት፤ አባቶቻችን የሀገር ነጻነትን ያስጠበቁበት የዓድዋ ድል ታሪክና ክብር በሚገባው ልክ የሚያውቅ ትውልድ መፈጠር አለበት፡፡ ለዚህም አሁን እየተደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ነው፡፡ በቅርቡም የተገነባውን የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም መጥቀስ ይቻላል፡፡ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየሙ ያለፈውን ታሪክ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ በመሆኑ ወጣቱ ትውልድ ታሪኩን በተጨባጭ ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚያስችለው ነው፡፡

ሙዚየሙ ስለ ዓድዋ እና ከዓድዋ ጋር ተያይዞ ስላለው የመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነት ታሪክ የሚያስረዳ በመሆኑ ትውልዱ ከዚህ ቀደም ከሚያውቀው በተጨማሪ ትልቅ ዕውቀት የሚጨምርለት ነው፡፡ ትውልዱ የተከፈለትን መስዋዕትነት ይበልጥ እንዲያውቅ የሚያግዘው ይህ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም በዚህ በአጭር ጊዜ መገንባቱም እጅግ አስደሳችና አኩሪ ታሪክ ነው ይላሉ፡፡ ትውልዱ የዓድዋን የድል ታሪክ በአግባቡ እንዲያውቅና እንዲረዳ ከማድረግ ባለፈ ሕዝቡን በአንድ ማስተሳሰር የሚችል መታሰቢያ ሙዚየም እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

አቶ ፍቅረሰላም፤ ባለፉት መቶ ዓመታት የተለዋወጡ መንግሥታት የዓድዋ ድል በዓል በዚህ ልክ እንዲታወስና ትውልዱ እንዲረዳው አላደረጉም፡፡ ይህ የሚያስቆጭ ነው፡፡ አሁን ግን የመላው ኢትዮጵያውያን ታሪክ የሆነው የዓድዋ ድል በሚመጥነው ከፍታ ከፍ ብሎ ታይቷል። ታሪካችንም መነበብ መታየት የሚችልበት ዕድል ተፈጥሯል፡፡ በመሆኑም በዚህ መታሰቢያ ሙዚየም አማካኝነት ኢትዮጵያ ከፍ ብላለች ዓድዋም የሚመጥነውን ክብር አግኝቷል፡፡ ስለዚህ ትውልዱ ከታሪኩ መማር ይኖርበታል ይላሉ፡፡

አንዳንድ ጸሐፍቶች እና የኢትዮጵያን እድገት የማይፈልጉ የዓድዋን ታሪክ አዛብተው ሲፅፉ እንደነበር ያነሱት አቶ ፍቅረሰላም፤ የዓድዋ ድል ሊደበዝዝ የማይችል ተነግሮ የማያልቅ ደማቅ አኩሪ ታሪክ እንደሆነ ነው የገለጹት፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትውልዱ ላይ በተፈጠሩ የተዛቡ ትርክቶች የጋራ አንድነትን እና ወንደማማችነትን ለመሸርሸር ተሠርቷል፡፡ ይሁንና ትውልዱ ታሪኩን መረዳት በሚችልበት የጋራ ትርክት ላይ በመሥራት አንድነትን እና ወንድማማችነትን ማጠናከር እንደሚገባ በማመላከት በቀጣይም ትውልዱ እንደ ጀግኖች አባቶቹ ሁሉ የጋራ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አንድነቱን አጠናክሮ በጋራ ሊቆም ይገባል በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል፡፡

ሌላው የመዲናዋ ነዋሪ የሆኑት አቶ ወራቄ ዑመር በበኩላቸው፣ ባለፉት ዓመታት ትውልዱ ታሪኩን በአግባቡ እንዳያውቅ ተደርጎ በተዛቡ ትርክቶች ውስጥ በመቆየቱ በትርክቶቹ ምክንያት ወደ አላስፈላጊ ግጭቶች ሲያመራ የነበረ መሆኑን አንስተው ሲያስረዱ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እነዚህን የተሳሳቱ ትርክቶችን ለማረም እና ዓድዋንም በሚገባው የታሪክ ከፍታ ልክ ለመገለፅ ተሠርቷል፡፡ ከተሠሩ ሥራዎች መካከልም የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም አንዱ ነው፡፡ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ከመታሰቢያነቱ ባለፈም የቱሪዝም ዘርፉን ለማነቃቃት ትልቅ አቅም ያለው ነው፡፡

በመሆኑም ትውልዱ ከዓድዋ ድል ብዙ ሊማር ይገባዋል፡፡ በተለይም፤ አንድነትን እና ለጋራ ጉዳይ በጋራ መቆምን ከዓድዋ አርበኞች በመማር ጀግኖች አባቶቹ ያቆዩለትን ሀገር በአንድነት ማስጠበቅ፣ ባህሉን እና እሴቶቹን መጠበቅ ይኖርበታል ይላሉ። ‹‹ጣልያን ተደራጅቶ እና ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቆ ለወረራ ሲመጣ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች አባቶች ግን በባዶ እግራቸው ከሁሉም አቅጣጫ በወኔ ወጥተው ድል ተቀዳጅተዋል›› የሚሉት አቶ ወራቄ፤ የዓድዋ ድል ከኢትጵያውያን ባለፈ የአፍሪካውያን ድል ኩራት መሆኑን ጠቅሰው በወቅቱ በባርነት ቀንበር ስር ለነበሩ አፍሪካውያን በሙሉ ነጻ የወጡበት ፋና ወጊ የነጻነት ድል ነው ብለዋል፡፡

‹‹አሁን ያለው ትውልድ አባቶቹ ያስረከቡትን ሉዓላዊት ሀገር በልማትና በቴክኖሎጂ ወደፊት ለማራመድ በቅድሚያ አንድነቱን ማጠናከር አለበት›› የሚሉት ደግሞ የሌተናንት አብዲሳ አጋ አምስተኛ ልጅ ወይዘሮ አኒሳ ወይም ኤልሳቤት አብዲሳ አጋ ናቸው። የሌተናንት አብዲሳ አጋ አምስተኛ ልጅ የሆኑት ወይዘሮዋ እንዳሉት አኒሳ አባታቸው ያወጡላቸው ስያሜ ሲሆን እናታቸው ደግሞ ኤልሳቤት ብለው ይጠሯቸው ነበር።

ወይዘሮ አኒሳ ወይም ኤልሳቤት እንደሚሉት፤ የኢትዮጲያውያን ማንነት የሚታወቀው በጀግንነት ነው፡፡ ጀግንነቱም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ታሪካዊ ከሆኑት ከጀግኖች እናቶች እና አባቶቹ የተወረሰ ነው። የዓድዋ ድልም የኢትዮጵያውያን ጀግኖች መታሰቢያ ድል ከመሆን ባለፈ የመላው ጥቁር ሕዝብ ኩራት በኢትጵያውያን ጀግኖች የተገኘ ድል ነው፡፡ ድሉ የመላው ኢትዮጵያውያን የጋራ ድል እንደመሆኑ አሁን ያለው ትውልድም የጀግኖች አባቶቹን ታሪክ በመድገም በልማት ዳግም ዓድዋን መፍጠር እንዳለበት አንስተዋል። በመሆኑም በሁሉም ዘርፍ ሀገሩን በጀግንነት መጠበቅ እና በጀግንነት የወረሰውን ነፃነት ማስቀጠል ይኖርበታል ነው ያሉት።

ወይዘሮ አኒሳ ወይም ኤልሳቤት፤ ወላጅ እናታቸው ከሆለታ የጦር ትምህርት ቤት በመውጣት ከአብዲሳ አጋ ጋር ጣልያን ድረስ የዘመቱ መሆኑን አስታውሰው፤ ‹‹ሴቶችም ሆነ ወንዶች ከአባቶቻቸው የወረሱትን የሀገር አደራ በመጠበቅ እና በጀግንነት ለሀገራቸው ብዙ ዋጋ ከፍለዋል›› በማለት የዛሬው ትውልድም ኢትዮጵያ ምን ላይ እንዳለች ዓይኑን ከፍቶ ማየት አለበት፡፡ ከአባቶቹም ሆነ ከታናናሾቹ መልካሙንና ለሀገር የሚጠቅመውን በጎ ሥራ የመሥራት ግዴታና ኃላፊነት አለበት በማለት አስገንዝበዋል፡፡

128ኛው የዓድዋ ድል በዓል ልዩ ዕትም

# የኢትዮጵያ የቦክስ ስፖርት አባት ያልተነገረ ታሪክ

ሰለሞን ገብረጊዮርጊስ (ዶ/ር)

ከገብረዝጊ (ማከ) ቤተሰብ መካከል በስፖርት ጎልቶ ስማቸው የሚጠቀሰው የኦሊምፒክ ተሳታፊ የነበሩት ሻምበል አርአያ ገብረዝጊ ናቸው፡፡ እርሳቸው፣ በሰፊው የኢትዮጵያ የቦክስ ስፖርት አባት ተብለው የሚታወቁ ሲሆን፤ ይህ ስም ቢያንሳቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም፡፡ እኚህ ታላቅ ሰው የቦክስ ስፖርትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያስተዋወቁ እና እንዲለመድ ያደረጉ ናቸው፡፡ በተጨማሪም እኤአ በ1964 የቶኪዮ ኦሊምፒክ የኢትዮጵያ የቦክስ ቡድን ዋና አሰልጣኝ እና መሪ ሆነው ተሳትፈዋል፡፡

ሻምበል አርአያ ህይወታቸው በበርካታ የክብር ዘመናት የተንቆጠቆጠ ቢሆንም፣ በተወሰኑ አጋጣሚዎች ግን ብርቱ ሀዘንና መከራን አሳልፈዋል፡፡ ከእርሳቸው ጋር በመጨረሻ የተገናኘሁት እኤአ በ1997 መጀመሪያ አካባቢ በደቡብ ኤርትራ መፋንሶ በሚባል መንደር ልጎበኛቸው በሄድኩበት ጊዜ ነበር፡፡ ይህ ሪፖርት የተጠናቀረው እርሳቸው ከነገሩኝ፣ ከሰጡኝ ሠነዶች፣ ከቦክስ ፌዴሬሽን ያገኘኋቸው መረጃዎች እንዲሁም ቀደም ሲል በአዲስ አበባ እኤአ 2019 ከቦክስ ስፖርት ባልደረቦቻቸው ጋር (በተለይ ከበቀለ አለሙ -ጋንቺ እና ኢንስፔክተር ታደሰ ኃይሌ ጋር) ካደረግኳቸው ቃለ መጠይቆች ነው፡፡

አርአያ ገብረዝጊ የተወለዱት እኤአ በ1923 በኤርትራ መፋልሶ ሰራዬ አካባቢ፣ ከመንደፈራ 7 ኪሎ ሜትር ከዋናው ከተማ አስመራ ደግሞ በስተደቡብ 60 ኪሎ ሜትር ላይ በሚገኘው ቦታ ነው፡፡ እድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላ ድረስ በግብርና ሥራ ላይ የቆዩ ሲሆን፣ በመቀጠል ወደ አስመራ በመጓዝ በጣሊያኖች ቡና ቤት እና በሽያጭና በመሳሰሉት ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ነበር፡፡

መካከለኛ ቁመት እና መጠነኛ የሰውነት አቋም ቢኖራቸውም በተቃራኒው ከፍተኛ የሆነ አካላዊ ጥንካሬ እና ብርታት ነበራቸው፡፡ (ሁኔታቸው ማይክ ታይሰንን ያስታውሰናል)፡፡ እሳቸው ይህ ችሎታ እንዳላቸው የተገነዘቡት ከጓደኞቻቸው ጋር በተለያዩ ጊዜያት የቡጢ ፍልሚያ በሚያደርጉበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ለቦክስ ልዩ ፍላጎት አደረባቸው፡፡ በወቅቱ የቦክስ ስፖርት ልክ እንደ እግር ኳስ፣ብስክሌት እና መኪና እሽቅድምድም ሁሉ በአስመራ በሚገኙ ጣልያኖች ዘንድ እጅግ ዝነኛ ነበር፡፡

ሻምበል አርአያ ጠንካራ ፕሮፌሽናል ቦክሰኛ መሆን በሕዝብ ዘንድ እውቅናና ክብርን እንደሚያስገኝ አስቀድመው በመረዳት፣ ፕሮፌሽናል ቦክሰኛ ለመሆን በወር 5 ሊሬ ለፈረንጆች እየከፈሉ ይሰለጥኑ ነበር፡፡ በኋላ ላይ በአዲስ አበባ ለቦክስ ስፖርት ባልደረቦቻቸው እንደተናገሩት፣ የቦክስ ስፖርት በአስመራ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኝ ነበር፡፡ ነገር ግን በስፖርቱ ዝነኛ ለመሆን መጀመሪያ ከጣሊያኖች በኋላ ደግሞ ከእንግሊዞች ጋር መወዳደር እና ማሸነፍ ግድ ነበር፡፡ ነገር ግን ነጮቹ እንደ ሻምበል አርአያ ካሉ ጥቁሮች ጋር ለመፋለም ብዙም ፍላጎት ያልነበራቸው ከመሆኑም በተጨማሪ የተወሰኑት ከነጭራሹ ለመፋለም ፍቃደኛ አልነበሩም፡፡ በተለይ በጥቁር በቦክስ ተመትተው ፊታቸው ደም በደም ሆኖ በጓደኞቻቸው እና በቤተሰቦቻቸው መታየት አይፈልጉም ነበር፡፡

ሻምበል አርአያ እና ጓደኞቹ የቦክስ ክህሎታቸውን በደንብ ካዳበሩ በኋላ፣ ይፋዊ ላልሆነ የወዳጅነት ፍልሚያ ነጮችን ጋብዘው የቦክስ ግጥሚያ ያደርጉ ነበር፡፡ ነጮቹም እንደፈሩት በቦክስ ድብደባ ምክንያት ፊታቸው ደም በደም ሆኖ ሲታይ ይመራቸው ነበር፡፡ ነገር ግን የሀገሬው ነዋሪ ቦክሰኞች በጊዜው የነበረውን የዘረኝነት ሰንሰለት መበጠስ ያልቻሉ ሲሆን፤ በዚህ ምክንያት ለትጋታቸው ምንም ዓይነት እውቅናም ሆነ የገንዘብ ሽልማት ያገኙም ነበር፡፡ እነዚህ የሀገሬው ነዋሪ የሆኑ ቦክሰኞች በየጊዜው ቅሬታቸውን እና አቤቱታቸውን ቢያቀርቡም ቅሉ ምንም ዓይነት ለውጥ አልነበረም፡፡ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ፣ አርአያን ጨምሮ ቢያንስ የተወሰኑ ቦክሰኞች መከራቸውን እና ችግራቸውን ሊፈታ የሚችል አማራጭ መፈለግ ጀመሩ።

ማግኘት የቻልኳቸው ሰነዶች እንደሚያሳዩት፣ አርአያ የሀገር ፍቅር ማህበርን እኤአ በ1942 በመቀላቀል በአባልነት እስከ 1952 ቆይተዋል፡፡ በ1940ዎቹ መጨረሻ አካባቢ አርአያ ከኤርትራ ለቀው በመውጣት የተሻለ ዕድል ይኖረኛል ብለው ወደገመቱበት ኢትዮጵያ ሀገራቸው ኑሯቸውን አደረጉ፡፡ መጀመሪያ ከአስመራ ወደ ደቀምሐረ በአውቶቡስ ተጉዘው፣ ከዛም ወደ አዲግራት በእግራቸው ተጓዙ፡፡ ወደ አዲስ አበባም ከትግራይ በመኪና ተጉዘዋል፡፡ በነበራቸው የቦክስ ችሎታ እና የሀገር ፍቅር ማህበር አባልነታቸው (ይህ ጊዜ ኤርትራ በእንግሊዞች አስተዳደር ሥር የነበረችበት እና ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን ሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት ጉጉት ያደረባቸው ጊዜ ነበር፡፡) በዚህ ምክንያት አርአያ በቃኘው ሻለቃ የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ዘብ ውስጥ በቀላሉ የሚሊተሪ ፖሊስ አባል ለመሆን ቻሉ፡፡ በወቅቱ የዚህ ክብር ዘበኛ አባል መሆን ታላቅ ክብር ነበር፡፡ በሚሊተሪ የፖሊስ አባልነት ከነበራቸው መደበኛ ሥራ በተጨማሪ፣ ለፖሊስ ኃይሉ የቦክስ አሰልጣኝ ሆነው ያገለግሉ ነበር፡፡



THE FATHER OF ETHIOPIAN BOXING

By

Solomon Ghebre-Ghiorghis Gebrezghi (Ph.D.)

Araia Gebrezghi as a young boxer in Asmara in the 1940s.

One of the remarkable personalities in the **Gebrezghi Family** was the Olympian **Captain Araia Gebrezghi**. He is widely and deservedly otherwise known as the **Father of Ethiopian Boxing.** He was the main person who introduced and

**በ19 አርባዎቹ ወጣቱ አርአያ ገብረዝጊ በአስመራ ከተማ በወጣት ቦክሰኝነት ጊዜው፣**

እኤአ ከ1960 እስከ 1963 ድረስ በተካሄደው የኮሪያ ጦርነት ወቅት፣ ከቃኘው ሻለቃ ጋር ወደ ሩቅ ምስራቅ በመጓዝ የሚሊተሪ ፖሊስ መኮንን በመሆን አገልግለዋል፡፡ በኮሪያ ዘመቻ ወቅት ጀግንነት ያሳዩ በመሆናቸው በወቅቱ የዘመቻው አዛዥ ከነበረው የአሜሪካ የጦር አዛዥ የምስጋና ምስክር ወረቀት ተበርክቶላቸዋል፡፡

ሻምበል አርአያ በቦክስ ስፖርት የላቀ የሙያ ህይወት የጀመሩት ከኮሪያ ዘመቻ ከተመለሱ በኋላ ነበር፡፡ በወቅቱ ከክቡር ዘበኛ ለቀው በመውጣት፣ ፖሊስ ሠራዊትን ተቀላቀሉ፡፡ ከመደበኛ ሥራቸው በተጨማሪ የራሳቸውን የቦክስ ስፖርት ክለብን በአዲስ አበባ መመሥረት ችለው ነበር፡፡ ክለቡንም "ሳምሶን የቦክስ ክለብ" ብለው ሰየሙት፡፡ በወቅቱ ከፖሊስ ሠራዊትና ከክቡር ዘበኛ የሚመጡትን እንዲሁም ሌሎች ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ጨምሮ ያሰለጥኑ ነበር፡፡ በተለያዩ የቲያትር እና የሲኒማ አዳራሾችም ውድድር ያዘጋጁ ነበር፡፡ የቦክስ ስፖርት በእሳቸው ተነሳሽነት ምክንያት በተጀመረው እንቅስቃሴ ተወዳጅ እየሆነ መምጣት ችሎ ነበር፡፡ እንዲያውም ከዚህ ባለፈ " በለው የቦክስ ክለብ " እና " የአዲስ አበባ ወጣቶች ክለብ" የተሰኙ ሁለት ተጨማሪ የቦክስ ክለቦች ተቋቁመው ነበር፡፡

የአዲስ አበባ ወጣቶች ክለብ በእስጢፋኖስ መንግሥቱ ባለቤትነት የተያዘ ነበር፡፡ እነዚህ 3 ክለቦች ቦክሰኞቻቸውን በመምረጥ በተለያዩ መድረኮች እንዲፋለሙ ያደርጉ ነበር፡፡ ሻምበል አርአያ እኤአ በ1964 ወደ ጃፓን ቶኪዮ ኦሊምፒክ የተጓዙት ብሔራዊ የቦክስ ቡድን መሪ እና ዋና አሠልጣኝ ሆነው ነበር፡፡ በኋላ ላይ ደግሞ በኮንጎ በተካሄደው የመላው አፍሪካ ጨዋታዎች በዚሁ ኃላፊነት ተሹመው ነበር፡፡ በቶኪዮ ኦሊምፒክ ላሳዩት ውጤታማ ሥራም የኢትዮጵያ መንግሥት የምስጋና ደብዳቤ አበርክቶላቸዋል፡፡

ሻምበል አርአያ ኦሊምፒክና መላ አፍሪካ ጨዋታዎችን ጨምሮ በበርካታ ውድድሮች መሳተፍ የቻሉ ቦክሰኞችን በሰልጣኝነት ዘመናቸው ማፍራት ችለዋል፡፡ ከነዚህ መካከል፡-

ከአዲስ አበባ ጥላሁን እሸቴ፣ አሰፋ አግነው ፣ ንጉሤ ኃይለጊዮርጊስ ይጠቀሳሉ፡፡ ከአስመራ ደግሞ ተስፋሚካኤል፣ አደም ፋላ፣ ማሞ በየነ ይታወሳሉ፡፡ ሻምበል አርአያ አሰልጣኝና ቡድን መሪ ሆነው ወደ ቶኪዮ ኦሊምፒክ ከዚያም ከአንድ ዓመት በኋላ እኤአ በ1965 መላ አፍሪካ ጨዋታ ላይ ካሳተፋቸው ቦክሰኞች መካከል አበበ መኮንንና ታደሰ ገብረጊዮርጊስ ከአዲስ አበባ፣ ታደሰ ገብረጊዮርጊስ፣ ንጉሤ ሀብተጊዮርጊስ፣ በቀለ አለሙ-ጋንቺ ከአስመራ ይገኙበታል፡፡

ሻምበል አርአያ ባገኙት ሰፊ ዝና እና ችሎታ ምክንያት፣ በእሳቸው እና በጣሊያን ታዋቂ በነበረው ቦክሰኛ ፍሬዝጊ ገብረሥላሴ መካከል በአስመራ ከተማ በ1960ዎቹ የቦክስ ውድድር ተካሂዶ ነበር፡፡ ፍሬዝጊ ወደ አስመራ ለውድድር ሲመጣ አርአያም ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ በመሄድ በውድድሩ ተገናኝተዋል፡፡ ውድድሩም በአቻ ውጤት ነበር የተጠናቀቀው፡፡

ሻምበል አርአያ ከአሰልጣኝነት እና ከተወዳዳሪነት ባሻገር የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ኢንተርናሽናል የቦክስ የሪንግ ዳኛ እና ከሪንግ ውጭ ዳኛ ሆነው የሰሩበት ታሪክም አላቸው፡፡

ሻምበል አርአያ እና የኢትዮጵያ ቦክስ ቡድን በ1968 የሜክሲኮ ኦሊምፒክ ላይም ተሳትፈዋል፡፡ ከሜክሲኮ በኋላ ግን፣ በአቶ ይድነቃቸው ተሰማ ይመራ በነበረው በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከቦክስ ውድድር ወደ ማራቶን እና ሌሎች ሩጫ ስፖርቶች ትኩረቱን አዞሮ ነበር፡፡ ቦክስ ከሩጫ ውድድር ይልቅ ከፍተኛ አካላዊ ዝግጅት የሚያስፈልገው እና ከፍተኛ በጀት የሚፈልግ በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን የአካል ቁመና የተመቸ ስፖርት ላይሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የቦክስ ስፖርት በኢትዮጵያ ያለው ተፈላጊነቱ እየቀነሰ ሄደ፡፡ የቦክስ ቡድኖች በከፍተኛ ድካም የሚገነቡ እና ከባድ ሥራን የሚጠይቁ በመሆኑ፣ ከመንግሥት በቂ ክትትል እና ድጋፍ ስላልተገኘ፣ የቦክስ የቡድን አባላቶች በየፊናቸው ተበታተኑ፡፡ ሻምበል አርአያም ከቦክስ ስፖርት በጡረታ በመገለል፣ በፖሊስ መኮንንነት ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ በዚህ ሙያቸው በሐረር በመቀጠል ደግሞ ደሴ ተመድበው ነበር፡፡ በመጀመሪያ ኢትዮ-ሶማሌ ጦርነትም ተሳትፈዋል፡፡ በመቀጠልም ወደ ሸዋ ፖሊስ ከዛም አዲስ አበባ ወደሚገኘው የፖሊስ ዋና መስሪያ ቤት በፖሊስ ሻምበልነት ተመደቡ፡፡ ከዚያ በኋላ ነውም ነው በጡረታ የተገለሉት፡፡

ሻምበል አርአያ ዮሴፍ የሚባል ልጅ ነበራቸው፡፡ ልጃቸው ጎበዝ እና ታታሪ የነበረ በመሆኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ባልደረባ ሆኖም ይሰራ ነበር፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከሥልጣን ከተወገዱ በኋላ፣ ወታደራዊው ደርግ ወደ ሥልጣን በመምጣት ተቃዋሚዎችን በተለይም ኢህአፓን ለማጥፋት የቀይ ሽብር ዘመቻ በመጀመሩ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣት ኢትዮጵያውያንን ለእስር እና ለሞት ተዳረጉ፡፡ ዮሴፍም የኢህአፓ አባል ነህ በሚል ተጠርጥሮ በአዲስ አበባ ከርቸሌ ወደሚባለው እስር ቤት ተወረወረ፡፡ የስኳር ህመምተኛ የነበረ በመሆኑ እና ደርግም መድኃኒቱን እንዳይወስድ የከለከለው በመሆኑ በሽታው በፈጠረበት የጤና መወሳሰብ ህይወቱ አለፋል፡፡ እስከሬኑ ወደ ምኒልክ ሆስፒታል ከተወሰደ በኋላ በ1982 በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ቀብሩ ተፈፅሟል፡፡ ይህ ለሻምበል አርአያ እጅግ ልብ የሚሰብር ክስተት ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ በኋላ ሕይወት ለሻምበል አርአያ ጥሩ አልነበረችም፡፡


በዚህ ምክንያት ሻምበል አርአያ ከእውነታው ውጪ በሆነ አስተሳሰብ በመያዝ፣ አብዝተው የአልኮል መጠጥ ይጎነጩ ስለነበር የአካልም ሆነ የአእምሮ ጤናቸው እያሽቆለቆለ ሄደ፡፡ ይከፈላቸው የነበረው ጡረታ በቂ ባለመሆኑም በአዲስ አበባ ከሚገኙት እጅግ ከተጎሳቆሉ መንደሮች መካከል በ4 ኪሎ በሚገኘው መኖሪያ ሰፈር ለመኖር ተገደው ነበር፡፡ በዚህም ቤተሰባቸው በተለይም እናታቸው ለተንስኤ ትተውለት ባለፉት እና በመፋልሶ በሚገኘው ቤታቸው እንዲኖሩ ወስደዋቸው ነበር፡፡ ጥሩ አጋጣሚ ሆኖ ሻምበል አርአያ ወጣት የሆነች ሚስት ያመጡላቸው ሲሆን፣ ለተወሰኑ ዓመታትም አብራቸው ኖራለች፡፡ ነገር ግን በሚከፈላቸው ጡረታ ማነስ እና ምናልባትም ዕድሜያቸው በመግፋቱ ምክንያት በድንገት ጥላቸው ልትሄድ ችላለች፡፡

በህይወቱ ከፍተኛ ቦታ ለመድረስ የቻለው ታላቁ የቦክስ ስፖርት ሰው፣ ከኮሪያና ከጃፓን ርቆ በሚገኘው አንድ የአፍሪቃ መንደር ተወስኖ፣ ከአንድ ውብ የነበረች የዮኮሃማ፣ (ጃፓን) ፍቅረኛው በቶኪዮ ከተማ የተነሱት ፎቶግራፍ እያየ በስተ እርጅናው ብቻውን ይኖር ነበር፡፡ እንደበፊቱም ራሱን መሆን አልቻለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ይህ በሕይወቱ ለሀገር ታላቅ ሥራ የሠራው ባለውለታ መሆኑን ሳያውቁና እርሱ ባልፈጠረው ከልጁ ጋር በተያያዘ ቀውስ ለዚህ ዕጣፋንታ መዳረጉን ሳይገነዘቡ፣ መጥፎ ነገር ሲናገሩትና ሲያጣጥሉት "እኔኮ ጀግና ወታደር ነኝ!!!" ብሎ ይመልስላቸው ነበር፡፡ ይህን መስማት ታሪኩን ለሚያውቁ ሰዎች እጅግ ልብ የሚሰብር ነበር፡፡ ቀደም ሲል ያገኘው ዝና፣ በዓለም ደረጃ ተሳታፊነቱና የሀገር ባለውለታ መሆኑን ዘንግቶት ነበር፡፡ ወጣትነቱን የሰዋለትና ያን ያህል የደከመበት ሙያ የሚገባውን አልከፈለውም፡፡

# የስፖርቱ ዓለም ዓድዋ!!

ቦጋለ አበበ




ታላቁ የዓድዋ ድልና የአበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ድል ታሪካዊ ግጥምጥሞሽ ሁሌም አስገራሚና እንደአዲስ የሚነገር ነው። ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ቅኝ ገዢው ጣልያን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ እስካፍንጫው ታጥቆ ለመውረር ሲመጣ እጅግ ኋላ ቀር በሆነ መሳሪያ በወኔ፣ አልሸነፍ ባይነትና አስደናቂ ጀግንነት ድል ተደርጎ ተመልሷል። ይህም በጥቁር ሕዝቦች የጦርነት ታሪክ ህያው ድል ሆኖ ከመዘከሩ ባለፈ በዓለም ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ ተዘርዝሮ የማያልቅ ተጽእኖ ማሳደር ችሏል።

የአበበ ቢቂላም የ1960 ሮም ኦሊምፒክ የማራቶን ድል ተመሳሳይ ነው። አበበ የአባቶቹን ሀገር በግፍ ለመውረር በመጣው ጣልያኖች ሀገር በወቅቱ ዘመናዊ ስልጠናና ዝግጅት አድርገው ምቹ የመሮጫ ጫማ ካጠለቁ አያሌ ነጮች ውስጥ በባዶ እግሩ አፈትልኮ ሌላኛውን የዓድዋ ድል ተምሳሌት ሮም ኦሊምፒክ ላይ ፈጽሟል። ይህም ድሉ በኦሊምፒክ መድረክ የጥቁር አትሌቶች ፋና ወጊ ድል ከመሆኑ ባሻገር ልክ እንደ ዓድዋ ሁሉ ጥቁሮች በስፖርቱ መድረክ ቀና ብለው እንዲሄዱ የማይፋቅ አሻራውን አሳርፏል።

በዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች ጥቁሮች አሁን ላይ በየትኛውም ዓለም አቀፍ መድረክ ተፎካካሪ እንዲሆኑ ከማስቻል ባሻገር በትልቅ ደረጃ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ለማሳየት በርካታ ጥቁር ከዋክብት ብዙ ችግሮችን ተጋፍጠዋል። በተለይም ጥቁር አሜሪካውያን አትሌቶች በዚህ ረገድ ያዩት ፈተና ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም።

አፍሪካውያንም ቢሆኑ በርካታ መከራዎችን ተጋፍጠው ለታላቅ ክብር በመብቃት ለአሁኖቹ አትሌቶች ፋና ወጊ ሆነው እኩልነትን ማንፀባረቃቸው አይካድም። ለዚህም ታሪካዊውን ኢትዮጵያዊ የማራቶን ኮከብ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ በትልቁ የሚነሳ የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆኖ እናገኘዋለን።

ኢትዮጵያውያን በስፖርቱ ብቻም ሳይሆን በዓድዋ ድል የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌትና የማዕዘን ድንጋይ ሆነዋል። የጥቁር ሕዝቦች ኩራት የሆነው የዓድዋ ድል የሚዘከርበት የካቲት ወር በመላው ዓለምም የጥቁር ሕዝቦች መታሰቢያ ሆኖ ይከበራል።

በስፖርት መድረክ ዘረኝነትን የታገሉ፤ እኩልነትን ያንፀባረቁና በድላቸው የጥቁር ሕዝቦችን አንገት ያቀኑ በርካታ ጥቁር ከዋክብቶች መኖራቸው አይካድም። ከነዚህ ከዋክብቶች ግን ተፅዕኗቸው ከፍተኛ የነበረ፤ ድላቸው በርካታ ትርጉም የነበረውና በትልቅ ደረጃ ከሚነሱት መካከል የታላቁ ዓድዋ ድል ባለቤት የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንቁ ልጅ አበበ ቢቂላና የሮም ኦሊምፒክ ህያው የማራቶን ድል ተጽእኖ ቀላል እንዳልነበረ በብዙ ድርሳናት ተጽፎ ይገኛል።

1928 ፋሺስት ጣሊያን በአምባገነኑ ቤኒቶ ሞሶሎኒ በመመራት ኢትዮጵያን ከወረረ ከሃያ አራት ዓመታት በኋላም ታላቁ አበበ ቢቂላ ታላቋን ሮም በባዶ እግሩ ወሮ ዓለምን ጉድ አሰኘ። የምንጊዜም የማራቶን ንጉሱ የአፍሪካውያን ኩራትና የነፃነት ተምሳሌት እንዲሁም፤ የመጀመሪያው ጥቁር የማራቶን ኦሊምፒክ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ በጥቁሮቹ ጀግኖች መታሰቢያ ወር የካቲት የጥቁር ሕዝቦች ኩራት ሆኖ ከስልሳ ዓመት በፊት በኢትዮጵያውያን አዲስ ዓመት ዋዜማ በሮም ኦሊምፒክ የፈፀመው ታሪካዊ ጀብድ በመላው ዓለም ያሉ ጥቁር አትሌቶችን በእጅጉ ያኮራና ያነሳሳ ነበር።

ጳጉሜን 5 ቀን 1952 አስራ ሰባተኛው የሮም ኦሊምፒያድ በታላቋ ሮም ጎዳናዎች በርካቶች አይናቸውን ለማመን የተቸገሩበት ጀብድ በአምባገነኑ ሞሶሎኒ ሀገር በበርካታ ነጮች መሐል አንድ ጥቁር በባዶ እግሩ ይጽፈዋል ብሎ ማንም አልጠረጠረም። ልክ እንደ ዓድዋ ድል ሁሉ የጥቁር ሕዝቦች ተአምርን ለመቀበል የሚተናነቃቸው ዘረኝነትን በደማቸው ያሰረፁ ነጮች እንዴት ይህ ሊሆን እንደቻለ አሁንም ድረስ ግራ ይጋባሉ። አፍሪካውያንን ያኮራ ኢትዮጵያውያንን ከልብ ያስፈነጠዘው ታሪካዊ ድል በአበበ ቢቂላ ቀጫጭን እግሮች በወርቅ ቀለም መጻፉ ግን እየተናነቃቸውም ቢሆን ሊያላምጡት ተገደዋል።

ከ83 ሀገራት የተውጣጡ ከ5ሺ በላይ አትሌቶች በተካፈሉበት የሮም ኦሊምፒክ፤ የዓለም ሕዝብ ትኩረት በአውሮፓውያን አትሌቶች ላይ ነው፤ ስለኢትዮጵውያን አትሌቶች በተለይም ስለ አበበ ቢቂላ የሚያውቀው ነገር አልነበረም። አበበ ቢቂላ ወይም ሌላ አፍሪካዊ አትሌት ሊያሸንፍ እንደሚችል አልተጠበቀም። ከዚያ በፊት አንድም አፍሪካዊ በኦሊምፒክ ታሪክ ሜዳሊያ አግኝቶ አያውቅም።

የሮም ኦሎምፒክ የማራቶን ውድድር ግን፤ የዓለምን ታሪክ ቀየረ። የውድድሩ ውጤት፤ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን፤ ለመላው አፍሪካና ለዓለም ጥቁር ሕዝብ ድል ያበሰረ ችቦ አቀጣጠለ። ኢትዮጵያዊያው አትሌት አበበ ቢቂላ በባዶ እግሩ ሮጦ ታላቁን የኦሊምፒክ ማራቶን በአንደኝነት ከማሸነፍም በተጨማሪ፤ 2፡15፡16.2 በሆነ ሰዓት አዲስ የዓለም ክብረወሰን አስመዘገበ። በኦሊምፒክ ታሪክ የሜዳሊያ ባለቤት ለመሆን የቻለ የመጀመሪያው አፍሪካዊ ስፖርተኛ ሆኖ ስሙ በታሪክ መዝገብ በወርቃማ ቀለም ሰፈረ።

አበበ ቢቂላ የማራቶንን ርቀት ሮጦ ያሸነፈውና ሪከርድ ያስመዘገበው፤ በባዶ እግሩ መሆኑ ደግሞ የመላ ዓለም ስፖርት አፍቃሪዎችን በእጅጉ ያስደነቀ ነበር። የአበበ ቢቂላን ስምና የኢትዮጵያን ዝና በመላው ዓለም ተቀርፆ እንዲቀር አድርጓል። በዓድዋ ጦርነት ላይ የዘመቱ ኢትዮጵያውያን ባዶ እግራቸውን እንደነበሩ ያስታውሳል። ጋዜጠኞች አበበ ለምን ያለ ጫማ በባዶ እግሩ እንደሮጠ ጠይቀውታል፣ "ዓለም ሁሉ እንዲያውቅ ፈልጌ ነው" ሲል የተናገረው አበበ፤ "እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሌም የምናሸንፈው በጀግንነትና በወኔ እንደሆነ፤ ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅ በመፈለጌ ነው" ብሏል። የዓድዋን የጦርነት ታሪክ እያስታወሰ።

የአራት ዓመት ታዳጊ ሆኖ እናት ሀገሩ ኢትዮጵያ በጣሊያን ፋሽስት ስትወረር መጥፎውን ጊዜ ገና ባልጎለበተ የሕፃን አዕምሮው የሚያስታውሰው አበበ ቢቂላ፣ ሃያ ስድስት ዓመታት ጠብቆ ታላቁን የሮም ጎዳና በባዶ እግሩ ወሮ የማይደገመውን ታሪክ አኑሯል።

ከአራት ዓመት በኋላም 1956 በድጋሚ ጫማ አጥልቆ በቶኪዮ ኦሊምፒክ ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር አሸንፎ ጥቁሮች በማይደፈረው ርቀት አሁን ላይ ቁንጮ እንዲሆኑ መሠረቱን ጣለ። እሱ በከፈተው በርም ቁጥር ስፍር የሌላቸው የማራቶን አትሌቶች ለዘመናት ለርቀቱ የተፈጠሩት እነሱ ብቻ እስኪመስሉ አሁን ድረስ በዓለም አደባባይ እያንጸባረቁ ነው።

አበበ ምናልባት ያንን ውድድር ባያሸንፍ ኖሮ የጥቁር አትሌቶች በተለይም የረጅም ርቀት ታሪክ ዛሬ ከምናውቀው ተቃራኒ ሊሆን እንደሚችል በርካቶች ይስማማሉ።

እርግጥ ነው በሮም ኦሊምፒክ አበበ ብቸኛው ተሳታፊ አልነበረም። ብቸኛው ወርቅ ያጠለቀም አትሌት አይደለም። በዚያ ኦሊምፒክ ከተሳተፉ ጥቁሮች መካከል ሌላ ባለድልም ነበር። አሜሪካዊው ጥቁር የቡጢ ተፋላሚ መሐመድ ዓሊ በቀላል ሚዛን የወርቅ ሜዳልያ ተጎናፅፎ ነበር። ቢሆንም ኦሊምፒኩ በመሐመድ ዓሊ ወርቅ ሜዳልያ እምብዛም የደመቀ አልነበረም።

በወቅቱ ታሪክ የሚያስታውሰው ሌላ ክስተትም ነበር። ጊዜው ደቡብ አፍሪካ በአህጉራዊ ውድድሮች ለመጨረሻ ጊዜ ተሳትፋ የታገደችበት ነበር። የእገዳዋ ምክንያት ደግሞ ትከተለው በነበረ የአፓርታይድ ሥርዓት መሆኑ ነው። ቢሆንም የያኔ የሮሙ ኦሊምፒክ በመሐመድ ዓሊ የወርቅ ሜዳልያም ይሁን በደቡብ አፍሪካ መታገድ አይደለም የሚታወሰው።

ታዲያ በምን ይታወሳል? ያሉ እንደሆነ በውድድር ዘመኑ የማራቶን ሩጫ ያለ ጫማ ሮጦ የርቀቱ አዲስ ክብረወሰን ባስመዘገበው ኢትዮጵያዊ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ነው። በወቅቱ በርካታ ሊጠቀሱ የሚችሉ ነገሮች ቢከናወኑም አበበ ግን ታሪኮችን ሁሉ ልቆ የሚታወስ ድንቅ ታሪክ አስመዘገበ።

ያኔ፣ አይደለም አበበ ቢቂላ የሚባል አትሌት፣ ኢትዮጵያ ተብላ ስለምትጠራ ሀገርም የሚያውቅ ነጭ ብዙም አልነበረም። ይሁን እንጂ ውድድሩ በጣሊያን መካሄዱ እና የጣሊያን ወረራ በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ተጠናቅቆ ድል የመጨበጧ ወሬ ገና ከዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች የወሬ አጀንዳነት ባለመረሳቱ፣ የአበበ ቢቂላ ድል ገነነ። ለዚህም ነው ብዙዎች የአበበ ድልና ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች የጦርነት ድል ዓድዋ የሚመሳሰልባቸው ወይም የሚገጣጠምባቸው። አበበ ቢቂላ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈበት የማራቶን ውድድር አሸነፈ። የጥረት እንጂ የአጋጣሚ ጉዳይ አይደለም። ጀግና፤ ጀግናን ያፈራል።

የዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ሳይቀሩ ባልተጠበቀው የአትሌት አበበ ቢቂላ ድል ተደምመው ደጋግመው፣ በባዶ እግር ሮጦ የወርቅ ሜዳልያ ስላገኘው ኢትዮጵያዊው አትሌት ተናገሩ። በውድድሩ ማግስትም የጣሊያን ጋዜጦች ‹‹ኢትዮጵያን ለመውረር የኢጣሊያ ሀገር ወታደር ሁሉ አስፈልጎ ነበር፤ ኢትዮጵያ ግን አንድ ወታደር ብቻ ልካ ድፍን ሮምን ወረረችው›› የሚል ጽሑፍ ይዘው ወጡ። ይህም አጋጣሚ ብዙ ጥቁር አፍሪካውያን በዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፉ በር ከመክፈቱ በዘለለ ከቅኝ ግዛት ለመላቀቀ የነጻነት ትግል በማድረግ ላይ ለነበሩ የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ የ”ይቻላል” መንፈስና ትልቅ የስነልቦና ስንቅ ሆኗቸዋል።

የአበበ ቢቂላ አንፀባራቂ ድሎች ለአፍሪካውያን በፋና ወጊነት ጠቅሟቸዋል። በኩራችን ብለውም ሰይመውታል። አዲስ አበባ በ2000 ዓ.ም. ያዘጋጀችውን 16ኛውን የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አጋጣሚን ምክንያት በማድረግ በ50 ዓመታት ውስጥ ለአፍሪካ አኩሪ ታሪክ የፈጸሙ አትሌቶች ሲሸለሙ፤ አውራው ተሸላሚ አበበ ቢቂላ ነበር። ‹‹የአፍሪካ ማራቶን አባት›› ተብሎም በዶክመንተሪው ፊልም ላይ ተመልክቷል።

አፍሪካውያን ለአበበ ያላቸው ፍቅርና አክብሮት እስከዚህ ድረስ ነው አይባልም። የአፍሪካ አትሌክስ ሻምፒዮና በሴኔጋል መዲና ዳካር በ1971 ዓ.ም. ሲጀመር ወደ ዳካር ስታዲየም የሚያስገባውን መንገድ ‹‹አበበ ቢቂላ ጎዳና›› በማለት መሰየሟ ይታወሳል። ኢጣሊያም ብትሆን ለአበበ ክብሩን አልነፈገችም። የሮም ኦሊምፒክ 50ኛ ዓመትን ስትዘክር አንድ ድልድይ በስሙ ሰይማለች።

አምስተርዳም ከተማም የአበበ ቢቂላ መንገድ አላት። ‹‹ቶኪዮ ኦሊምፒያድ›› በተባለው የትረካ ፊልም ላይ የአበበ ቢቂላ የቶኪዮ ድል ተጨምሯል። ከዚሁ ፊልም የተወሰደ ክፍልም በ1968 በተሠራው ‹‹ማራቶን ማን›› በተባለው ፊልም ላይ ይገኛል። ‹‹ቪብራም›› የተባለ የአሜሪካ የጫማ አምራች ድርጅት በ2002 ‹‹ፋይቭ ፊንገርስ ቢቂላ” (Five Fingers Bikila) የተባለ ጫማ ለገበያ አቅርቧል።